ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

# ረቂቅ የተሻሻለ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ

የግብርና ሚኒስቴር

2014 ዓ ም

ማውጫ

1. መግቢያ ..... 1
2. የፖሊሲ ማሻሻያ አስፈላጊነት..... 2
3. የተሻሻለው ፖሊሲ ርዕይ፣ ግቦች፣ ዓላማዎችና መርሆች ..... 4
4. የፖሊሲው አድማስ..... 6
5. ማሻሻያ የተደረገባቸው የፖሊሲ ጉዳዮች ..... 6
5.1 የመሬት፣ ደንና ተፈጥሮ ሃብት አስተዳደርና አጠቃቀም 8
5.2 የቴክኖሎጂ፣ ግብዓት እና አገልግሎት አቅርቦት ስርዓት 16
5.3 የውሃ አጠቃቀም እና አስተዳደር 37
5.4 የምርት ግብይት 42
5.5 የገጠር ኢኮኖሚ ልማት 48
5.6 መሰረተ ልማት 51
5.7 የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግና ማጠናከር 55
5.8 የግብርናና ገጠር ልማት ፋይናንስ ሥርዓት 57
5.9 ተቋማዊ የአሰራር ስርዓት 61
5.10 ዘርፈ-ብዙ ጉዳዮች 68
6. የፖሊሲው አፈፃፀም ማዕቀፍ ..... 76
7. ፖሊሲውን የማስፈፀም ኃላፊነት ያለባቸው ተቋማት ..... 77
8. የፖሊሲ ክትትል፣ የግምገማ እና የክለሳ ስርዓት ..... 77
9. የፖሊሲው ስርጭት..... 77
10. ፖሊሲው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ ..... 77
11. የቃላት መፍቻ..... 78

# 1. መግቢያ

የግብርና ዘርፍ ብዙ የሰዉ ኃይል የተሰማራበት በተለይም ለገጠሩ ህብረተሰብ የኑሮ ዋስትና መሰረት ነዉ። ዘርፉ ሰብል ፣ እንስሳትና አሳ እና የደን ውጤቶችን በማምረት ከአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ውስጥ በ2013 ዓ.ም የ32.5 በመቶ ድርሻ የሸፈነና የኢኮኖሚ መሰረት በመሆን ለሀገራዊ የጥቅል ኢኮኖሚ (ማክሮ ኢኮኖሚ) ከፍተኛ አስተዋፅዖ እያበረከተ ይገኛል። በተጨማሪም ዘርፉ ለሀገሪቱ የምግብና ስርዓተ ምግብ ዋስትና፣ የውጭ ምንዛሪ እና የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ ዋናው ምንጭ ከመሆኑም በላይ ቁልፍ የህልውና መሰረት ነው።

የግብርናና ገጠር ልማት የሚመራበት የገጠር ልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና ስልቶች በ1994 ዓ.ም ተቀርፆ ስራ ላይ ውሏል። ይህንኑ መሠረት ባደረጉና በተከታታይ ዓመታት ሥራ ላይ በዋሉ የልማት ዕቅዶች ተነድፈው የግብርናና ገጠር ልማትን ትኩረት ተሰጥቶ ሀገራዊ ኢኮኖሚ ውስጥ የበኩሉን ድርሻ ሲጫወት ቆይቷል። ይህን ተከትሎም ከነበረበት አነስተኛ የእድገት ደረጃ አንፃር ሲታይ በግብርና ከፍተኛ ምርትና ምርታማነት ዕድገት ከመመዝገቡም ባሻገር ዘርፉ የሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች እድገት እንዲፋጠን የመሪነት ሚናውን ተጫውቷል። በገጠር የነበረው የድህነት ደረጃ ቀንሷል።

ሆኖም የዘርፉ ዕድገት ከአዳጊ የምርት ፍላጎት ጋር አብሮ መጓዝ ባለመቻሉ ምክንያት በቂ ምግብ የማያገኙ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ዜጎች ይገኛሉ። ኢንዱስትሪ የሚፈለገውን ጥሬ ዕቃ በበቂ አይነት፣ መጠንና ጥራት ማቅረብ አልተቻለም። በተጨማሪም ለውጪ ንግድ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶችን አቅርቦት ማሳደግና ተወዳዳሪነት ማረጋገጥ እንዲሁም ከውጪ የሚገቡ የግብርና ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት አልተቻለም።

ስለሆነም የዘርፉን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ፣ መልካም አጋጣሚዎችን ለመጠቀም እና የግብርናን ዘርፍ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ለማስተሳሰርና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግሩን ለማሳካት የደንና ተፈጥሮ ሃብትን በመጠበቅና በዘላቂነት በመጠቀም የግብርናን ምርታማነትና ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ በሥራ ላይ ያለውን ፖሊሲ ተሻሽሎ ወጥቷል።

## 2. የፖሊሲ ማሻሻያ አስፈላጊነት

ነባሩ የገጠር ልማት ፖሊሲ ግብርናና ገጠር ልማት የሚመራበት አምስት  ዋና ዋና እና ተመጋጋቢ የትኩረት አቅጣጫዎችን አስቀምጧል፡፡ እነዚህም የሰው ጉልበትን በሰፊው መጠቀም፣ የመሬትና ተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም፣ የተቀናጀና ከተለያዩ አግሮ-ኢኮሎጂ አካባቢዎች ጋር የተጣጣመ የግብርና ልማት ማካሄድ፣ በገበያ የሚመራ የግብርና ልማት ማካሄድ እና የተቀናጀ የገጠር ልማት ናቸው፡፡ ፖሊሲው የቴክኖሎጂና ግብዓት አቅርቦትና አጠቃቀም ማስፋፋት፣ በገጠር መሠረተ ልማት ላይ መዋዕለ ንዋይ ማስፋፋት፣ በኅብረት ሥራ ማህበራት አማካይነት የአነስተኛ ይዞታ አርሶና አርብቶ አደር ግብርና ገበያ መር እንዲሆን ማስቻል፣ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማጠናከር እንዲሁም ግብርና ነክ ያልሆኑ የገጠር ኢንተርፕራይዞችን ማስፋፋት ላይ ያተኮረ ሲሆን በዋናነት በመንግሥት የተመራና የተቀናጀ የልማት አቅጣጫ ነው፡፡ መንግስት ይህን ፖሊሲ ነድፎ በተገበረባቸው ዓመታት የግብርናው ዘርፍ እያደገና የሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች እድገት እንዲፋጠን በማድረግ ለተደረሰበት አጠቃላይ ኢኮኖሚያዊ እድገት የመሪነት ሚናውን ተጫውቷል፡፡

በነባሩ ፖሊሲ ግልፅ አቅጣጫ ተቀምጦላቸው ነገር ግን የተሟላ የህግ ማዕቀፍ አለመነደፉ እና የአሰራር ስርዓት አለመዘርጋቱ፣ የምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን (መሬት፣ ጉልበትና ካፒታል) አቀናጅቶ ምርታማነት ማሳደግ ላይ በቂ ትኩረት አለመስጠቱ፣ ለአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች ትርጉም ያለው የማበረታቻ ስርዓት አለመዘርጋቱ፣ የመንግስትን ሚና ያጎላ እና የሌሎች የባለደርሻ አካላትና ሚናቸው በግልፅ አለማስቀመጡና ለተሳትፏቸው ውጤታማነት የሚያገዝ የማበረታቻ ስርዓት አለመዘርጋቱ፣ ለእንስሳትና አሳ ሃብት ልማት ተገቢ ትኩረት አለመስጠቱ፣ ለዘላቂ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም፣ ዘርፉን የሚመጥን ፋይናንስ (ብድር፣ ኢንሹራንስ እና አማራጭ ፋይናንስ) አለመቅረብ፣ የተሟላ የማስፈፀሚያ ማእቀፍ አለመዘርጋት እና የማስፈፀም አቅም አለመገንባቱ ዋነኞቹ የፖሊሲው እጥረቶች ነበሩ፡፡

በዚህም የተነሳ ዘርፉ በአብዛኛው አነስተኛ ይዞታ ባለውና ለፍጆታ በሚያመርት፣ ዝቅተኛ ቴክኖሎጂ በሚጠቀም፣ በዝናብ ላይ ጥገኛ በሆነ አርሶና አርብቶ አደር የሚከናወን መሆኑና የደንና ተፈጥሮ ሃብት መመናመንና መጎሳቆልን ያስከተለ ሆኖ እንዲቀጥል አስገድዶታል፡፡ ይህም የግብርና ምርታማነት ዕድገት በሚፈለገው መጠንና

ፍጥነት እንዳይራመድ አድርጎታል፡፡ በተመሳሳይ ዝቅተኛ ምርታማነት ካላቸው የግብርና ምርቶች ወደ ከፍተኛ ምርታማነት ወዳላቸው ምርቶች የመሸጋገር ሂደቱ ዘገምተኛ ሆኗል፡፡ በተጨማሪም የሚመረተው ምርት የራስ ፍጆታን አሟልቶ ለገበያ ሊቀርብ የሚችለው ትርፍ የምርት መጠን አነስተኛ በመሆኑ ግብርና በተሟላ መልኩ ገበያ መር እንዳይሆን ብሎም የዘርፉን መዋቅራዊ ለውጥ (ግብርና ትራንስፎርሜሽን) አዝጋሚ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ የዘርፉ የሰው ሃይል ምርታማነት ዕድገት በሚፈለገው ፍጥነት ባለመጓዙ ካለው አጠቃላይ አምራች የሰው ሃይል በዘርፉ የተሰማራውን ድርሻ በመቀነስ ወደ ሌሎች ዘርፎች በተለይም ወደ ኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚው የተሸጋገረው የሰው ኃይል አነስተኛ ነው፡፡ ከመስኖ አለመስፋፋትና የውሃ አጠቃቀም ሥርዓት አለመዳበር ተዳምሮ ዘርፉ አሁንም ከዝናብ ጥገኝነት ባለመላቀቁ በተደጋጋሚ የሚከሰተው ድርቅ በግብርና የተሰማራውን የህብረተሰብ ክፍል ክፉኛ ከማጥቃት ባሻገር የሀገርን ኢኮኖሚ እየፈተነው ይገኛል፡፡ በሌላ በኩል በግብርና ዘርፍ የግሉ ዘርፍ በአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደር እና አርብቶ አደሮች ተፈላጊ በሆኑ የግብርና ግብዓቶች አቅርቦትና በሰፋፊ የግብርና ልማት ሥራዎች ላይ እንዲሳተፍ ለመሳብና ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ አልተቻለም፡፡

በመሆኑም ዘርፉ ሀገራዊ የምግብ ፍጆታ ማሟላት ባለማስቻሉ የሀገሪቱ አንድ አራተኛ ህዝብ ምግብ የማያገኝበትና ሌሎች ቀላል የማይባል ቁጥር ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በዕለት ደራሽ እርዳታና በልማታዊ ሴፍቲኔት ጥገኛ ሆነዋል፡፡ በተጨማሪም ከዘርፉ የሚገኘው የምርት እድገት በቂ ባለመሆኑ ለውጪ ንግድ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶችን ማሳደግና ተወዳዳሪነት ማረጋገጥ፣ ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃነት የሚውል በቂ ምርት ማቅረብ እንዲሁም ከውጪ የሚገቡ የግብርና ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት ለመተካት አልተቻለም፡፡

በሌላ በኩል ሀገራችን ካላት የሥርዓተ-ምህዳር አወቃቀርና አቀማመጥ ተለያይነት የተነሳ የግብርናውን ዘርፍ ለማሳደግ የሚያስችል ሰፊ የተፈጥሮ ሃብት እና የአየር ንብረት እምቅ አቅም፣ ሰፊ የገበያ እድሎች እንዲሁም የኢኮኖሚ እድገትን ተከትሎ የሚመጣው የግብርና ምርት መጠንና አይነት (አመጋገብ ስርዓት ለውጥ) ፍጆታ መጨመር ምክንያቶች ዘርፉን ይበልጥ ለማሳደግ የሚያስችሉ መልካም አጋጣሚዎች አሉ፡፡

ስለሆነም የዘርፉን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ፣መልካም አጋጣሚዎችን ለመጠቀም እና የግብርናን ዘርፍ ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ለማስተሳሰርና የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግሩን ለማሳካት የደንና የተፈጥሮ ሃብትን በመጠበቅና በዘላቂነት በመጠቀም የግብርናን ምርታማነትና ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ ነባሩን ፖሊሲ ማሻሻል አስፈልጓል፡፡

## 3. የተሻሻለው ፖሊሲ ርዕይ፣ ግቦች፣ ዓላማዎችና መርሆች

### ርዕይ

በ2030 ዓ.ም. ግብርናን በማሻገር በገጠር መዋቅራዊ ለውጥ በማምጣት ለሀገር ብልፅግና ጉልህ ሚና ተጫውቶ ማየት፡፡

### ተልዕኮ

የግብርናን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት ማሳደግ እና የደንና ተፈጥሮ ሃብትን መጠበቅና በዘላቂነት መጠቀምን ማረጋገጥ ብሎም ግብርናን ከሌሎች የገጠር የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ማስተሳሰር ነዉ፡፡

### ዋና ዋና ግቦች

ፖሊሲው የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች ይኖሩታል፡፡ እነርሱም፡-

- ፈጣን፣ አካታችና ዘላቂ የግብርና ዕድገት ማስመዝገብ፣
- የገጠር ነዋሪዎች ገቢ በማሳደግ ከድህነት ማላቀቅ እና የምግብና ስርዓተ ምግብ ዋስትና ማረጋገጥ፣
- ለሀገራዊ የምግብና ስርዓተ ምግብ ዋስትና እና ሉዓላይነት እንዲረጋገጥ ጉልህ አስተዋፆ ማበርከት፣
- የግብርናን የሰው ሃይል ምርታማነት በማሳደግ ከግብርና ዘርፉ የሚወጣውን የሰው ሃይል በግብርና እሴት ጭመራ እንዲሁም ከግብርና ውጪ ባሉ የገጠር የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች እና ለሌሎች ዘርፎች ማሻገር፣

- ለወጪ ንግድ እድገት እና ከውጪ የሚገቡትን ምርቶች በሀገር ውስጥ ምርት መተካትን ማረጋገጥ እንዲሁም ለኢንዱስትሪው ዘርፍ በቂ ጥሬ እቃ ማቅረብ ናቸው::

## ዋና ዋና አላማዎች

የፖሊሲዉ ዋና ዋና አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ፈጣን የግብርና ምርትና ምርታማነት እድገት ማረጋገጥ፣
- የአነስተኛ ይዞታ አርሶና አርብቶ አደር ግብርናን በገበያ ተወዳዳሪነት ማሳደግ፣
- የተፈጥሮ ሃብት ልማትና ጥበቃን በማሻሻል ዘላቂ አጠቃቀምን ማሳደግ
- የደን ልማትና አጠቃቀም በማሳደግ ሀገራዊ የደን ውጤትን ፍላጎት ማሟላት ፣
- በገጠር የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን በማስፋፋት የስራ እድል ፈጠራን ማሳደግ፣
- በከተማና ከተማ ዙሪያ አካባቢዎች በንፅፅር ከፍተኛ ምርትማነትና ዋጋ ያላቸው የግብርና ልማት ማሳደግ፣
- በአየር ንብረትና በሌሎች የተፈጥሮ ክስተቶች ተፅዕኖ የሚመጣ ተጋላጭነትን መቋቋም የሚያስችል አቅም ማሳደግ ናቸው::

## መርሆዎች

ፖሊሲዉን ውጤታማ ለማድረግ በሚከተሉት መርሆዎች መሰረት የሚመራ ይሆናል::

- መንግስት ፖሊሲ መቅረፅ እና አስተዳደራዊና የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት ላይ ትኩረት በማድረግ የግል ዘርፍ፣ የኅብረት ሥራ ማኅበራት እና ሌሎች ተዋንያኖች በዘርፉ መጫወት ያለባቸውን ተገቢ ሚና ከፍ እንዲል ማስቻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣
- የግል ዘርፍ ተሳትፎ ይበልጥ እንዲጠናከርና እንዲሰፋ አስቻይ ሁኔታ መፍጠርና ፍትሃዊ የመወዳደሪያ ሜዳ እንዲኖር በማስፈለጉ፣
- መንግስት በገበያ ውስጥ ጣልቃ የሚገባው ጉድለትን ለመሙላት ወጪ ቆጣቢነት እና የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣
- ከገበያ ስርዓት ጋር በተጣጣመ መልኩ የምግብ ሉዓላዊነት ለማረጋገጥ በትኩረት መስራት በማስፈለጉ፣

- የምግብ ማምረትና አቅርቦት ሂደት ደህንነቱ የተጠበቀ፣ በንጥረ-ነገር ይዘቱ የበለፀገ፣ ትኩስ እና ተመጣጣኝ ዋጋን መሰረት ያደረገ ይሆናል፤ ዘላቂ የተፈጥሮ ሃብት የሚጠብቅና ጤናማ አከባቢ እንዲፈጠር የሚያደርግ እንዲሁም ጠንካራና ጤነኛ የገጠር ህብረተሰብ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣
- ሀገራችን የተቀበለቻቸውን አካባቢያዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶችን እና ግቦችን በተጣጣመ ሁኔታ ማስፈፀም በማስፈለጉ ፣
- ዘመናዊ መረጃ አያያዝ ስርዓቶችን በመዘርጋት የዘርፉን የቁጥጥርና አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን ማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው።

## 4. የፖሊሲው አድማስ

ይህ ፖሊሲ የግብርና ምርቶችን ልማት እና ግብይት፣ የደንና ተፈጥሮ ሃብት ልማት፣ ጥበቃና ዘላቂ አጠቃቀም እንዲሁም የገጠር ልማት ማስተባበርን ይይዛል።

## 5. ማሻሻያ የተደረገባቸው የፖሊሲ ጉዳዮች

የፖሊሲ ማሻሻያው የመሰረታዊ የፖሊሲ አቅጣጫ ለውጦች እና የነባሩን ፖሊሲ አቅጣጫዎች ማስፋትና ማጠናከርን አካቷል። እነዚህን ለውጦች ለመተግበር በዘጠኝ ዋና ዋና እንዲሁም ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ ማሻሻያ ተደርጓል።

መሰረታዊ የፖሊሲ አቅጣጫ ለውጥ የተደረገባቸው የሰው ሃይል ምርታማነት ማሳደግ፣ በካፒታል የተደገፈ የግብርና ልማት ማስፋፋት እና የገጠር መሬት ምርታማነቱን በላቀ ሁኔታ የሚያሳድግ አካል እንዲለማ ማስቻል፤ እነዚህንም የምርት ግብዓቶች በማቀናጀ ምርታማነታቸውን ማሳደግ (total factor productivity) ያካትታል። በተጨማሪም ማሻሻያው የመንግስትና የግሉ ዘርፍ አጋርነት፣ የግልና የመንግስትን ሚና በአግባቡ መለየት፣ ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት እና የግብርና አምራቹን በበለጠ መደገፉ ናቸው። የመሬት ፖሊሲ የግብርና ምርትማነትና ዘላቂነት ለማሳደግ በሚያስችል መልኩ ተፈትሾ ይነደፋል። ከነባሩ ፖሊሲ ግቦች አንዱ የምግብና ስርዓት ምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ሲሆን የዚህ ፖሊሲ ማሻሻያ ግብ ከምግብ ተመፅዋችነት ከመላቀቅ ባሻገር ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት በመተካት የምግብ ሉዓላዊነትን

ማረጋገጥ ነው፡፡ ሌላው የተሻሻለው ፖሊሲ አቅጣጫ ለአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሩ እና አርብቶ አደሩ ትርጉም ያለው ማበረታቻ በመስጠት ለፍጆታ ከማምረት ባለፈ ለገበያ የሚያመርቱ እንዲሆኑ ማስቻል እና አርሶና አርብቶ አደሩን ወደ ባለሃብትነት ማሻጋገር ናቸው፡፡

በነባሩ ፖሊሲ ግልፅ አቅጣጫ ተቀምጦላቸው ነገር ግን የተሟላ የህግ ማዕቀፍ ያልተነደፈላቸው እና የአሰራር ስርዓት ያለተዘርጋላቸው በተለይም የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲና እቅድ፣ ከመንግስት ድርጅቶች በተጨማሪ በምርምርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት እና የግብዓት አቅርቦት የሌሎች ተዋናዮችን ሚናና ተሳትፎ፣ በሰፋፊ የግብርና ልማት የግሉ ዘርፍ ሚናና ተሳትፎ፣ ቴክኖሎጂን በበለጠ ተጠቃሚ የሚሆን እና ገበያ የተመራ ግብርናን እውን ለማድረግ በዚህ ፖሊሲ የተሟላ የህግ ማዕቀፍ ይነደፍላቸዋል እንዲሁም የአሰራር ስርዓት ይዘረጋላቸዋል፡፡ የግብርና ገጠር ልማት ፋይናንስ አቅርቦት ለማሻሻል የሚያስችል የተሟላ የህግ ማዕቀፍ፣ አሰራርና ማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት በዚህ ፖሊሲ ተካቷል፡፡ በተጨማሪም የግብርና እድገት ከገጠር ልማት ጋር የተቆራኘ በመሆኑ ይህንን ለማረጋጋጥ ግብርናን ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር የሚያስተሳስር፣ በገጠር ከግብርና ውጪ ያሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች የሚያስፋፋ፣ የከተማና ገጠር ትስስርን የሚያጠናክር እና የተቀናጀ የገጠር መሠረተ-ልማቶችንና አገልግሎቶችን ማስፋፋትን የሚያስተባብር የአሰራር ስርዓትና የተቋማዊ አደረጃጀት በዚህ ፖሊሲ የሚሰየም ይሆናል፡፡

ይህ ፖሊሲ በስድስት የግብርና ምርት ስርዓቶችና አካባቢዎች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ እነዚህም የባለአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደር ጥምር ግብርና፣ የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደሮች አካባቢ፣ ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ተጋላጭ የሆኑ አካባቢዎች፣ ከተማና ከተማ ዙሪያ ግብርና ፣ የመካከለኛና ሰፋፊ ግብርና እና የተፈጥሮ ደን አካባቢ ናቸው፡፡ የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ግብርና ይህ ፖሊሲ ትኩረት ካደረገባቸው አምት ምርት ስርዓቶች ውስጥ አንዱና ዋነኛ ከመሆኑ በተጨማሪ የአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ልዩ ትኩረት በመስጠት በተሻሻሉት ዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮች ውስጥ ተካቶ የአካባቢዎቹን ልዩ ባህሪያት በአግባቡ እንዲመለስ ለማስቻል አንዱ የዘርፍ ብዙ የፖሊሲ አቅጣጫ ሆኖ ተቀምጧል፡፡

በዚህ ፖሊሲ ማሻሻያ የተደረገባቸው ዘጠኝ ዋና ዋና እና ዘርፍ ብዙ የፖሊሲ ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው።

## 5.1 የመሬት፣ ደንና ተፈጥሮ ሃብት አስተዳደርና አጠቃቀም

መሬት፣ ደንና የተፈጥሮ ሃብት በአግባቡ መጠበቅ፣ መጠቀምና ማስተዳደር ብሎም ከሰው ኃይልና ካፒታል ጋር ማጣመር ዘላቂ የግብርና እድገት ለማሳካት ወሳኝ ነው። ስለሆነም ይህንን አላማ ለማሳካት የመሬት፣ ደን እና የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምና አስተዳደር ፖሊሲ እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

### 5.1.1 የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም

የመሬት ስሪት እና ስርዓት የግብርና ምርትማነት እና ዘላቂነት ለማሳደግ በሚያስችል መልኩ እንደሀገር ተፈትሾ የሚሻሻል ሲሆን የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ፖሊሲ የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀምን እንዲያረጋግጥ፣ የገጠር መሬት አስተዳደርንና አጠቃቀምን እንዲያሻሽል፣ የተበጣጠሱ የእርሻ መሬት ይዞታዎችን በፈቃደኝነት ኩታገጠም ማድረግና ማዋሃድ እንዲያስችል እንዲሁም የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ተቋማዊ አደረጃጀት ዘላቂና የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም በሚያሰፍን መልኩ ተሻሽሏል።

#### 5.1.1.1 የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም

የመሬት አጠቃቀምን በተቀናጀ መልኩ አቅዶ መጠቀም መሬት ለልማት የላቀ አስተዋፆ ማበርከት በሚችልበት ሁኔታ ጥቅም ላይ ለማዋል ያስችላል። ይህም ግብርና በመሬቱ የመልማት አቅም እየተለየ እንዲለማ በማስቻል ዘላቂ የግብርና ልማት ለማከናውን ይረዳል። የነባሩ ፖሊሲ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲና ዕቅድ ማውጣት አስፈላጊ መሆኑንና ይህም አግሮ-ኢኮሎጂን መሰረት አድርጎ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚያስፈልግ የፖሊሲ አቅጣጫ አስቀምጧል። ሆኖም በጥቅል የተቀመጠውን አቅጣጫ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አስገዳጅ የሆነ የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲና ዕቅድ አልወጣም። በመሆኑም የተለያዩ ዘርፎች ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ የልማት እቅዶችንና ፕሮግራሞችን ከሌሎች የመሬት አጠቃቀም ተግባራት ጋር ማቀናጀት አልተቻለም። በሌላ በኩል በአርብቶና ከፊል አርብቶ አደር

አካባቢዎች ያለው መሬት በጎሣ/በባህላዊ አሰራር ላይ የተመሠረተ የወል የመሬት ይዞታ ስሪት ስለሆነ ለዚህ ስሪት እውቅና መስጠትና አሰራር መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የመሬት አጠቃቀም በጥናትና በዕቅድ ላይ እንዲመሰረትና መሬትን እንደ መልማት አቅሙ ለተገቢው አገልግሎት ለማዋል፣ የገጠርና የከተማ የመሬት አጠቃቀምን ተመጋጋቢ ለማድረግ፣ ዘላቂ ያልሆነ የመሬት አጠቃቀምን ለማስወገድ፣ በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች በመሬት አጠቃቀም ምክንያት የሚፈጠሩ የመሬት ሽሚያ እና ግጭት ለመቀነስ የተቀናጀ መሬት አጠቃቀም እንዲሰፍን ይደረጋል፡፡

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የተቀናጀ መሬት አጠቃቀም ፖሊሲ ይነደፋል፣ ዕቅድ ይዘጋጃል፤ የህግ ማዕቀፍ ይወጣል እና የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

### 5.1.1.2 የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም

የገጠር መሬትን በአግባቡ ማስተዳደርና መጠቀም የአርሶና አርብቶ አደር የይዞታ ዋስትና ለማስከበርና ለማጠናከር የግብርና ቴክኖሎጂና ግብዓት አጠቃቀም በማሳደግ እንዲሁም የመሬት አጠቃቀምን በማበረታታት ዘላቂ የግብርና እድገት እውን ለማድረግ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ የመሬት ይዞታ ዋስትናን ለማስከበር የገጠር መሬት ምዝገባና ቅየሳ ስርዓት በመዘርጋት ሰፊ ስራ በመሰራቱ የይዞታ ዋስትናን በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ በተለይም ሴቶች በህገ-መንግስቱ የተሰጣቸውን ከወንዶች እኩል በመሬት የመጠቀም መብት የማረጋገጥ አስተዋጽዖውም ከፍተኛ ነው፡፡

በሌላ በኩል በስራ ላይ ያለው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ የምዝገባና ቅየሳ ስራዎችን ሊያግዙ የሚችሉ ዝርዝር ድንጋጌዎች አለመያዙ፣ ባለይዞታው በግሉ በመሬቱ ላይ ያለማውን መሸጥ አለማስቻሉ፣ በይዞታ የመጠቀም መብትን ለብድር ማስያዣነት አለመፍቀድ፣ የይዞታ መብትን ለፈለጉት ሰው በስጦታ፣ በውርስና በኪራይ በህገ-መንግስቱ በተፈቀደው መሰረት ማስተላለፍ አለማስቻሉ፣ ባህላዊ የመሬት አስተዳደርን ግምት ውስጥ ያላስገባ መሆኑ፣ የመሬት ኪራይና ማስጠመድ የአሰራር ስርዓት አለመዘርጋቱ ዋናዎቹ ክፍተቶቹ ናቸው፡፡ በተጨማሪም የአርሶና አርብቶ አደር

የመሬት ይዞታዎች ወደ ከተማ ክልል ሲካተቱ የይዞታዎች ዋስትና ለማስቀጠል የሚያስችል የህግ ማእቀፍና የአሰራር ስርዓት ባለመኖሩ በአነስተኛ ካሳ ባለይዞታዎቹን ማፈናቀል በስፋት ይስተዋላል፡፡

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የገጠር መሬት ይዞታን የመጠቀም መብትን ለብድር ማስያዥነት ማዋል፣ የይዞታ መብትን ለፈለጉት ሰው በስጦታ፣ በውርስና በኪራይ ማስተላለፍ እና ባለይዞታው በግሉ በመሬቱ ላይ ያለማውን መሸጥ ይፈቀዳል፣ የመሬት ሊዝ፣ ኪራይና ማስጠመድ የተቀላጠፈ እንዲሆን ይደርጋል፣
- የመሬት ይዞታ የካሳ አከፋፈል የይዞታውን የመልማት አቅም ከግምት የሚያስግባ፣ አማራጭ የካሳ አይነቶችን መሰረት ያደረገ ይህም በተመሰከረለት ገማች እንዲፈፀም ይደረጋል፣
- የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም የህግ ማዕቀፍ የወል መሬት አስተዳደር እና ከአንድ በላይ ጋብቻ ጉዳዮችን እንዲያስተናግድ ይደረጋል፣
- የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም የይዞታ ምዝገባና ቅየሳ ስራዎችን ወጥ ለማድረግ የምዝገባና ቅየሳ መሳሪያዎች አይነት እና ስልቶች በግልፅ ይደነገጋል፣
- በከተማ ዳርቻ የአርሶና አርብቶ አደር ይዞታ ወደ ከተማ ሲካለል የመሬት ይዞታ እንዲጠበቅ ይደረጋል፡፡

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሩን እና አርብቶ አደሩን ዘላቂ የመሬት የመጠቀም መብት የሚያረጋግጥ፣ መሬት በላቀ መልኩ ምርትማነቱን በሚያሳድግ አካል መልማቱን የሚያረጋግጥ እንዲሁም የመሬት የመጠቀም መብት ወደ ሌላ ሶስተኛ ወገን የሚዘዋወረው በጊዜ በተገደበ ሆኖ የሚከተሉት የማስፈፀሚያ ስልቶች ይነደፋሉ፡፡

- የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም የህግ ማዕቀፍ ይሻሻላል፣ የአሰራር ስርዓትና መስረት ልማት ይጠናከራል፣
- የገጠር መሬት ዋጋ ትመና አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- በከተማ ዳርቻ የአርሶና አርብቶ አደር ይዞታ ወደ ከተማ ሲካለል የባለይዞታዎችን መብት እንዲያስጠብቅ ተደርጎ የከተማ መሬት ይዞታ መብት ምዝገባ የህግ ማዕቀፍ ይሻሻላል፣ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

### 5.1.1.3 አነስተኛ የእርሻ መሬት ይዞታን ማሰባሰብና ማዋሃድ

በሀገራችን አነስተኛ ይዞታ ባላቸው አርሶ አደሮች የሚካሄደው እርሻ 95.8 በመቶ የሚሆነውን የለማ የእርሻ መሬት እና 96.2 በመቶ የሚሆነውን የሰብል ምርት የሚሸፍን ሲሆን የእርሻ መሬቶቹም በአብዛኛው አነስተኛ ስፋት ያላቸው፣ የተበጣጠጠሱና የተበታተኑ ናቸው። እነዚህ ይዞታዎችን በማሰባሰብና በማዋሃድ መካከለኛና ሰፋፊ እርሻዎች እንዲፈጠሩ በማገዝ የግብርና ቴክኖሎጂና ግብዓት አጠቃቀማቸውን በማሳደግ ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር፣ የምርት ጥራትን ለማሻሻል እንዲሁም የተፈጥሮ ሃብትን በአግባቡ ለመጠቀም እንደሚቻል ታይቷል። በተጨማሪም የተሰባሰበ ይዞታ ከባለሀብት ጋር የወል እርሻ ልማትን ሳቢና አዋጪ ያደርጋል እንዲሁም የቴክኖሎጂና የግብዓት ፍላጎትም ማደግን ተከትሎ ለተደራጁ ወጣቾችን አገልግሎቱን በማቅርብ ሰፊ የስራ አድል ይፈጥራል።

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የተበጣጠጠሱና የተበታተኑ የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች በፈቃዳቸው በጋራ ባለቤትነት፣ በመከራየት ወይም በመለወጥ ማሳዎቻቸውን አሰባስበው እንዲያርሱ፣ ምርት እንዲያሰባስቡ፣ እሴት እንዲጨምሩና እንዲገበያዩ በሂደት እውቀትና ሃብት ካላቸው ጋር አዋህደው መካከለኛና ሰፋፊ እርሻዎች እንዲፈጠሩ ይደረጋል።

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- አነስተኛ የእርሻ መሬት ይዞታዎችን ማሰባሰብና ማዋሃድ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍና አሰራር ስርዓት ይዘረጋል።

### 5.1.1.4 የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ተቋማዊ አደረጃጀት

መሬት በተደራጀና የዘርፉን መስተጋብሮች (መሬት አጠቃቀም፣ መሬት መብትና ግዴታ፣ መሬት ልውውጥና ግብይት) በተረዳ ሁኔታ ተቋማዊ በሆነ መልኩ አቀናጅቶ ማስተዳደርና መምራት ከመሬት የሚጠበቀውን የኢኮኖሚ፣ የመልካም አስተዳደር፣ የማህበራዊ ፍትህ እና የግጭትን በማስወገድ የመሬትን በዘላቂነት መጠቀም ያስችላል። መሬት የከተማና የገጠር ተብሎ በመከፈሉ ምክንያት በሁለት የተለያዩ ተቋማዊ አደረጃጀት እንዲተዳደር በመደረጉ በአሁኑ ወቅት መሬትና መሬት ነክ የሆኑ ሥራዎች

ከዘጠኝ በላይ በሆኑ ተቋማት ተበታትነው ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም መሬትን እንደግልና የጋራ ይዞታነቱ መብት ለማወቅና ለመጠበቅ፣ የመሬቱን ልኬት በትክክል ለማወቅ፣ ዋጋውን ለመመዘንና ለመወሰን፣ ሀብቱን ከብክነት ለመታደግ፣ አጠቃቀሙን ለመወሰንና ለመከታተል የሚያስችል ጠንካራ ተቋማዊ አደረጃጀት አልተዘረጋም፡፡ በዚህ ምክንያት መሬት ለምርትና የኑሮ መሰረት ከመሆን ይልቅ በተቃራኒው የግጭት እና የሙስና መስፋፋት መንስኤ ከመሆኑም በላይ በመንግስትና በመሬት ተጠቃሚው ህዝብ መካከል የጥርጣሬ ምንጭ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በተለይም በከተሞች ዙሪያ የአጠቃቀም ልውውጡን ኢ-መደበኛ በማድረግ የእርሻ መሬት ሽሚያ አስከትሏል፡፡

### የፖሊሲ አቅጣጫው

- የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደርን በተሻለ ለመምራት ተበታትነው የሚገኙ የመሬት አደረጃጀቶችን ወደ አንድ በማምጣት በገለልተኛ እና ጠንካራ ተቋማዊ አደረጃጀት ይዋቀራል፡፡

### የማስፈፀሚያ ስልቶች

- የተበታተነ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አደረጃጀትን በገለልተኛ (መሬት በቀጥታ ተጠቃሚ ያልሆነ) ተቋም እንዲመራ ለማድረግ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ ተቋማዊ አደረጃጀት እና መሰረተ ልማት ይዘረጋል፡፡

## 5.1.2 የደን ሀብት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም

የሀገራችን ደን ሽፋን 17 በመቶ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ይህም ሃብት በ2013 በጀት ዓመት ለሀገራዊ ኢኮኖሚ 2.8 በመቶ ለግብርና ኢኮኖሚ ደግሞ 8.6 በመቶ አስተዋፆ ማድረጉ ሪፖርት ቢደረግም የደን ሃብቱ ለአጠቃላይ ኢኮኖሚ ያለው አስተዋፆ እስከ 12.8 በመቶ እንደሚደርስ በጥናት ተረጋግጧል፡፡ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀምን በተገቢው መንገድ በማከናውን የተለያዩ የደን ውጤቶችን ለሀገር ውስጥ ገበያና ለወጪ ንግድ በማቅረብ የውጪ ምንዛሬ ገቢ ምንጭና የሥራ ዕድል በመፍጠር እንዲሁም ፈጣን የሕዝብ ቁጥር ዕድገትንና የከተሞች መስፋፋትን ተከትሎ እያደገ የመጣዉን የማገዶና የግንባታ ፍላጎትን ለመሙላት ያስችላል፡፡ የጥምር ደን እርሻ ልማት የግብርና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የአርሶና አርብቶ አደሩን ገቢና የኑሮ ደረጃ በዘላቂነት ለማሻሻል ያስችላል፡፡ እንዲሁም ሌሎች የሥነ-ምሕዳር አገልግሎቶችን በማሻሻል የአፈር መሸርሸርን በመቀነስ የኃይል ማመንጫና

የመስኖ ግድቦች በደለል እንዳይሞሉ በማድረግ ለኃይል አቅርቦት እና ለግብርና ምርት እድገት አስተዋፆው በማድረግ አንረጓዴ ኢኮኖሚውን ግንባታ ያሳካል።

ይህንን በመገንዘብ መንግሥት የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ፖሊሲና ስትራቴጂ ማዕቀፎች ቀርፆ በመተግበር ላይ ይገኛል። ባለፉት ሦስት ዓመታት የተተገበረው የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ መርሃ-ግብር አንዱ የፖሊሲው ትግበራ ማሳያ ነው። ሆኖም የደን ልማቱ የደንና የደን መሬት ባለቤትነት መብትን በሚያረጋግጥ እንዲሁም የኅብረተሰቡንና የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ውጤታማነትን ለማጎልበት በሚያስችል መልኩ በተሟላ የፖሊሲ ማዕቀፍና የአሠራር ሥርዓት አልተመራም። በተለይም በግል የደን ልማት ለመሰማራት የሚፈልጉ ባለሀብቶች የመሬትና ፋይናንስ (ብድርና ኢንሹራንስ) አቅርቦት አለመኖር እንዲሁም የደን ልማት ለትርፋማነት ረጅም ጊዜ የሚወስድ እና የመሬት ህጉ ይህንን የማያበረታታ በመሆኑ የግል ዘርፍ ተሳትፎ በጣም ዝቅትኛ እንዲሆን አድርጎታል። ደን ለማልማት፣ ለማስተዳደር፣ እንዲሁም የደን ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋት በበጀት፣ በሰው ኃይልና በሎጂስቲክ ግብዓት በበቂ ሁኔታ አልተደገፈም። የመሬት አጠቃቀም ፖሊስና ዕቅድ አለመኖር ደንና የደን መሬትን ለመለየት፣ ለማስከበርና በዘላቂነት ለማልማትን የበለጠ አስቸጋሪ አድርጎታል። ይህም የደን መጨፍጨፍና መመናመን በማስከተሉ እና የምርት ሰጪ ደኖች ባለመስፋፋታቸው እያደገ የመጣውን የደን ዉጤቶች ፍላጎት ለሟሟላት ባለመቻሉ በዓመት ከ350 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ወጭ በማድረግ የደን ውጤቶችን ወደ ሀገር ዉስጥ ማስገባት አስገድዷል።

**የፖሊሲ አቅጣጫ**

- ደንና የደን ልማትን በተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲና ዕቅድ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ይደረጋል፣
- የተፈጥሮ ደኖችን ለማልማት፣ ለመጠበቅና በዘላቂነት ለመጠቀም የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የደን እሳትን አስቀድሞ ለመተንበይ፣ ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል በቴክኖሎጂ የተደገፈ የአሰራር ስርዓትና መሰረተ ልማት ይዘረጋል፣
- የግልና ማኅበረሰብ ደንና የደን መሬት የመጠቀም መብት እንዲረጋገጥ ይደረጋል፣

- አነስተኛና ሰፋፊ ምርት ሰጪ ደን ለማልማትና እሴት ለመጨመር እና ከውጪ የሚገቡ የደን ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት የሚያስፈልጉ የመሬትና የፋይናንስ አቅርቦትና ሌሎች አስቻይ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ይደረጋል፣
- በመንግስትና በግል ባለሃብቱ አጋርነት እና በመንግስት ደን እንዲለማ፣ እንዲጠበቅ እና ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፣
- የደን ልማትና አጠባበቅ የስርዓተ ምህዳር አገልግሎቶችን በማሳደግ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታን ለማረጋገጥ እና ሀገራችን የተቀበለቻቸውን ቀጠናዊ፣ አህጉራዊና ዓለምአቀፍዊ ስምምነቶችና ግቦች እንዲሳኩ በትኩረት ይሰራል፣

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የደን ልማት፣ አጠባበቅና አጠቃቀም የፖሊሲ ማዕቀፍ፣ የአሰራር ስርዓት እና ተቋማዊ አደረጃጀት ይሻሻል፣
- የደን እና የደን መሬት የመለየትና የመጠቀም መብት አሰራር ስርዓት ይሻሻላል፣
- ከውጪ የሚገቡ የደን ውጤቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት በተመረጡ የምርቶች እሴት ሰንሰለት ስትራቴጂ ይነደፋል፣ የድጋፍና የማበረታቻ ስርዓት ይዘረጋል፣ የልማት ፕሮግራሞች ይነደፋሉ፣ መዋቅራዊ አደረጃጀት ይገነባል፣
- ለደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የመንግስትና ለግል ባለሃብቱ አጋርነት የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል
- የደን ሃብት አጠቃቀም አገልግሎት ክፍያ (Payment for Ecosystem Services) እና ማህበረሰቡ ጠብቆ ላቆየዉ የብዝሀ ሕይወት ሀብትና እዉቀት የሚኖረዉ የጥቅም ተጋሪነት የሚያረጋግጥ የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣

### 5.1.3 የተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም

የተፈጥሮ ሀብት በአንድ መልክዓ-ምድር የሚገኝን የአፈር፣ የውሀ፣ የእጽዋት እና እንስሳትን መስተጋብርንና ጥምርታን የያዘ ነው። የተፈጥሮ ሃብት ልማትና አጠቃቀሙም ዘለቄታዊነት መርህ ላይ ከተመሰረተ ለሀገራዊ ኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ ነው። ስለሆነም ይህን ሀብት በአግባቡ በመለየት፣ በመተንተን እና በመረጃ ቋት በማደራጀት የተሰናሰለ የልማት እቅድን አዘጋጅቶ መተግበር አስፈላጊ ነው። ይህም

የእጽዋት ሽፋንንና ስብጥርን ለማሻሻል፣ የመሬት መራቆትን እና የአፈር መሸርሸር በመቀነስ፣ የአፈር ጤንነትና ለምነት በመጠበቅና በማሻሻል የግብርና ግብአቶች ውጤታማነትን በማረጋገጥ እንዲሁም የገፀ እና ከርሰ-ምድር ውሃን በማበልፀግ ለዘላቂ የግብርና ልማት መሰረት ይጥላል። በአጠቃላይ የተፈጥሮ ሃብት ልማትና ጥበቃ ጤናማ አካባቢን በመፍጠር፣ ዘላቂ የግብርና ልማት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፣ የምግብና ስነ-ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል።

የተፈጥሮ ሃብት ልማትና አጠቃቀም የአፈርን ልዩ ባህሪያት (የተፈጥሮ ቁሳአካልና ንጥረ ነገር ይዘት፣ አሲዳማነተና ጨዋማነት እና የውሀ አዘልነትን) ከግምት ውስጥ ያላስገባና በሂደት እየተከላ የመጣውን የአፈር ለምነትና ጤንነት ችግር ለመፍታት የሚያስችል መደላድል ሳይፈጥር ቆይቷል። በተለይም በአሲዳማነት የተጠቃ መሬት ላይ ጥቅም ላይ የሚውለው ማዳበሪያና ምርጥ ዘር ውጤታማነት በእጅጉ እንዲቀንስ አድርጎታል። በተጨማሪም የጥምር እርሻ ደን ዘዬ ለምግብ ዋስትናና ገቢ ማስገኛ ቀጥተኛ ጥቅሞች ባለፈ የአካባቢ ተፈጥሮዊ ሚዛንን የጠበቀ ግብርና ልማት ለማጎልበት የሚያስችል የተሟላ የፖሊሲ ማዕቀፍና ተቋማዊ አደረጃጀት አልተመራም።

### የፖሊሲ አቅጣጫው

- የተፈጥሮ ሃብት አያያዝና አጠቃቀም የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀቅም እቅድን መሰረት ያደረገ፣ ተፋሰስን ያማከለ፣ የውሃ፣ ዕፅዋትና አፈር (የተፈጥሮ ቁሳአካልና ንጥረ ነገር ይዘት፣ አሲዳማነተና ጨዋማነት እና የውሀ አዘልነትን) ባህሪያትና ሀብት የለየና ታሳቢ እንዲያደርግ ይደረጋል፣
- የተፈጥሮ ሃብት አያያዝና አጠቃቀም የሰው ጉልበት በማቀናጀት ሜካናይዝድ እንዲሆን ይደረጋል፣
- የተፈጥሮ ሃብት ልማት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል አካታች እና አሳታፊ፣ በጋር ባለቤትነትና በተጠያቂነት የሚጠቀሙበትና የሚያስተዳደሩበት፣ ልማቱንም ለገቢ ማስገኛ እና ለኑሮ ዋስትና እንዲውል ይደረጋል።

### የማስፈፀሚያ ስልቶች

- የተፈጥሮ ሀብቱን በመረጃ ቋት ለማደራጀትና ሃብቱን ለማልማት የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ይወጣል፣ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣

- ሀብቱን ለማስተዳደርና በአግባቡ ለመጠቅም የህግ ማዕቀፍና የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል በተለይም ማህበረሰብን የሚያበረታታ የአካባቢ ተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም አገልግሎት ክፍያ (Payment for Ecosystem Services) እና ማህበረሰቡ ጠብቆ ላቆየዉ የብዝሀ ሕይወት ሀብትና እዉቀት የሚኖረዉ የጥቅም ተጋሪነት የሚያረጋግጥ የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የተቀናጀ የአፈር ለምነት እና ጤናማነት ስትራቴጂ ይሻሻላል፣ የህግ ማዕቀፍ ይወጣል፣ አስራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የጥምር እርሻ ደን ዘዴ ስትራቴጂ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የግጦሽ መሬት ልማትን ከእንስሳት እርባታ እና ከተፈጥሮ ሃብት ልማት ጋር በተቀናጀ ሁኔታ ለመምራት የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ አስራር ስርዓት እና ተቋማዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣
- የተፈጥሮ ሃብት ልማት ተጠቃሚዎች ባለቤትነትና በተጠያቂነት የሚጠቁሙበትና የሚያስተዳደሩበት፣ ልማቱንም ለገቢ ማስገኛ እና ለኑሮ ዋስትና እንዲውል የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል።

## 5.2 የቴክኖሎጂ፣ ግብዓት እና አገልግሎት አቅርቦት ስርዓት

የግብርናን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት ለማሳዳግ ውጤታማና ቀጣይነት ያለው የቴክኖሎጂ ማፍለቅና ማባዛት፣ ጥራቱና ወቅታዊነቱ የተጠበቀ ግብዓትና አገልግሎት አቅርቦትና አጠቃቀም አስፈላጊ ነው። በመሆኑም የምርምርና ቴክኖሎጂ፣ የኤክስቴንሽንና ምክር አገልግሎት፣ የሰብል ምርት ግብዓቶች፣ የእንስሳትና አሳ ሀብት ልማት ግብዓቶች፣ የሰብል ጤና ጥበቃ፣ እንስሳት ጤናና ደህንነት እና የሜካናይዜሽን አገልግሎት እንዲሁም የግብአት አጠቃቀም የማበረታቻ ስርዓት እና የግብዓት ፍላጎት፣ ምርትና አቅርቦት መከታተያ ስርዓት መዘርጋት በዚህ ፖሊሲ ተሻሽለዋል።

### 5.2.1 የምርምር እና ቴክኖሎጂ

ጠንካራ የምርምርና ቴክኖሎጂ ስርዓት የብዙ ተዋንያን ተሳትፎ የሚያረጋግጥ፣ የቴክኖሎጂ ማፍለቅ፣ መልቀቅና መመዝገብ ስርዓት የሚዘረጋ እና የቴክኖሎጂ አፍላቂዎች የባለቤትነትና ተጠቃሚነት ዋስትና የሚሰጥ በሆነ መልኩ መዘርጋት

ይኖርበታል። መንግስት ምርምሩን የሚደግፍ የፖሊሲ ማዕቀፍ የተሟላና አግሮ ኢኮሎጂ ዞኖችን ያገናዘበ የምርምርና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ስርዓት መዘርጋት አቅጣጫ አስቀምጧል። የፖሊሲው ትኩረት የነበረው በአንድ በኩል ሀገራዊ የምርምር አቅምን በከፍተኛ ደረጃ ማጎልበት በሌላ በኩል ተወዳዳሪ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ከውጭ በማስገባት በማላመድና በማበልፀግ ለተጠቃሚዎች በማድረስ ፈጣን የግብርና ዕድገት ማረጋገጥ ያለመ ነበር። ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ ከፌደራል የምርምር ተቋም በተጨማሪ የክልል ግብርና ምርምር ተቋማት እና የግብርና የትምህርት መስክ በሚሰጡ ዩኒቨርሲቲዎች በምርምር ተግባራት ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ።

ነባሩ ፖሊሲ ቴክሎጂዎችን ከውጪ ማስገባትን ተግባራዊ ለማድረግ በቂ የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት፣ የቴክኖሎጂ ባለቤትና ተጠቃሚነት የሚያረገግጥ ሥርዓት ባለመዘርጋቱ እና ለሁሉም አይነት ቴክኖሎጂዎች ክፍተቶች ውጫዊ (ከሌሎች ሀገሮች) መፍትሄዎች በበቂ ሁኔታ ባለመገኘቱ የሚፈለገውን ውጤት አላስገኘም። በተጨማሪም ፖሊሲው አገራዊ የምርምር ስርዓቱ አካላት ተቋማዊ አደረጃጀታቸውን ጠብቀው በየግላቸው የምርምር ስትራቴጂ ነድፈውና ሃብት አሰባስበው እንዲሰሩ የሚፈቅድ ቢሆንም ውጤታማና ተጠያቂነት ያለው ትስስር ለመፍጠር የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ አልነበረም።

የግብርና ቴክኖሎጂ የማፍለቅ ስራ በዋናነት በመንግስት እንደሚሰራ በስራ ላይ ያለው ፖሊሲ አቅጣጫ በማስቀመጡ የግል ባለሀብቱ ተሳትፎ ተገድቦ ቆይቷል። የመንግስት የምርምር ተቋማትም ቴክኖሎጂ ማፍለቅ ላይ መስራት እንደሚችሉ ቢመላከትም በዋናነት በውጪ የፈለቁ ቴክኖሎጂዎችን በአገር ውስጥ የማላመድ ስራ ላይ እንዲያተኩር በመደረጉ የምርምር አቅማቸው በሰው ኃይል፣ በመሰረተ ልማት እና አጠቃላይ የአቅም ግንባታ ስራ ላይ የተሰራው ስራ ውስንነት ነበረበት። በመሆኑም በግል እና በመንግስት የሚፈልቁ ቴክኖሎጂዎች ብቃት የሚፈተሸበትና የሚረጋገጥበት፣ ተወዳዳሪ ቴክኖሎጂ የሚፈልቅበት ስርዓት አለመኖሩ የግብርና ቴክኖሎጂ የሚለቀቅበት እና የሚመዘገብበት ምቹ ሁኔታ እንዳይኖር አድረጎታል። በተጨማሪም የንግድ ፈቃድ እና ምዝገባ ስርዓቱ የግብርና ቴክኖሎጂ ማፍለቅ ስራን እንደ አንድ የግል ባለሃብት መሳተፍ የሚችልበት ዘርፍ ተደርጎ አልተካተተም።

የቴክኖሎጂ ማፍለቅ፣ መልቀቅና መመዝገብ ስርዓት ትኩረት የነበረው የምርምር ስርዓቱ የተከተለ በመሆኑ የተወሰኑ ሰብሎች ዝርያ ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ በሌላ መልኩ የግብርና ቴክኖሎጆዎች የሮያሊቲ ክፍያ የተሟላ የህግ ማዕቀፍና አሰራር ስርዓት አልተዘረጋም፡፡ የፈጠራ፣ የአነስተኛ ፈጠራና ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የህግ ማዕቀፍ በዕጽዋትና በእንስሳት ላይ የሚደረጉ የምርምርና ፈጠራ ውጤቶችን ጥበቃ የሚሰጥ ድንጋጌዎች ባለማካተቱ በግብርና ምርምር የሚወጡ ቴክኖሎጂዎችን በባለቤትነት ለማስመዝገብም አልተቻለም፡፡

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የግብርና ምርምር ስርዓቱ አግሮኢኮሎጂ ዞኖች አዳጊ ቴክኖሎጂ ፍላጎትን የሚያሟላ እና የሚፈልቁ ቴክኖሎጂዎች የበለጠ ችግር ፈቺና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የቴክኖሎጂ ማፍለቅ ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ፣ ሁሉን ተዋንያን ማሳተፍና ማስተሳሰር፣ የመንግስት ምርምርን አቅም የሚያጎለብትና ውጤታማ እንዲሆን፣ የሁሉንም የግብርና ቴክኖሎጂዎችና አሰራር ስርዓት ያካተተ ምርምር እና የግል ዘርፍን ተሳትፎ እንዲያድግ ይደረጋል፣
- የግብርና ቴክኖሎጂ ማፍለቅ፣ መልቀቅ እና መመዝገብ ሁሉንም ተዋንያን አሳታፊ፣ የሁሉንም የግብርና ቴክኖሎጆዎች እና የአሠራር፣ የአመራረት ወይም የምርምር ስልቶች መመዝገብ፣ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎና ኢንቨስትመንት አበረታች እና የሚፈልቁ ቴክኖሎጂዎች በብዛትና በአይነት እንዲጨምሩና ይበልጥ ችግር ፈቺና ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ይደረጋል፣ አሰራሩም በገለልተኛ ተቋም ይመራል፣
- ሁሉን ተዋንያን ምርምሮችና ፈጠራዎች ይደገፋሉ፣ የሚወጡ ቴክኖሎጂዎች የባለቤትነት ጥበቃ የሚደረግላቸው ይሆናል፣ የግብርና ቴክኖሎጂ አፍላቂዎች የሮያሊቲ ክፍያ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- ሀገራዊ የብዙ ተዋንያን ምርምር ስታራቴጂ ይነደፋል፣
- የምርምር ተቋማት ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት ማሻሻያ ይደረጋል፣
- የምርምር ውጤቶች ለተጠቃሚው የሚደርሱበት (research commercialization) በተለይም የመንግስት ምርምር ስርዓት ማሻሻያ (ምርምር በክፊል ለትርፍ የሚሰራበት አሰራርን ጨምሮ) አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣

- የግል ምርምር ተዋንያን ምዝገባ፣ ፍቃድ እና ቁጥጥር የሚወስን የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል እንዲሁም የግል ምርምር ተሳትፎን ለማሳደግ የመንግስት እና የግል አጋርነት የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የግብርና ቴክኖሎጂ ማፍለቅ፣መልቀቅ እና መመዝገብ ሁሉንም ተዋንያን እና ቴክኖሎጂዎች ባካተተ መልኩ የሚያስተናግድ የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓት እና ተቋማዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣
- የተለቀቀ ወይም የተመዘገበ ቴክኖሎጂዎች ውጤታማነቱ ሲቀንስ ወይም ሲለቀቅ የነበረውን ባሕርይ እንደለወጠ ሲታመን ከምዝገባ ስርዓቱ የሚሰረዝበትና ጥቅም ላይ እንዳይውሉ የሚያስገድድ የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የፈጠራ፣ አነስተኛ ፈጠራና ኢንዱስትሪያዊ ንድፍ የህግ ማዕቀፍ ግብርናን ትኩረት ባደረገና ባለመብቶችን በሚያበረታታ መልኩ ይሻሻላል፣
- የባለቤትነት መብት ምዝገባና ጥበቃ ለሚያስፈልጋቸው የግብርና ቴክኖሎጂዎች የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የሮያሊቲ ክፍያ ስርዓትን ይዘረጋል፣ የተቋማት አደረጃጀት ይጠናከራል።

### 5.2.2 የኤክስቴንሽን እና ምክር አገልግሎት

የኤክስቴንሽን እና ምክር አገልግሎት የተለያዩ ተጠቃሚዎችን የእውቀት፣ ክህሎት፣ የአመለካከትና የባህሪ ለውጥ ለማምጣት የተለያዩ የኤክስቴንሽን ዘዴዎችና ሥልቶችን በመጠቀም የማስተማር፣ የማማከር፣ የማደራጀትና የማስተባበር አገልግሎቶችን መስጠት ነው። ይህንን አገልግሎት ገበያ ተኮር፣ ምሉዕ፣ ተደራሽ፣ ዘላቂ፣ አሳታፊ እና ፍላጐት ላይ መሠረት ያደረገ የግብርና ልማትን በማሳካት የተጠቃሚውን ህይወት ማሻሻልና ለሀገር ኢኮኖሚ አስተዋጽኦ የሚያደረግ ቁልፍ መሣሪያ ነው።

ይህንንም በመገንዘብ መንግስት ላለፉት ዓመታት በአገር አቀፍ ደረጃ 14,065 የሚሆኑ የአርሶና አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት፣ 20 የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጆች፣ ከ69,625 (17,096 ሴቶች) በላይ የግብርና ባለሙያዎች በሁሉም የገጠር ቀበሌዎች በማሰማራት የኤክስቴንሽን አገልግሎት እያቀረበ ይገኛል። ይህ አገልግሎት ለአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችንና ግብዓቶችን በማስተዋወቅና ተጠቃሚ በማድረግ ጉልህ ሚና

ተጫውቷል። አገልግሎቱ በመንግሥት የሚቀርብ ሆኖ ትኩረቱም በግብርና ግብዓት እና ቴክኖሎጂ አቅርቦት፣ በቀበሌ ግብርና ባለሙያዎች፣ በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማእከላት አገልግሎት፣ በግብርና ቴክኒክ፣ ሙያ እና ትምህርት ሥልጠና ኮሌጆች ላይ ብቻ ነበር።

ከጥቂት ዓመታት በፊት የግብርና ኤክስቴንሽን ስትራቴጂ የፀደቀ ሲሆን ስትራቴጂው የብዙ ተዋንያን የኤክስቴንሽን አገልግሎትን፣ የእሴት ሰንሰለትን፣ ገበያ ተኮርነትን፣ በተጠቃሚው ፍላጐት ላይ የተመሠረተ አገልግሎት አቅርቦትን ትኩረት የሚያደርግ አቅጣጫዎች አስቀምጧል። ይሁንና ስትራቴጂውን ለማስፈፀም የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ አልወጣም እንዲሁም ተቋማዊ አሰራርና ስርዓት አልተዘረጋም።

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የኤክስቴንሽንና ምክር አገልግሎት የተለያዩ ተዋንያን የሚሳተፉበት፣ ጥራትን ማዕከል ያደረገ፣ አማራጭ፣ ተወዳዳሪና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን፣ በተጠቃሚው ፍላጐት ላይ የተመሠረተ፣ ተደራሽነት ያለው፣ አሳታፊ የሆነ፣ የእሴት ሰንሰለትን መሠረት ያደረገ ምሉዕና አካታች እንዲሆን ይደረጋል።

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የግብርና ኤክስቴንሽን ስትራቴጂ ይሻሻላል፣
- በኤክስቴንሽንና ምክር አገልግሎት ለመሰማራት ለሚፈልጉ ተዋንያን ምዝገባ፣ ፍቃድ እና ቁጥጥር፣ በመካከላቸው የሚኖረውን ቅንጅታዊ አሰራርና ተጠያቂነት የሚወስን የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ መዋቅራዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣
- የብዙ ተዋንያን የኤክስቴንሽንና ምክር አገልግሎት የክፍያ ስርዓት ይዘረጋል፣
- የመንግስት የኤክስቴንሽንና ምክር አገልግሎት ተወዳዳሪና ተጠያቂ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል።

### 5.2.3 የሰብል ልማት ግብዓት

#### 5.2.3.1 የአፈር ማዳበሪያ እና ሌሎች የአፈር ለምነትና ጤንነት ግብዓት

የአፈርን ለምነትና ጤንነትን ለማሻሻል የሚያግዙ ግብዓቶች (የአፈር ማዳበሪያ፣ ግብርና ኖራ፣ ጅብሰም እና የተፈጥሮ ማዳበሪያዎች) የምርት እና ምርታማነት ዕድገትን

እንዲጨምር ለማድረግ፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ በማዕድንና በንጥረ ነገር የበለፀገ ምርት ለማምረት ጉልህ ሚና አላቸው። መንግስት የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትን ለመደገፍ የማዳበሪያ ማምረትና ንግድ የህግ ማዕቀፍ ስራ ላይ እንዲውል አድርጓል። ይሁንና የፖሊሲው ትኩረት የነበረው የአፈር ማዳበሪያ ከውጪ አስገብቶ ማሰራጨት እና አፈፃፀሙም በዋናነት በመንግስት እና በህብረት ስራ ማህበራት የተመራ ነበር።

ነባሩ ፖሊሲ የአፈር ለምነትን፣ ሥርዓተ-ምህዳርን እና የተጠቃሚውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የማዳበሪያ ፍላጎትን ለማሰባሰብና ለማጠናከር የሚረዳ ስርዓት ካለመኖሩም ባሻገር በውስን ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ ዓይነት ላይ ብቻ በማተኮርና ለሌሎች የአፈር ለምነት ማሻሻያ ግብዓቶች በተለይም የተፈጥሮ ማዳበሪያ፣ የግብርና ኖራ፣ ጅብሰም ትኩረት አለመስጠት በሀገር ደረጃ ለተመዘገበው አነስተኛ የማዳበሪያ አጠቃቀም ዋነኛ ምክንያቶች ናቸው። የማዳበሪያ የአቅርቦት እና ስርጭት ሥርዓት ፍላጎትን መሰረት ያደረገ አለመሆን፣ እሴት የማይጨምሩ ተዋናዮች መብዛት እንዲሁም በቂና የተቀላጠፈ አጋዥ የሎጂስቲክስ አቅርቦት እጥረት ምክንያት ማዳበሪያን ተጠቃሚዎች በሚፈልጉበት ወቅትና ጥራትን በጠበቀ መልኩ ከማቅረብ አኳያ የጎላ ክፍተት ይስተዋላል።

የማዳበሪያ እና የሌሎች የአፈር ለምነት ማሻሻያ ግብዓቶችን በባለቤትነት የሚመራ ተቋማዊ አደረጃጀት እና ቅንጅታዊ አሰራር ባለመስፈኑ አዳዲስ የማዳበሪያ አይነቶችን ለመመዝገብ፣ ተገቢውን የጥራት ደረጃ ለማውጣትና ለመተግበር እንዲሁም የጥራት ቁጥጥር ለማከናወን የሚያስፈልጉ የተሟሉ የአፈር ላቦራቶሪዎችና የመሰረተ ልማት አለመዘርጋት እንዲሁም ለዘርፉ በቂ የብድር አቅርቦት እና ጠንካራ የብድር አመላለስ ስርዓት አለመኖር የዘርፉ ዋነኛ ተግዳሮቶች ናቸው።

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የአፈር ለምነትና ጤንነት ሥርዓተ-ምህዳርን እና የተጠቃሚውን ፍላጎት ላይ እንዲመሰረት ይደረጋል፣
- የማዳበሪያን ከውጭ ከማስገባት ይልቅ አገር ውስጥ ማምረት እና የሀገር ውስጥ ፍላጎትን አሟልቶ ወደ ውጭ መላክ፣ በተወሰኑ ሰው ሰራሽ የማዳበሪያ አይነቶች ላይ ከማተኮር ይልቅ ሥርዓተ-ምህዳርን መሰረት ያደረገ የተቀናጀ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ላይ እንዲያተኩር ይደረጋል፣

- የማዳበሪያ ማምረት፣ አቅርቦትና ግብይት የግል ባለሃብቱና የህብረት ስራ ማህበራት ሚና እንዲያድግ ይደረጋል ፣
- የማዳበሪያ ጥራትና ቁጥጥር ስርዓቱ ጠንካራ ሆኖ ይገነባል፡፡

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የማዳበሪያ ፖሊሲ ይነደፋል፣ የህግ ማዕቀፍ ይሻሻላል፣ የጥራትና ቁጥጥር ስርዓት ይጠናከራል፣ መዋቅራዊ አደረጃጀትና መሰረተ ልማት ይዘረጋል፣
- የሌሎች የአፈር ለምነትና ጤንነት ማሻሻያ ግብዓቶች የፖሊሲ ማዕቀፍና የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

### 5.2.4.2 የዕጽዋት ዘር

ጥራቱን የጠበቀ የተሻሻሉ የዕጽዋት ዘር መጠቀም ሌሎች የግብርና ቴክኖሎጂዎችና ግብዓቶች ተጠቃሚነትን በማሻሻል ለምርትና ምርታማነት እድገት ወሳኝ ግብዓት ነው፡፡ ይህንኑ በመገንዘብ መንግሥት ሀገራዊ የዘር ኢንዱስትሪ የህግ ማዕቀፍ እና ተቋማዊ ስርዓት ዘርግቷል፡፡ የዘር አቅርቦት ስርዓቱን ለማጠናከር የፌዴራልና የክልል የምርጥ ዘር ድርጅቶች በማቋቋም እንዲሁም በየጊዜው ተሳትፎአቸው እየጨመረ የመጣውን የግሉ ዘርፍ ተሳታፊዎችን አቅም ለመገንባት የድጋፍና የቁጥጥር ስርዓት ተዘርግቷል፡፡

ነባሩ ፖሊሲ የተሻሻሉ ዘር የማፍልቅ፣ የመፈተሽና በሰርቶ ማሳያ ደረጃ ለተጠቃሚዎች የማስተዋወቅ ስራ በዋነኝነት የመንግስት ድርሻ እንደሆነ አስቀምጧል፡፡ የማባዛቱ ስራ በአብዛኛው በግል ባለሃብቶችና በተመረጡ አርሶ አደሮች እንደሚከናወን ቢያመላክትም አፈፃፀሙ ግን በመንግስት ምርጥ ዘር ደርጅቶች የተመራ ነው፡፡ በተጨማሪም የዘርፉ የግብይት ስርዓት በተገቢው ያልተዘረጋ በመሆኑ የዘር ስርጭቱ በአብዛኛው በህብረት ስራ ማህበራት በኩል የሚፈፀም ነው፡፡ የግል ዘር አምራቾች ከተጠቃሚው ጋር በቀጥታ መገናኘት የሚችሉበት አሰራር በተሟላ ሁኔታ አልተዘረጋም፡፡

ለሁሉም ባለድርሻ አካላት በቀላሉ ተደራሽ የሆነና ተአማኒነት ያለው የዘር ፍላጎትና አቅርቦት ማሰባሰቢያና ማጠናቀሪያ ስርዓት አለመኖር፣ ያለውም ስርዓት ቢሆን በውስን ሰብሎችና ዝርያዎች ላይ ያተኮረ በመሆኑ፣ ለሌሎች ሰብሎችም ሆነ አዳዲስ ለሚለቀቁ ዝርያዎች አሰራር ባለመዘርጋቱ፣ ዘር አምራቾች በግብይት ስርዓቱ ላይ ያላቸው ሚና

አነስተኛ መሆኑ እና የዘር ግብይት መሰረተ ልማት በበቂ ሁኔታ አለመደራጀቱ እና የዘር ጥራት ማረጋገጥ እና ኳራንታይን አሰራሩም አለመጠናከር የዘር ኢንዱስትሪውን ጎድቶት ቆይቷል፡፡

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የዕፅዋት ዘር አቅርቦት ሥርዓተ-ምህዳርን እና የተጠቃሚውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ፣ የሀገር ውስጥ ፍላጎትን አሟልቶ ወደ ውጭ መላክ የሚያስችል አቅም ይፈጠራል፣
- የምርጥ ዘር አቅርቦትና ግብይት በገበያ መርሆዎች የሚመራ ይሆናል፣
- የግል ባለሃብቱንና የህብረት ስራ ማህበራትን ሚና እንዲጎላ ይደረጋል፣
- የዕፅዋት ዘር ጥራትና ቁጥጥር ስርዓቱ ጠንካራ ሆኖ ይገነባል፣
- የመንግስት ምርጥ ዘር ድርጅቶች በዘር ኢንዱስትሪው ሊጫወቱት የሚገባውን ሚናና ሃላፊነት ተለይቶ ማሻሻያ ይደረጋል፣

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የዕጽዋት ዘር የፖሊሲ ይነደፋል፣ የህግ ማዕቀፍ ይሻሻላል፣ የጥራትና ቁጥጥር ስርዓት ይጠናከራል፣ መዋቅራዊ አደረጃጀትና መሰረተ ልማት ይገነባል፣
- የመንግስት ምርጥ ዘር ድርጅቶችን በዘር ኢንዱስትሪውን ሚናቸውንና ሀላፊነታቸውን በአግባቡ የሚለይ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የዕጽዋት ዘር መጠባበቂያ ክምችት ሥርዓት ይደራጃል፡፡

### 5.2.3.3 የፀረ-ተባይ ኬሚካል

ሰብልን ከተባይ፣ ከበሽታ አምጪ ተዋስያን እና ከአደገኛ ወራሪ አረሞች ጥቃት መከላከል የቅድመና ድህረ ምርት ብክነትን በመቀነስ ምርትን ለመጨመር ብሎም የመዳረሻ ገበያዎች የምርት ጥራት መስፈርትን ለማሟላት የፀረ-ተባይ ኬሚካል መጠቀም ዋነኛ የሰብል ጤና ጥበቃ ዘዴ ሆኖ ይገኛል፡፡ መንግስት የፀረ-ተባይ ኬሚካል ምዝገባና ቁጥጥር የህግ ማዕቀፍ ስራ ላይ አውሏል፡፡

ይሁንና በስራ ላይ ያለው የህግ ማዕቀፍ አንድ የተመዘገበን ፀረ-ተባይ ኬሚካል የመጀመሪያው አስመጪ ሳይፈቅድ በሌላ አስመጪ ወደ ሀገር ለማስገባት እንደሚቻል በግልፅ ባለመደንገጉ፣ በሀገር ውስጥ የኢንቨስትመንት ፍቃድ አውጥተው በመስራት ላይ ያሉ አለም አቀፍ አምራቾች የራሳቸውን የተመረተ (በፓተንት የተመዘገበ) ፀረ ተባይ በሀገር ውስጥ ለማስመዝገብና የተጠቃሚዎችን ፍላጎት ለማነሳሳት ስራ እንዲሰሩ የማያበረታታ እንዲሁም በሀገር ውስጥ ለማምረት፣ ለማዘጋጀት፣ ለማሸግ እና ዳግም ለማሸግ የሚያስችሉ ድንጋጌዎች ባለማከተቱ ምክንያት የግሉን ዘርፍ እና የህብረት ስራ ማህበራትን በፀረ-ተባይ አቅርቦትና ግብይት ተሳትፏቸው ዝቅተኛ ነው። ሌላው የነባሩ ፖሊሲ ትኩረት የነበረው ፀረ-ተባይ ከውጪ አስገብቶ ማሰራጨት ሲሆን የርጭት ስራውም የሚከናወነው በተነፃፃሪ የጤናና የአካባቢ ጉዳትን የሚቀንሱ አማራጭ የተባይ መከላከያ መንገዶችን የሚያበረታታ አልነበረም። በተጨማሪም ሀገሪቱ ያላት ፀረ-ተባይ ኬሚካል የመቆጣጠር አቅም ውስን እንዲሆን እና ፀረ-ተባይ ኬሚካልን በወቅቱ ለማስወገድ ባለመቻሉ ጥቅም ላይ ሊውሉ የማይችሉና ጊዜ ያለፈባቸው የፀረ-ተባይ ኬሚካል ክምችት እንዲፈጠር አስገድዷል።

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የፀረ-ተባይ አቅርቦትን በበቂ መጠንና ዓይነት ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት እንዲሁም በሀገር ውስጥ ለማምረት፣ ለማዘጋጀት፣ ለማሸግ እና ዳግም ለማሸግ የሚያስችል አቅም በመፍጠር የሀገር ውስጥ ፍጆታን አሟልቶ ወደ ውጭ ለመላክ የሚያበረታታ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፣
- የፀረ-ተባይ ኬሚካል ጠንካራ የምዝገባ፣ ጥራትና ቁጥጥር ሥርዓት ይፈጠራል፣ ግብይቱና ስርጭቱ በገበያ መርሆዎች እንዲመራ ይደረጋል፣
- የመንግስት የፀረ-ተባይ ኬሚካል አምራች ድርጅቶች በዘርፉ ሊጫወቱት የሚገባውን ሚናና ሃላፊነት ተለይቶ ማሻሻያ ይደረጋል፣
- የፀረ-ተባይ ኬሚካል አጠቃቀም የጤና እና የአካባቢ ጉዳት እንዲቀንስ ይደረጋል፣ ጥቅም ላይ የማይውሉ ጊዜ ያለፈባቸው የፀረ-ተባይ ክምችት እንዳይፈጠር እና ተፈጥሮ ሲገኝ በወቅቱ እንዲወገድ ይደረጋል።

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የፀረ-ተባይ ኬሚካል አጠቃቀም እና አያያዝ ፖሊሲ ይነደፋል፣ የህግ ማዕቀፍ ይሻሻላል፣ ጠንካራ መዋቅራዊ አደረጃጀት ይገነባል፣
- የመንግስት የፀረ-ተባይ አምራች ድርጅቶች በዘርፉ የሚጫወቱትን ሚናና ሀላፊነት የሚያሻሽል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- ጥቅም ላይ የማይውሉ ጊዜ ያለፈባቸው የፀረ-ተባይ ክምችት እንዳይፈጠር እና ተፈጥሮ ሲገኝ በወቅቱ ለማስወገድ የሚያስችል አሰራር ስርዓት ይዘረጋል።

## 5.2.4 የእንስሳትና አሳ ሀብት ልማት ግብዓት

የእንስሳትና አሳ ሃብታችን በቁጥርም ሆነ በተለያይነት /Genetic diversity/ ከፍተኛ ሲሆን ይህን በአግባቡ ማርባትና ጥቅም ላይ ማዋል ለምግብና ስርዓተ-ምግብ ዋስትና፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓትና ለወጪ ንግድ በቂ አቅርቦት እንዲሁም በእሴት ሰንሰለቱ ውስጥ ሰፊ የስራ ዕድል እንዲፈጠር ያስችላል። ነባሩ ፖሊሲ የዝርያ ማሻሻያ፣ መኖ አቅርቦት ማሻሻል እና የጤና ጥበቃ ስራዎች ላይ ትኩረት ያደረገ ነበር። በቅርቡም የእንስሳትና አሳ ሃብት ልማት ፍኖተ ካርታና የእንስሳት ርቢ ፖሊሲ ተቀርጾ ወደ ስራ ተግብቷል።

ሆኖም ግን የእንስሳትና አሳ ሀብት ልማት የፖሊሲ ማዕቀፍ እሴት ሰንሰለትን የተከተለ ልማትና ግብይት በተቀናጀ መልኩ ለመምራት፣ የምርቶቹን ልዩ ባህርይ ባገነዘበ መልኩ የልማት አቅጣጫን ማስቀመጥ፣ የምርት አቅርቦት መጠንና ዓይነት የሚለይ፣ ለጥራትና በእሴት ጭመራን ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ፣ የገበያ ትስስርና ማልማት ስራዎችን ለማከናወን፣ የወጪ ንግዱን መዳረሻ ገበያዎችን ለማስፋትና የዋጋ ተወዳዳሪነትን ለማሻሻል እንዲሁም አስቻይና ደጋፊ አገልግሎቶችን ለማቀረብ የሚያስችል የተሟላ የህግ ማዕቀፍና አሰራር ስርዓት አልተዘረጋለትም። በተጨማሪም የእንስሳት ሀብት ልማት ለሀገራዊ የግብርና ምርት እንዲሁም የስርዓተ ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ካለው አስተዋፆ አንፃር ለልማቱ የተሟላ ትኩረትና ድጋፍ አልተሰጠውም። በሌላ በኩል የእንስሳት እርባታ በኃላቀርና የተበታተነ የአረባብ ዘዴ የሚከተል በመሆኑ እያደገ የመጣውን የአንስሳት ተዋፅዖ ፍላጎት ለማሟላት አልተቻለም። በመሆኑም ይህንን ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል ዘመናዊ የእንስሳት፣ አሳና ንብ እርባታ ስርዓት ለመዘርጋት እንዲቻል የዝርያ ማሻሻል፣ መኖ እና የጤናና ደህንነት ግብዓት አቅርቦት ለማሻሻል የተሟላ የፖሊሲ ማዕቀፍ ያስፈልጋል።

### 5.2.4.1 የእንስሳትና ዓሳ ዝርያና ዘር እና የርባታ ግብዓት

የተሻሻሉ የእንስሳት እና የዓሳ ዝርያዎችን መጠቀም የእንስሳትና አሳ እርባታን ለማዘመን እና ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ወሳኝ ግብዓት ነው፡፡ ይህንኑ ዕውን ለማድረግ የተሻሻሉ ዝርያዎችን ለተጠቃሚው ለማቅረብ መንግስት የምርምር እና በሰው ሰራሽ ዘዴ የቀንድ ከብት የማዳቀያ ማዕከላት በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች አቋቁሟል፡፡

የፖሊሲው ትኩረት የነበረው ከፍተኛ ምርት የሚሰጡ ዝርያዎችን ከውጭ በማስገባት ሲሆን አፈፃፀሙ በአመዛኙ በመንግስት ፕሮጀክቶች የተመራ እና የግል ባለሃብቱን ተሳትፎ ዝቅተኛ ነበር፡፡ እስካሁን የተከናወኑትም የእንስሳትና የዓሳ ዝርያዎች ማሻሻል ስራዎች ሥርዓት ባለው መንገድ ባለመመራታቸው ይህ ነው የሚባል ውጤት ካለማስመዝገባቸውም በላይ የእንስሳትና የዓሳ ዘር ሃብታችንን ባልተፈለገ መንገድ በመበረዝና በመሸርሸር ላይ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም የሀገር ውስጥ የእንስሳት ዝርያዎቻችን በልቅ የርቢ ሂደት ምክንያት ተፈላጊ ባህርያታቸው እየተሸረሸሩና እየተበረዙ በመሄድ ንጹህ የሀገር በቀል የእንስሳት ዝርያ እንዳይጠፋ የሚጠብቅ የህግ ማዕቀፍና አሰራር አልተዘረጋም፡፡ ይህንን የፖሊሲና የአሰራር ክፍተት ለመሙላት የእንስሳትና የአሳ ዝርያዎችንና ዘሮችን በባዮቴክኖሎጂ ዘዴ የስነ-ዘረመል ቁስ በመጠበቅ ለማሻሻል እና በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል የእንስሳት ርቢ ፖሊሲና ስትራቴጂ ተነድፏል፡፡ ይሁንና ፖሊሲውንና ስትራቴጂውን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እና ተቋማዊ አሰራርና ስርዓት አልተዘረጋም፡፡

የንብ እርባትን ለማዘመን የሚያስፈልጉ ግብዓቶች (ንግስት፣ የተሻሻል ቀፎዎች፣ የንብ ሰም) አቅርቦትና ግብይት ስርዓት አለተዘረጋም፡፡ በመሆኑም ካለን መጠነ ሰፊ የእንስሳትና አሳ ሃብት ሀገራችን ተጠቃሚ መሆን ሳትችል ቆይታለች፡፡

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የተሻሻሉ የእንስሳትና የዓሳ የውጪ ዝርያዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት፣ ለማዳቀልና በሀገር ውስጥ ለማባዛት እና የሀገር በቀል ዝርያዎችን እንደየአግባባቸው በመለየት ለማሻሻልና ለማባዛት የሚያስችል አቅም ይፈጠራል፣
- የተሻሻሉ የእንስሳትና የዓሳ ዝርያና ዘር አቅርቦትና ግብይት በገበያ መርሆዎች እንዲመራ ይደረጋል፣

- የግል ባለሃብቱ እና የህብረት ሥራ ማህበራትን ተሳትፎ የሚያበረታታ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፣
- የመንግስት የዝርያ ማሻሻያ፣ የብዜት እና ማዳቀያ ማዕከላት ውጤታማነታቸውን ለማጎልበት ሚናቸውና ሃላፊነትቻው ተለይቶ ማሻሻያ ይደረጋል፣
- ጠንካራ የጥራትና ቁጥጥር ሥርዓት እና ስርዓቱን አቀናጅቶ የሚመራ ተቋማዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፡፡

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የእንስሳትና ዓሳ ርቢ የፖሊሲና የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ መዋቅራዊ አደረጃጀትና መሰረተ ልማት ይዘረጋል፣
- የተሻሻሉ የእንስሳትና አሳ ዝርያዎችና ዘር አቅርቦትና ግብይት አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የንብ ርባታ የፖሊሲ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የግብዓት አቅርቦትና ግብይት አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የመንግስት የእንስሳትና የዓሳ ምርምር እና የቀንድ ከብት የሰው ሰራሽ ማዳቀያ ማዕከላት በከፊል ለትርፍ ወደሚስሩ ተቋማትነት የሚቀየሩበት የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

### 5.2.4.2 መኖ

ጥራቱን የጠበቀ መኖ የእንሰሳት ሃብት ምርትና ምርታማነት በማሻሻልና ትርፋማ በማድረግ የእንስሳት ሃብት ልማትን ለማዘመን ወሳኝ ግብዓት ነው፡፡ ይህንኑ ዕውን ለማድረግ መንግስት የመኖ ልማት እና አቅርቦት ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡ የመኖ ልማትና ንግድ አስተዳደርና ቁጥጥር ለማጠናከርና የመኖ ልማቱን ኢንዱስትሪና የእንስሳት እርባታውን በማሻሻል የሕዝብን ጤንነት ለመጠበቅ መንግስት የቁጥጥር ህግ ማዕቀፍ ስራ ላይ አውሏል፡፡ በተጨማሪም የመኖ ጥራትና ደህንነት ቁጥጥር ተግባራትን ለማከናወን የዋና ዋና የመኖ ግብዓቶችንና በፋብሪካ የተቀነባበሩ ምጥን መኖዎችን የደህንነትና የጥራት ደረጃዎች ወጥቶላቸዋል፡፡

ይሁንና ለመኖ ልማት የሚውሉ መሬቶችን በአግባቡ ለይቶ የሚያስቀምጥ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ ባለመኖሩ፣ መኖ ማምረትና ለገበያ ማቅረብ እንደ አንድ ወሳኝ

የግብርና ዘርፍ አለመታየትና ለማስፋፋት የሚረዳ አበረታች የአሰራር ስርዓት ካለመዘርጋቱም ሌላ የእንስሳት መኖ ልማትና ግብይት የሚመራበት የተሟላ የፖሊሲ ማዕቀፍ አልተዘረጋም።

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የተሻሻሉ የመኖ ሰብሎች፣ የተፈጥሮ ግጦሽ፣ የሰብል ተረፈ ምርት እና በፋብሪካ የተዘጋጁ መኖዎችን በበቂ (በኮሜርሻል ደረጃ) ለማምረት፣ አቅርቦትንና ግብይት በገበያ መርሆዎች ይመራል፣
- የሀገር ውስጥ ፍጆታን አሟልቶ ወደ ውጭ ለመላክ እድል የሚፈጥርና የሚያበረታታ እንዲሆን ይደረጋል፣
- የግል ባለሃብቱ እና የህብረት ሥራ ማህበራትን ተሳትፎ የሚያበረታታ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፣
- የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲው ለመኖ ልማት የሚውሉ መሬቶችን መለየት ተገቢውን ትኩረት ይሰጣል፣
- የሬንጅላንድ እና የተፈጥሮ ግጦሽ አያያዝና አጠቃቀምን ፍላጎትን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ይደረጋል፣
- ጠንካራ የመኖ ጥራትና ቁጥጥር ሥርዓት ይጠናከራል።

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የእንስሳት መኖና ሥነምግብ ስትራቴጂ ይሻሻላል፣ የህግ ማዕቀፍ ይቀረፃል፣ መዋቅራዊ አደረጃጀትና ቅንጅታዊ አሰራር ይዘረጋል፣
- በዕፅዋት ዘር ፖሊሲና ህግ ማዕቀፎች ለመኖ ዘር ልማት ተገቢውን ትኩረት የሰጠ ሆኖ ይነደፋል።

### 5.2.4.3 የእንስሳት ጤና ግብዓት

የእንስሳት በሽታ አምጪ ተህዋስያንና በሽታ አስተላላፊ ተባዮችን ጥራቱ፣ ደህንነቱና ፈዋሽነቱ የተረጋገጠ የእንስሳት መድሃኒትና ክትባት ተጠቅሞ ለመከላከል እና ለማከም የእንስሳት ሀብት ልማትንና ጤንነት አጠባበቅን ለማሻሻል፣ እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች በዓለምአቀፍ ገበያ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ እና የህብረተሰብ ጤናን ለመጠበቅ የእንስሳት ጤና ግብዓት ወሳኝ ነው።

ይህንንም ፍላጎት ለማሟላት የእንስሳት ክትባት በሀገር ውስጥ የማምረት አቅምን ለማሳደግ የብሄራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩትን በማቋቋም የእንስሳት በሽታን ለማከም ብሎም ለመከላከል ሰፊ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ በመመደብ የእንስሳት መድሃኒት ከውጪ ማስገባት እንዲሁም የእንስሳት መድሃኒት ተዘዋዋሪ ፈንድ ዘርግቶ አቅርቦትን ሲደግፍ ቆይቷል፡፡ ይህንኑ በፖሊሲ ለመደገፍ የእንስሳት መድሃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር የህግ ማዕቀፍ ስራ ላይ ውሏል፡፡ ድንበርና ክልል ተሻጋሪ መድሃኒቶችን መቆጣጠር ትኩረት በማድረግ ተግባርና ሃላፊነት ለፌዴራል ተቆጣጣሪ አካል የተሰጠ ሲሆን በክልል ውስጥ ብቻ የሚከናወኑ የቁጥጥር ተግባራት ለክልሎች ተሰጥቷል፡፡

የእንስሳት መድሃኒት አቅርቦት የበሽታ ስርጭት፣ የእንስሳት ብዛት እና ወቅትን መሰረት ያደረገ የትንበያ ስርዓት የሚከተል አለመሆኑ በተጠቃሚው የሚፈለጉ መድሃኒቶችን በበቂ መጠንና አይነት ከውጪ ለማስገባት፣ በሀገር ውስጥ ለማምረት እና ለማቅረብ አልተቻለም፡፡ በአነስተኛ መጠን የሚፈለጉ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ የተመዘገቡ ወይም ያልተመዘገቡ መድሃኒቶችን ለማስገባት የሚያስችል የማበረታቻና አሰራር ስርዓት አለመዘርጋቱ በገበያ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ እጥረት እንዲከሰት አድርጓል፡፡ የእንስሳት በሽታን ለመመርምር የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በበቂ ሁኔታ ባለመሟላታቸው ምክንያት ተገቢ ያልሆነ የእንስሳት መድሃኒት በመጠቀም በአለም በከፍተኛ ደረጃ ስጋት ለሆነው ተህዋሲያን መድሃኒትን እንዲላመዱ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡

የመድሃኒትና ክትባት ቁጥጥር ስርዓት በክልል ደረጃ ቁጥጥር ስራውን የሚሰራ አካል ራሱን ችሎ አለመደራጀቱ እንዲሁም በክልሎች ተግባርና ሃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ አለመኖሩ የህገ ወጥ የመድሃኒት ዝውውር እና ተገቢ ያልሆነ የመድሃኒት አያያዝና አጠቃቀም አስከትሏል፡፡ በተጨማሪም ገበያ ላይ እንዲውሉ የተፈቀዱ መድሃኒቶች በመስክ ስራ ወቅት  የጥራት፣ የፈዋሽነት እና የደህንነት ችግር ሲኖርባቸው የመስክ ባለሙያዎች የተቀናጀ መረጃ አሰራር ስርዓት ባለመዘርጋቱ የጥራትና ደህንነትና ፈዋሽነት ችግር ያለባቸው መድሃኒቶች በገበያ ውስጥ እንዲዘዋወሩ አስተዋፆ አድርጓል፡፡

የእንስሳት መድሃኒት አቅርቦት በውስን አምራቾች የተንጠለጠለ በመሆኑ አብዛኛው ከውጪ የሚገቡ መድሃኒቶች ላይ ያተኮረ ሆኗል፡፡ ሆኖም ግን በውጪ ምንዛሬ እጥረት

የመድሃኒት በሚፈለበት ወቅት፣ አይነትና መጠን ለማቅረብ አልተቻለም። በተመሳሳይም ክትባት ማምረትና አቅርቦት በአንድ የመንግስት ድርጅት ብቻ የሚከናወን መሆኑና ይህም ቢሆን በተወሰኑ ምርቶች ላይ የሀገር ውስጥ ፍላጎትን አሟልቶ ወደ ውጭ የመላክ አቅም ቢፈጠርም በአይነትና በጥራት የማምረት የአቅም ውስንነት አለበት። በሌላ መልኩ ባህላዊ የእንስሳት ህክምና ዘዴ የአሰራር ስርዓትና ተቋማዊ አደረጃጀት ባለመዘርጋቱ ለእንስሳት ህክምና ያለውን አስተዋፆ በተሻለ መልኩ መጠቀም አልተቻለም።

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የእንስሳት መድሃኒት፣ ክትባት እና የህክምና መሳሪያ አቅርቦትን በበቂ መጠንና አይነት ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት እንዲሁም በሀገር ውስጥ ለማምረት እና የሀገር ውስጥ ፍጆታ አሟልቶ ወደ ውጪ ለመላክ አቅምና ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፣ አቅርቦትና ግብይቱ በገበያ መርሆዎች ይመራል፣
- ጠንካራ የምዝገባ፣ ጥራትና ቁጥጥር ሥርዓት ይገነባል።

**የማስፈሚያ ስልቶች**

- የእንስሳት መድሃኒት፣ ክትባትና ሌሎች ተያያዥ ግብዓቶች አጠቃቀም እና አያያዝ የህግ ማዕቀፍ ይሻሻላል፣ መዋቅራዊ አደረጃጀት ይጠናከራል፣ መሰረተ ልማት ይዘረጋል፣
- የገበያ ጉድለት ለሚስተዋልባቸው የመድሃኒትና ክትባት አይነቶች አቅርቦትና ፋይናንስ አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የግል ዘርፉን ተሳትፎ ለማሳደግ የአስቻይ ሁኔታና የማበረታቻ ስርዓት እንዲሁም የመንግሰት እና የግል አጋርነት የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የባህላዊ የእንስሳት ህክምናና መድሃኒት የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- ጥቅም ላይ የማይውሉ ጊዜ ያለፈባቸው የእንስሳት መድሃኒት ክምችት እንዳይፈጠር እና ተፈጥሮ ሲገኝ በወቅቱም ለማስወገድ የሚያስችል አሰራር ስርዓት ይዘረጋል።

### 5.2.5 የዕፅዋት ጤና ጥበቃ አገልግሎት

ሰብልን ከበሽታ፣ ነፍሳት ተባይና አረም መከላከልና መቆጣጠር፣ ቅድመና ድህረ ምርት ብክነትን በመቀነስ ምርትን ለመጨመር ብሎም የመዳራሻ ገበያዎች ጥራት

መስፈርቶችን ለማሟላት ዋነኛ አገልግሎት ነው። መንግስት ለተወሰኑ ተባዮች የቅኝት፣ አሰሳ፣ ክትትል፣ ትንበያና ቅድመ ማስጠንቀቅያ፣ የዕፅዋት ተባይ ልየታና ትንተና፣ ድህረ-ምርት ተባይ መከላከል ስርዓት ዘርግቶ የመከላከልና የቁጥጥር ስራዎች እያከናወነ ይገኛል። ይህንን ለማገዝ በተለያዩ ጊዜና ደረጃ የሰብል ጤና ክሊኒኖችና የምርምር ስራዎች ተሰርተዋል። ሆኖም ግን አየር ንብረት ለውጥ እና ሌሎች ምክንያቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፉና እየጨመረ የመጣውን ተባዮች ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የተሟላ የፖሊሲ ማዕቀፍ እና መሰረተ ልማት ክፍተት ይታያል።

የሰብል ጥበቃ ስራን በተጠናከረ ተቋማዊ አደረጃጀት እና ቅንጅታዊ አሰራር ባለመመራቱ የዘርፉ ተዋንያን እና መሰረተ ልማት በአግባቡ መጠቀም አልተቻለም። በተለይም የዕፅዋት ጤና ክሊኒኖች የተሟላ መሰረተ ልማት ባለመሟላቱ ተልዕኮቻቸውን ለመወጣት ተግዳሮት ሆኖ ይገኛል። በተመሳሳይም የሰብል ጥበቃ አገልግሎት እንደ አንድ የአገልግሎት ዘርፍ እንዳይስፋፋ እንቅፋት ሆኗል። ይህም አርሶ አደሩን በበቂ ሁኔታ በመደገፍ በነፍሳት ተባይ፣ በበሽታና አረም የሚደርሰውን ጥቃት በመከላከል ምርትና ምርታማነትን በሚለፈገው መጠን ለማሳደግ አልተቻለም።

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የድንበር ዘለል ተዛማችና መደበኛ ተባዮችን አፋጣኝ ምላሽ መስጠት የሚያስችል የተባይ ቅኝት፣ አሰሳ፣ ክትትል፣ ትንበያና ቅድመ ማስጠንቀቅያ ስርዓት እንዲጠናከር ይደረጋል፣
- የዕፅዋት ጤና አጠባበቅ፣ የመከላከልና የመቆጣጠር ስርዓት (የተቀናጀ የተባይ በሽታን መከላከያ መንገዶችን ጨምሮ) እንዲጠናከር ይደረጋል፣
- የተቀናጀ ተቋማዊ አደረጃጀትና መሰረተ ልማት ይገነባል።

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የዕፅዋት ጤና አጠባበቅ ፍኖተ ካርታ ይነደፋል፣ ተቋማዊ አደረጃጀትና መሰረተ ልማት ይጠናከራል፣
- የእፅዋት ተባይ መቆጣጠርና መከላከል አገልግሎት ስትራቴጂ ይሻሻላል፣
- የድንበር ዘለል ተዛማችና መደበኛ ተባዮች አሰሳ፣ ትንበያና ቅድመ ማስጠንቀቂያና መከላከል ስርዓት ይሻሻል።

### 5.2.6 የእንስሳት ጤናና ደህንነት አገልግሎት

እንስሳት ከተለያዩ በሽታዎች ለመከላከልና ድህንነታቸውን በመጠበቅ ምርትና ምርታማነታቸውን ለማሳደግ እና የመዳራሻ ገበያዎችን የጤና እና ምርት ጥራት መስፈርቶች ለማሟላት የእንስሳት ጤና እና ደህንነት አገልግሎት ዋነኛ መሳሪያ ነው:: የእንስሳት ጤና አገልግሎትን ለማዘመንና ለመደገፍ የሚያስችሉ የሕግ ማዕቀፍች ስራ ላይ ውለዋል::

ሆኖም ግን የህግ ማዕቀፎቹ የተወሰኑ እንስሳት በሽዎችን ስለመከላከልና ስለመቆጣጠር የተደነገጉ፣ የእንስሳት ደህንነትን፣ የእንስሳት ልየታን፣ የማህበረሰብ ጤና፣ ድንበር ተሸጋሪ እንስሳቶችን ጉዳይ በበቂ ሁኔታ ያላካተቱ ናቸው:: በተጨማሪም የእንስሳት ጤና አገልግሎት ስርዓት የመንግስትና የግሉን ዘርፍ ሚዛናዊና አግባብ ባለዉ መልኩ ያላሳተፈና አገልግሎቱ በመንግስት ላይ የተንጠለጠለ አድርጎታል:: ሆኖም ግን ደረጃውን የጠበቀ፣ ተደራሽ እና ፈጣን ምላሽ መስጠት የሚያስችል እንዲሁም እያደገ የመጣ ያለውን ዘመናዊ ስልተ ምርቶችን ያማከለ የእንስሳት ጤናና ደህንነት ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል የፖሊሲ ማዕቀፍ እና ጠንካራ ተቋማዊ አደረጃጀት አልተዘረጋም

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የእንስሳት ጤናና ደህንነት አገልግሎት ተዓማኒ፣ ተደራሽ፣ ጥራቱን የጠበቀ፣ ተወዳዳሪ እንዲሆን ግልፅ የመንግስትንና የግሉን ዘርፍ ሚናና ሀላፊነት በአገባቡ ተለይቶ ይተገበራል፣
- የግል ባለሃብቱ እና የህብረት ሥራ ማህበራትን ተሳትፎ የሚያበረታታ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፣
- የበሽታ መከላከል እና መቆጣጠርና የመረጃ ቅብብሎሽ ስርዓት ማዘመን እንዲሁም የአገልግሎቱን ጥራትና ቁጥጥር ሥርዓት ይገነባል፣

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የእንስሳት ጤና እና ደህንነት አገልግሎት ለማቅረብ የግልፅ የመንግስትንና የግሉን ዘርፍ ሚናና ሀላፊነት የሚለይ ፍኖተ-ካርታ ይነደፋል፣ የህግ ማዕቀፍ ይሻሻላል፣

የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ ገለልተኛ ተቋማዊ አደረጃጀት፣ ቅንጅታዊ አሰራርና መሰረት ልማት ይዘረጋል፣

- የመንግስት የእንስሳት ጤና ምርመራና ምርምር ማዕከላት ማሻሻያ (ማዕከላቶቹ በከፊል ለትርፍ የሚሰሩበት አሰራርን ጨምሮ) የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የግል ዘርፉን ተሳትፎን ለማሳደግ የመንግሰት እና የግል አጋርነት የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤
- ዘመናዊና ሰፋፊ እርባታዎች ለበሽታ መከላከል፣ ቁጥጥር እና ክትትል ስራ በሚያመች መልኩ እንዲቋቋሙ የሚያደርግ ብሔራዊ ባዮሴኩሪቲ ደረጃ ይወጣል፣
- በእንስሳት ጤናና በወጪ ንግድ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታ የቁጥጥርና የመከላከል አስራር ስርዓት ይዘረጋል።

### 5.2.7 የሜካናይዜሽን አገልግሎት

ሜካናይዜሽን አገልግሎት የግብርና ልማትን ከመሬት ዝግጅት ጀምሮ ሰብልና እንስሳት ምርት ማምረት፣ መሰብሰብ፣ ማቀነባበር፣ ማጓጓዝ እና ማሸግ በተሳለጠ ሁኔታ በማከናወን የሰው ሃይል፣ የመሬትና የሌሎች ግብዓቶች ምርታማነት በመጨመር፣ ቅድመና ድህረ-ምርት ብክነትን በመቀነስ እና የምርት ጥራት በማሻሻል እና የመጀመሪያ ደረጃ እሴት ለመጨመር ውሳኝ ነው።

ነባሩ ፖሊሲ የሰውን ጉልበት በሠፊው የመጠቀም አቅጣጫ ላይ ያተኮረ ቢሆንም አገልግሎቱን ለማስፋፋት የተለያዩ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ተደርገዋል። በቅርቡ የግብርና ሜካናይዜሽንን ለማስፋፋት ስትራቴጂ ተነድፏል። የሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎችን አቅርቦት ለማሻሻል እና የአገልግሎት አሰጣጡን ለማስፋፋትና ተደራሽ ለማድረግ የተወሰኑት ቴክኖሎጂዎችና መሳሪያዎች ከቀረጥና ታክስ እፎይታ ተሰጥቷል። በተጨማሪም የተወሰኑ የግብርና ሜካናይዜሽን ደረጃዎች ፀድቋል። ሆኖም ግን ከውጪ የሚገቡ ሆነ በሀገር ውስጥ እየተመረቱ ያሉ ቴክኖሎጂዎችን ጥራትና ደረጃ ማሟላታቸውን የሚቆጣጠር የአሰራር ስርዓት እና ጠንካራ ተቋማዊ አደረጃጀት በተሟላ መልኩ አልተዘረጋም።

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎችን በሀገር ውስጥ ለማምረት፣ ለማልማትና ለማባዛት እንዲሁም ከውጭ ለማስገባት የሚያስችል ምቹ ሁኔታን ይፈጠራል፣
- የግል ባለሃብትና የህብረት ስራ ማህበራት የመሪነት ሚና እንዲኖራቸው የሚያበረታታና የሚያመቻች፣ ቀልጣፋ የማስተዋወቅ፣ የሽያጭ እና የድህረ ሽያጭ አገልግሎት እንዘረጋ ይደረጋል፣
- የአጠቃቀም ስርዓት ይዘረጋል፣ ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት ይዘረጋል፣ አጋዥ መሠረተ ልማት ይገነባል፡፡

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የግብርና ሜካናይዜሽን ስትራቴጂ ይሻሻል፣ የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የጥራት ደረጃ ማረጋገጫ ጠንካራ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣መዋቅራዊ አደረጃጀትና ቅንጅታዊ አሰራር ይዘረጋል፣
- የግብርና መሳሪያዎችና ማሽነሪዎች ኦፕሬተር እና የጥገና ቴክኒሻን ብቃት ማረጋገጫ አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

## 5.2.8 የቴክኖሎጂና ግብዓት አጠቃቀም የማበረታቻ ስርዓት

የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል ቀጣይነት ያለዉ የቴክኖሎጂና የግብዓት አጠቃቀም ማሳደግ ወሳኝ ድርሻ አለው፡፡ ይሁንና በአነስተኛ አርሶና አርብቶ አደር ላይ የተመሰረተው የሀገራችን ግብርና የግብዓትና ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ደረጃ እጅግ ዝቅተኛ ነው፡፡ ምርጥ ዘር፣ ፀረ ተባይ ኬሚካል እና የአፈር ማዳበሪያ ያሉ ሌሎች ግብዓቶችን የሚጠቀሙ አርሶ አደሮች ድርሻ በአማካይ ከግማሽ በታች ቢሆን ይህም የምርታማነት እድገት በሚፈለገው ደረጃ እንዳይጨምር አድርጎታል፡፡ በተጨማሪም በትንሹ የተመረት ምርት ከፍተኛ የድህረ ምርት ብክነቱም ይደርስበታል፡፡ ከእንስሳት ልማት አኳያም ቢሆን የተሻሻለ መኖ አጠቃቀም፣ የእንስሳት አያያዝ እና ምርታማነት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የግብርና ምርታማነትና ተወዳዳሪነት ብሎም ውስጣዊ መዋቅራዊ ሽግግር የሚጠበቀውን ያህል እንዳይፋጠን የራሱን አሉታዊ አስተዋፆ ፈጥሯል፡፡

ነባሩ ፖሊሲ ለአርሶና አርብቶ አደሩ ቀጥተኛ ድጎማ ማድረግ አዋጪና ዘላቂ እንዳልሆነ ያስቀመጠ ቢሆንም የቴክኖሎጂና ግብዓት አጠቃቀምን ለማሳደግ እስከ ቀበሌ ድረስ

በተዘረጋው አስተዳደራዊ መዋቅር አማካይነት ነፃ የግብርና ምክርና ስልጠና አገልግሎት እንዲዳረስ ተደርጓል፡፡ ሆኖም ግን ቀጥተኛ ድጎማዎች ሙሉ ለሙሉ በመነሳታቸው የአርሶና አርብቶ አደሩ የመክፈል አቅም ውስን በመሆኑ ምክንያት ዘመናዊ የእርሻ መሳሪያዎች፣ የሰብልና እንስሳት ምርታማነት ማሳደጊያ ግብዓቶች እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እና አጠቃቀም የሚያግዙ ቴክኖሎጂዎችና ግብዓቶች አጠቃቀም በሚፈለገው ደረጃ አላደገም፡፡ በቅርቡ የማበረታቻን አስፈላጊነት በመገንዘብ በጥናት ላይ የተመሰረት የግብርና ቴክኖሎጂዎች እና ግብዓቶች በተነፃፃሪ በተመጣጣኝ ዋጋ ለአርሶና አርብቶ አደሮች ማቅረብ እንዲቻል የቀረጥ እና ታክስ እፎይታ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ቴክኖሎጂዎች አዳጊ በመሆናቸውና ሌሎች ሀገሮች አምራቾቻቸውን በከፍተኛ መጠን ስለሚደጎሙ የሀገራችን አርሶና አርብቶ አደሮችን በሀገር ወስጥም ሆነ በውጭ ገበያ ተወዳዳሪነት የሚፈታተን በመሆኑ እንዲሁም ለአነስተኛ አርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች፣ ለከተማ ግብርና ተዋንያን እና ለግብዓት አምራች ኢንዱስትሪዎች አግባብነት ያለው የቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ የተጠናከረ የማበረታቻ የፖሊሲ አቅጣጫና የአሰራር ስርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡

### የፖሊሲው አቅጣጫው

- የግብርና ቴክኖሎጂዎችና ግብዓት አጠቃቀምን ለማሳደግ የአርሶና አርብቶ አደሩ እና የከተማ ግብርና ተዋንያን የመክፈል አቅም ግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ፣ በጥናት የተለዩ ቴክኖሎጂዎችና ግብዓቶች የገበያ ስርዓቱን በማያዛባ ሁኔታ እና በጊዜ የተገደበ ማበረታቻ ይሰጣል፡፡

### የማስፈፀሚያ ስልቶች

- የግብርና ቴክኖሎጂዎችና ግብዓት አጠቃቀም ማበረታቻ የሚዘረጋ የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ አሰራርና ቁጥጥር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የረጅም ጊዜ ኢንቨስትመንት ለሚፈልጉ የግብርና ልማት (የፍራፍሬ፣ ቡና፣ ሻይና ቅመማቅመምን ጨምሮ) እና የተፈጥሮ ሃብት ልማት (የአፈር ለምነት ማሻሻያን ጨምሮ) ስራዎችን ማበረታቻ የሚዘረጋ የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ አሰራርና ቁጥጥር ስርዓት ይዘረጋል፣

## 5.2.9 የግብዓት ፍላጎት፣ ምርት እና አቅርቦት መከታተያ ሥርዓት

የግብርና ግብዓቶችን በአይነትና መጠን ማስፋፋትና ተደራሽ ማድረግ የሰብል እና የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው። ይህንን በመገንዘብ መንግስት የተለያዩ የፖሊሲ ማእቀፎችን ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል። ሆኖም የፍላጎት ፈጠራና ዳሰሳ የሚካሄድላቸው ግብዓቶች ውስን ከመሆናቸውም በተጨማሪ ፍላጎቱ የሚሰበሰብበት መንገድ የመረጃ ተአማኒነት የጎደለው ሆኖ ይገኛል። በመሆኑም የተጠቃሚውን ፍላጎት በአንድ በኩል የግብዓት ምርትና አቅርቦትን በሌላ በኩል በስርዓት በማጠናቀር እርስ በእርሳቸው የተጣጣሙና የተመጋገቡ እንዲሆኑ ማድረግ አልተቻለም። በዚህ ሁኔታ የቀረበው ግብዓት በአይነትም ሆነ በመጠን ከተጠቃሚው ፍላጎት ጋር አለመጣጣም ማለትም ማነስ ወይም መብዛትና ጥቅም ላይ ሳይውል ማደርን አስከትሏል። የተጠቃሚውን የግብዓት ፍላጎት በጊዜ፣ በጥራት፣ በዋጋና የአካባቢ ነባራዊ ሁኔታዎችን በተሟላ መልኩ በማገናዘብ ለማቅረብ ለግብዓቶቹ ያለው የፍላጎትን መጠን፣ ያለውን ወይም የሚኖረውን የምርት መጠን እና የአቅርቦቱን አጠቃላይ ሁኔታ መከታተል የሚያስችልና ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ተደራሽ የሆነ የተሟላ ስርዓት አልተዘረጋም። የተዘረጉትም በሙከራ ደረጃ ያሉና የተወሰኑ ግብዓቶች ብቻ ያካተቱ እና ውስን ተጠቃሚዎች ተደራሽ የሆኑባቸው ናቸው።

የግብርና ግብዓቶችን አቅርቦት ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የተጠቃሚውን የግብዓት ፍላጎት መረጃ ተአማኒነት፣ የሁሉንም የግብር ምርት ስርዓቶችን ባካተተ፣ የሀገር ውስጥ አምራቾችንና አስመጪዎችን አቅም ያገናዘበ እንዲሁም ግብይትንና ስርጭትን ያቀናጀ፣ አመኔታ ባለው የመረጃ ልውውጥ ሥራዓት ላይ የተመረኮዘ፣ የመንግስትንና የሌሎች ግብዓት አቅራቢዎችን ሚና የለየ እንዲሁም በኢንፎርሜሽን ግንኙነት ቴክኖሎጂ የተደገፈ የግብዓት ፍላጎት፣ ምርትና አቅርቦት መከታተል የሚያስችል እና ለሁሉም ባለድርሻ አካላት በቀላሉ ተደራሽ የሆነ ስርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል።

### የፖሊሲው አቅጣጫው

- የተቀናጀ የግብዓት ግብዓቶች ፍላጎት፣ ምርትና አቅርቦት መከታተያ ሁሉንም ግብዓቶች ተጠቃሚዎች (ሰፋፊ ግብርና አልሚዎችን ጨምሮ)፣ አምራቾች እና አቅራቢዎችን በባካተተ እና የኢንፎርሜሽን ግንኙነት ቴክኖሎጂ የተደገፈ ሆኖ ይገነባል።

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የግብርና ግብዓቶች ፍላጎት፣ ምርት እና አቅርቦት መከታተያ አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ መዋቅራዊ አደረጃጀትና መሰረተ ልማት ይገነባል።

## 5.3 የውሃ አጠቃቀም እና አስተዳደር

ሀገራችን ወደ 122 ቢሊዮን ሜትር ኩብ የሚደርስ የውሃ ሃብትና 11.1 ሚሊዮን ሄክታር የሚሆን በመስኖ መልማት የሚችል የእርሻ መሬት እንዳላት ይታመናል። ይህን እምቅ የውሃና የመሬት ሀብት በማልማት ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ ከውጭ የሚገቡ የግብርና ምርቶች እና ግብዓቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት እና የአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖን ለመቋቋም ውሃ ዋነኛና የተለየ ግብዓት ነው። ይህም ከዝናብ፣ ሃይቅና ወንዝ ከመሳሰሉ በመሬት ገፀ ምድር የሚገኙ የተፈጥሮ የውሃ አካላት እና በከርሰ-ምድር የሚገኝን ውሃ በዘላቂነት መጠቀም ይጠይቃል። በተለይም የመስኖ መሠረተ ልማቶች የአገልግሎት ዘመናቸውን ለማራዘም እና ውጤታማነታቸውን ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ እንዲቀርፁ እንዲሁም የአጠቃቀምና አስተዳደር የተሟላ የፖሊሲ ማዕቀፍ እና የተጠናከረ ተቋማዊ አደረጃጀት አስፈላጊ ነው።

### 5.3.1 የግብርና ውሃ አያያዝና አጠቃቀም

በዝናብ ላይ ተወስኖ በአመት አንድ ጊዜ ብቻ ማምረት በፍጥነት እያደገ ላለው የህዝብ ቁጥር የሚያስፈልገውን የምግብ ፍላጎት ለማሟላት እንዲሁም በየጊዜው የሚከሰተውን የአየር ንብረት ለውጥ የሚቋቋም ግብርናን ለመፍጠር ዘላቂነት ያለው የመስኖ ልማት እና የግብርና ውሃ አጠቃቀም ማሻሻል ቁልፍ ጉዳይ ነው። ይህንን በመገንዘብ መንግሥት ዘላቂ የውሃ አጠቃቀምን መሠረት በማድረግ የእርሻ አሠራርን ማጎልበት አስፈላጊነትን፣ ዘርፈ ብዙ የልማት ፓኬጆች እና የውሀ እቀባና ውሃ ማሰባሰብ አስፈላጊነትን በተለያዩ ስትራቴጅዎቹ አመላክቷል። እነዚህንም መሰረት በማድረግ ባለፉት አመታት የመስኖ ልማትን ለማስፋፋት ከፍተኛ መዋለ ንዋይ በማፈሰስ ከሃያ ዓመት በፊት ከነበረበት 300,000 ወደ 1.2 ሚሊዮን ሄክታር ሽፋን በማሳደግ ተጠቃሚው ማህበረሰብ ከዝናብ ጥገኝነት እንዲላቀቅ ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

ሆኖም ግን ነባሩ ፖሊሲ ሁሉንም የውሃ አማራጮች ታሳቢ ያደረገ አልነበረም። በመስኖ የለማው መሬት መልማት ከሚችለው መሬት 11 በመቶ ብቻ ነው። በሀገራችን የከርሰ-ምድር ውሃ አለኝታ በአማካይ ከ36 እስከ 58 ቢ.ኪ.ሜ የሚደርስ ታዳሽ የከርሰ-ምድር ውሃ ክምችት እንዳለ ጥናቶች ይጠቁማሉ። በዚህም ሀብት ከ3.6 እስከ 5.8 ሚ/ሄክታር በተለያዩ የቴክኖሎጂ አማራጮች ለማልማት እንደሚቻልና በርካታ ማህበረሰቦችን ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል። ይህንን እምቅ ሃብት ሥራ ላይ ለማዋል ደጋፊ የሆነ ፖሊሲና ስትራቴጂ በመቅረፅ እና ስርዓት በመዘርጋት ዘመኑ የደረሰባቸውን ቴክኖሎጂዎች በስፋት በመጠቀም ግብርናውን ከዝናብ ጥገኝነት በማላቀቅ የመስኖ እርሻን በማስፋፋት ምርትና ምርታማነትን በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደግ ይቻላል። ሆኖም ግን የአካባቢው ሥርዓተ-ምህዳር መሠረት ያደረገ የግብርና ውሃ ምርምር ደካማ መሆኑና የልማት የኤክስቴንሽንና ምክር አገልግሎት አለመቀናጀት የቴክኖሎጅና የተሻሻለ የግብርና ውሃ አሠራር ስርፀት ደካማ አድርጎታል።

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የግብርና ውሃ አጠቃቀምና አስተዳደር የገፀ ምድር፣ ዝናብና ከርሰ ምድር ውሃ ምንጮች ተገቢውን ትኩረት በሰጠ ሁኔታ እንዲለማ ይደረጋል፣
- የዝናብ ውሃ አሰባሰብና አጠቃቀም እንደዋና የውሃ አቅርቦት አማራጭ ተደርጎ በትኩረት ይሰራል፣ የውሃው ምንጭ በሆኑ ተፋሰሶች ልማት ጋር በቅንጅት እንዲሰራ ይደረጋል፣
- የከርሰ-ምድር ውሃ ልማትና አጠቃቀም ሌላኛው የውሃ አቅርቦት አማራጭ ተደርጎ በትኩረት ይሰራል፣ የውሃው ምንጭ በሆኑ ተፋሰሶች ልማት ጋር በቅንጅት እንዲሰራ ይደረጋል፣
- የግብርና ውሃ አጠቃቀም የአሳ ልማትን እንዲደግፉ ይደረጋል፣
- ሰው ሰራሽ የግብርና ውሃ (Cloud Seeding ጨምሮ) ቴክኖሎጂ አጠቃቀም በተለይ በቆላማ አካባቢዎች ለማስፋት የድጋፍና የልማት ፕሮግራም ይዘረጋል፣
- የግብርና ውሃ አያያዝ ውሃና ኃይል ማቅረቢና ቆጣቢ ቴክኖሎጅዎችን አቅርቦት የሚያበረታታ እንዲሆን ይደረጋል፣ የምርምርና ኤክስቴሽን አገልግሎት በትኩረት ይቀርባል።

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የግብርና ውሃ አጠቃቀምና አስተዳደር ስትራቴጂ (ለሁሉም የውሃ ምንጮች) ይነደፋል፣ የህግ ማዕቀፍ ይወጣል፣ የአሰራር ስርዓትና የተቀናጀ ተቋማዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣
- የግብርና ውሃ ምንጭ በሆኑ ተፋሰሶች ልማት ላይ ውሃ ተጠቃሚዎች ተሳታፊ የሚሆኑበት ወይም የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍሉ የሚያስገድድ የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል።

## 5.3.2 የመስኖ አስተዳደር

የመስኖ አቅምችንን በፍጥነትና በዘላቂነት ተጠቅሞ ግብርናውን በአመት ከአንድ ጊዜ በላይ ማምረት እንዲቻል የመስኖ መሰረተ ልማት ከማስፋፋት ባልተናነስ ሁኔታ የተዘረጉትን መስኖ አውታሮች በአግባቡ ማስተዳደር አሰፈላጊ ነው። የመስኖ ልማት ለማስፋፋት ከፍተኛ መዋለ ንዋይ የሚጠይቅ ሲሆን ልማቱ ለሃገራዊ ኢኮኖሚ ካለው ከፍተኛ ሚና አንፃር የተለያዩ የፋይናንስ ምንጮችን ማስፋትና በአግባቡ መጠቀም ወሳኝ ነው።

የመስኖ አውታር ግንባታ ውስን ከመሆኑም በላይ የተገነቡትም የመስኖ አውታሮች የጥናት፣ ዲዛይንና ግንባታ እንዲሁም የውል አስተዳደር ሥራዎች የሚጠበቀውን ጥራት የማያሟሉና በታቀደላቸው ጊዜ ባለመጠናቀቃቸው ለተጨማሪ ወጪ በመዳረጋቸው የመስኖ ግብርና ውጤታማ እንዳይሆን አድርገዋል። የመስኖ ልማትና አስተዳደር በየጊዜው የሚለዋወጥ ተቋማዊ አደረጃጀት የተነሳ የመስኖ አውታሮችን አስተዳደር በተቀናጀ ሁኔታ ለመምራት አልተቻለም። የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበራት የአደረጃጀት እና የቴክኒክ ድጋፍ አሰራር ስርዓት ወጥ ያለሆነና ያለተቀናጀ በመሆኑ ማህበራቶቹን ውጤታማ እንዳይሆኑ አድርጓቸዋል። ለመስኖ አውታሮች ግንባታ ወጪ መተኪያ እና የውሃ ክፍያ ስርዓት አለመኖሩ የአውታሮች ጥገናና አስተዳደደርን ደካማ አድርጎቷል። የመስኖ ግብርና ከገበያ ጋር ያለው ትስስር በጣም ደካማ መሆኑ ትርፋማነቱን ዝቅተኛ ሆኗል። የመስኖ አሰራር የክትትልና የግምገማ ስርዓት እንዲሁም የመረጃ ፍሰቱ ዘለቄታዊ በሆነ መልኩ ባለመዘርጋቱ የተገነቡት የመስኖ አውታሮችን ገምግሞ የሚጋጥሙ ችግሮችን በወቅቱና በተገቢው መፍታት አለመቻል ዘለቄታዊ አገልግሎት እንዳይሰጡ አድርጓል። የአካባቢው ሥርዓተ-ምህዳር መሠረተ ያደረገ

የመስኖ ምርምር ደካማ መሆኑና የመስኖ ልማት የኤክስቴንሽንና ምክር አገልግሎት አለመቀናጀት የቴክኖሎጅና የተሻሻለ አሠራር ስርፀት ደካማ አድርጎታል።

በሌላ በኩል በሀገራችን የመስኖ ልማት በዋነኝነት ከመንግስት በሚመደብ በጀት እና ከልማት አጋሮች ድጋፍ ላይ የተንጠለጠለ ነው። የፋይናንስ አማራጮች እና ሃብት ማሰባሰብ አስፈላጊ ነው። ሆኖም ይህንን ለመተግበር የሚያስችል የፖሊሲ ማእቀፉ አልተዘረጋም። የልማት ዘርፉ ራሱን የቻለ የመስኖ ልማት ፈንድ ተቋም ባለመኖሩ ተለይቶ የሚታወቅበት ሀብት የማሰባሰብና የመጠቀም ስትራቴጂ የለውም። የመስኖ ልማት ላይ በተለያዩ ተቋማት መካከል ግልፅ ያልሆነ የተግባርና ሃላፊነት መደራረብና ሚና አለመለየት እንዲሁም ቅንጅታዊ አሰራር አናሳ መሆን ነው። የመስኖ መሠረተ ልማት ለማስተዳደርና ለመጠገን የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ለመጋራትን የሚያስችል አሰራር ሥርዓት ባለመዘርጋቱ ተጠቃሚው ማህበረሰብ መሰረተ ልማቱን እንደራሱ ሀብት ባለመመልከቱ ከመሰረተ ልማቱ በውጤታማነትና በዘላቂነት ጥቅም ላይ ማዋል ተግዳሮት ሆኖ ይግኛል።

የመስኖ አውታሮች ግንባታን የተጠቃሚውን ባለቤትነት ያልፈጠረ እና አስተዳድሩም ወጥ እና ጠንካራ ባለቤት ያልተለየለት እንዲሁም ዘላቂና ውጤታማ የመስኖ አውታሮች አሠራር ስርዓት እና ጠንካራ መዋቅራዊ አደረጃጀት ያልተዘረጋለት ነው።

በመሆኑም የግብርና ውሃ አጠቃቀም ዘላቂና ውጤታማ ለማድረግ የመስኖ መሠረተ ልማት ማስፋፋት፣ ርክክብ፣ ኦፐሬሽንና ጥገና፣ የመሠረተ ልማት ጥራትንና ምሉዕነትን የሚያረጋግጥና ከተፋሰስ ልማት ጋር የተቀናጀት የመስኖ ልማት ለማስፋፋት፣ ዘመናዊ የመስኖ ቴክሎጂዎችን ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያስችል የማበረታቻ ስርዓት አስፈላጊ ነው። የግሉ ዘርፍ በመስኖ ልማትና አያያዝ ላይ ተሳትፎ እንዲጎለብት የሚያስችል የህግ ማዕቀፍና አሰራር ስርዓት መዘርጋት አሰፈላጊ ነው። የመስኖ አውታር ጥናት፣ ዲዛይን እና ግንባታ እንዲሁም አዋጭነትና አካባቢያዊ ተስማሚነት ለማረጋገጥ አስገዳጅ የሆኑ የመስኖ ትግበራ ደረጃዎችና ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት እንዲሁም የመስኖ አውታሮችን ዘለቄታዊነት ለማሻሻል የተጠቃሚዎች የወጪ መጋራት የሚያስችል የህግ ማዕቀፍና አሰራር ስርዓት መዘርጋት ይገባል። የመስኖ መሰረተ ልማት ውጤታማነትን ለማረጋገጥ ከአዋጪ ጥናትና የዲዛይን ስራ ጀምሮ የገበያ መሰረተ ልማት፣ ስትራቴጂክ ምርቶችን

እንዲሁም ሌሎች የግብርና ልማት ደጋፊ አገልግሎቶች መካተታቸውን የሚያረጋግጥ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው።

## የፖሊሲ አቅጣጫው

- የተጠናከረ የመስኖ መሠረተ ልማት የርክክብ፣ ኦፕሬሽንና አስተዳደር እንዲኖር ይደረጋል፣ ይህም ከተፋሰስ ልማት እንዲቀናጅ ይደረጋል፣
- የመስኖ ልማትና አስተዳደር ፋይናንስ አማራጮችን እንዲሰፉ ይደረጋል፣ የግሉ ዘርፍ እና የህብረት ስራ ማህበራት የሚኖራቸው ሚና እንዲያድግ ይደረጋል፣
- የመስኖ ተጠቃሚዎች የአውታሩን አስተዳዳራዊ ወጪ እንዲጋሩ ይደረጋል፣
- የባለአነስተኛ ይዞታ የመስኖ ልማት ፈንድ እንዲቋቋም ይደረጋል፣
- የሁሉንም አይነት መስኖ አውታሮች ልማት አስተዳደርና አጠቃቀም የሚመራ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ተቋማዊ አደረጃጀት ይገነባል።

## የማስፈፀሚያ ስልቶች

- የመስኖ መሠረተ ልማቶችን ርክክብ፣ ኦፕሬሽንና አስተዳደር የሚደነግግ የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓትና የተቀናጀ ተቋማዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣
- የመስኖ ልማትና አስተዳደር ፋይናንስ አማራጮችን (የግሉን ዘርፍና የህብረት ስራ ማህበራትን ሚና እና የመንግስትና የግል አጋርነት ጨምሮ) የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የመስኖ ተጠቃሚዎች የወጪ መጋራት የሚወስን የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የአስራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የመስኖ ልማት ፈንድ የሚያቋቁም የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ አስራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የመስኖ ውሀ ተጠቃሚዎች ማህበር ማቋቋሚያ የህግ ማዕቀፍ የሁሉንም አይነት መስኖ አውታሮች አስተዳደርና አጠቃቀም ባካተተ መልኩ ይሻሻላል።

## 5.4 የምርት ግብይት

በገበያ የተመራ ግብርና ልማት የግብርና ስራን እንደ ቢዝነስ ተግባር የማጤን እና አምራቾች የምርት ስራን ከመጀመራቸው አስቀድሞ ገበያን የማወቅ፣ ምን አይነት ምርት፣ በምን መጠን እና መች፣ በምን አይነት የጥራት ደረጃ እንደሚፈለግ አውቆ ለማምረት ያስችላል። ይህም የገበያ ስርዓት የበለጠ መዋቅራዊ፣ በእዉቀትና በመረጃ ላይ የተመረኮዘ እና ግልጽ እንዲሆን የሚረዳ በመሆኑ አምራቹ በምርቱ መሸጫ ዋጋ ላይ የውሳኔ ሰጭነት ሚና እንዲኖረው በማድረግ ለሚያመርተው ምርት የተሻለ የገበያ ዋጋ እና ገቢ ያስገኛል። የግብይት ስርዓት በቀጣይነት ለማሻሻልና ለማጠናከር የሀገር ውስጥ ምርት ግብይት፣ የወጪ ንግድ እና የገቢ ምርቶችን በሃገር ውስጥ ምርት መተካት የገበያ አሰራር እና የህብረት ስራ ማህበራትን ማዘመን የተሟላ የፖሊሲ ማዕቀፍ መዘርጋት ያስፈልጋል።

### 5.4.1 የሀገር ውስጥ ምርት ግብይት አሰራር ስርዓት

ቀልጣፋ፣ ተደራሽና ፍትሀዊ የሆነ የግብርና ምርት ግብይት ሥርዓት ማስፈን አነስተኛ አርሶና አርብቶ አደሮች ትርፋማ ወደ ሆኑ አመራረቶችና ምርቶች እንዲሸጋገሩና የኑሮው ደረጃው እንዲሻሻል ያደርጋል። ሸማቹም ጥራት ያላቸውን ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኝ ያግዛል። በተጨማሪም ጥራቱን የጠበቀና ቀጣይነት ያለው ምርት ለወጪ ንግድ ለማቅረብ ይረዳል።

የምርት ግብይት የአሰራር ስርዓት በተሟላ መልኩ ባለመዘርጋቱ የግብይት ሰንሰለቱ እሴት በማይጨምሩ ተዋንያን በመበራከታቸው ከፍተኛ የግብርና ምርት ዋጋ መዋዠቅ እያስከተለ ይገኛል። የምርት አቅርቦትና ጥራት አስተማማኝ አለመሆን ምርት ለማቀነባበር በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የተገነቡ ኢንዱስትሪዎችም አስፈላጊውን የግብርና ምርት ስለማያገኙ ከአቅማቸው በታች ለማምረት ይገደዳሉ።

የግብርና ምርቶች ግብይት የህግ ማእቀፎች እና አሰራር ስርዓት አምራቹን ተገቢውን የገበያ ዋጋ እንዲያገኝ አላስቻሉም። የተወሰኑም የግብርና ምርቶችንም አምራቹ ከማምረቻና ተዛማጅ ወጪዎች በታች እንዲሸጥ አስገድዶታል። የገበያ ቁጥጥር ስርዓት የተሟላ አለመሆኑ የጥራት ደረጃዎችን፣ የምርት ዱካንና የምግብ ደህንነትን፣ የተዋንያን የግብይት አሰራር ሁኔታ፣ የምርትና ገንዘብ ልውውጥ እንዲሁም ምርት

ትራንስፖርት አገልግሎት የተቀላጠፈ አለመሆን የግብርና ምርት ግብይትን እንዳይዘምን አድርጓታል።

ገበያ ማረጋጋት አንዱ ተልዕኮአቸው የሆኑት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ባለባቸው የአመራርና አስተዳደር ድክመት እንዲሁም ከመንግሥት፣ ከፋይናንስ ዘርፍና ሌሎች አካላት ጋር ያላቸው ግንኙነት ጠንካራ ባለመሆኑ ምክንያት በምርት ግብይት ያላቸው ሚና ዝቅተኛ ነው።

የግብይት ፋይናንስና ስጋት ሽፋን መድን የተሟላ አለመሆን፣ የግብርና ምርትን በማሰባሰብ፣ በማከማቸት እና ጥራቱን በመጠበቅ ቀጣይነት ያለው የምርት አቅርቦት ለማከናወን ከፍተኛ የሆነ የመግዣ እና የመሰረተ ልማት ፋይናንስ አቅርቦት እጥረት ሌላው የግብርና ምርት ግብይት አሰራር ላይ ያለ ክፍተት ነው።

## የፖሊሲ አቅጣጫው

- የግብርና ምርቶች ግብይት የምርት አይነትና የገበያ መዋቅርን በለየ፣ እሴት ሰንሰለቱን በተከተለ እና የጥራትና ድህረ ምርት ብክነት መቀነስ እንዲያስችል ሆኖ ይገነባል፣
- የምርት ግብይት በጥራት ደረጃ ላይ የተመሰረተ የዋጋ ትመና እንዲሰፍን ይደረጋል፣ የገበያ መረጃ አቅርቦት እና ዘመናዊ የክፍያ ስርዓት እንዲሁም ኤሌክትሮኒክ ግብይት፣ ዘመናዊ የግብይት መድረኮችንና አገልግሎቶች ይገነባል፣
- የምርት የመሸጫ ዋጋ የማምረቻና ተዛማጅ ወጪዎችን የሚመልስ እንዲሆን በጥናት በሚመረጡ የግብርና ምርቶች በጊዜ የተገደበና ከገበያ መርሆች ጋር በተጣጣመ መልኩ ለአምራቾች ዝቅተኛ የምርት ዋጋ ድጋፍ ይደረጋል፣
- የግብርና ምርት በውል የሸጠ ማምረት፣ በመጋዘን ደረሰኝ ስርዓት፣ ፎርዋርድ ውል (forward contract) እና ፊውቸር ገበያ (futures market) እንዲመሰረት ይደረጋል።

## የማስፈፀሚያ ስልቶች

- የሀገር ውስጥ የግብርና ምርቶች የግብይት ህግ ማእቀፎች እና የአሰራር ስርዓቶችን በመፈተሽ ይበልጥ ልማቱን እንዲደግፉና አምራቹን እንዲያበረታቱ ተደርገው ይሻሻላሉ፣

- ለተመርጡ የግብርና ምርቶች በገበያ ፍላጎትና አቅርቦት እንዲመሰረትና ቀልጣፋ የእሴት ሰንሰለት ግንባታ ተገቢ የሆኑ የጅምላና የችርቻሮ መዋቅሮች የሚቀርጽ፣ የግል፣ የመንግሥትና የህብረት ሥራ ማህበራትን ሚና የሚለይ፣ ዘመናዊ የግብይት መድረኮችንና ሂደቶችን ሥራ የሚዘረጋ የገበያ መር ግብርና ልማት ስትራቴጂ ይነደፋል፣ የተቀናጀ መዋቅራዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣
- የድህረ ምርት ብክነት ስትራቴጂ ሁሉንም የግብርና ምርቶችን ባካተተ መልኩ ይሻሻል፣
- በመንግሥት መሪነት ወይም ድጋፍ የሚገነቡ የግብይት መድረኮችን እና የአደጋ ስጋትን አስተዳደር ስርዓት ሁሉንም የግብርና ምርቶችን ባካተተ መልኩ ይዘረጋል፣
- የውል ግብርና፣ የመጋዘን ደረሰኝ፣ ፎርዋርድ ውል እና ፊውቸር ገበያ አሰራርን የሚደግፍ የተሟላ የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣

### 4.4.2 የኅብረት ሥራ ማህበራት

የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች እና ቴክኖሎጅዎች አቅርቦትና ስርጭት፣ የሀገር ውስጥ እና የወጪ ንግድ ምርቶች ግብይት፣ በግብርና ምርቶች ላይ እሴት የመጨመር ተግባራት፣ የግብርና ሜካናይዜሽን አቅርቦትና አገልግሎት፣ የቁጠባና ብድር አገልግሎቶችን የማቅረብ ተግባራትን በማከናወን ለግብርናው ልማትና ግብይት ከሚሰጧቸው አገልግሎቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

አርሶና አርብቶ አደሮችን በማደራጀት ምርቶቻቸውን በማሰባሰብና በማከማቸት የመጋዘን አገልግሎት እንዲሁም የምርት ደረጃ መለየትና ማሸግ አገልግሎት በመስጠት ጥራቱን የጠበቀ ምርት እንዲያመርቱ፣ አላስፈላጊ የገበያ ሰንሰለትን በማሳጣር የተሻለ ዋጋ አንዲያገኙና ኑራቸው እንዲሻሻል ማድረግ ያስፈልጋል። ሆኖም የኅብረት ሥራ ማህበራት አመራርና አስተዳደር ስርዓት፣ ማህበራቱ በነፃ ገበያ ስርዓት ውስጥ መወዳደር የሚያስችል፣ አማራጭ የፋይናንስ አቅርቦት እና ኢንቨስትመንት የሚያመቻች እና የኦዲት፣ የኢንስፔክሽን እና የብቃት እውቅና ደረጃ አሰጣጥ በተሟላ የፖሊሲ ማዕቀፍ እና አሰራር ስርዓት አልተደገፍም።

የኅብረት ሥራ ማህበራት በሀገር ውስጥ የግብርና ምርቶች የግብይት ድርሻ 15 በመቶ ብቻ መሆኑ፣ በወጪ ንግድ ላይ ያላቸው ድርሻ በመጠን ከ4 እስክ 5 ከመቶ አለመብለጡ እንዲሁም የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን እና የፍጆታ ምርቶችን

ከውጪ በጅምላ ለማስገባት በቂ አቅም አልመፍጠራቸው በዘርፉ ላይ ያላቸው ተሳትፎ በሚፈለገው ደረጃ አለማደጉን ያመላክታል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራቶቹ በተሳተፉባቸው የግብርና እና የፍጆታ ምርቶች አቅርቦት ላይ የመጠን፣ የጥራት እና የወቅታዊነት ጉድለቶች ታይቶባቸዋል፡፡ ለዚህም ምክንያቶቹም ውጤታመነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ተሟላ የአሰራር ስርዓት እና በበቂ መሰረተ-ልማት አልመዘርጋት ናቸው፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራትን አዋጭነት ባለው መልኩ፣ ያለ በቂ ግንዛቤና ፈቃደኝነት አለማደራጀት፣ የአደረጃጀትና አመዘጋገብ ስርዓት ወጥ አለመሆን፣ እንቅስቃሴውን የሚመራ ጠንካራ አደረጃጀት አለመኖር ጠንካራ እና ውጤታማ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት መስጠት ያልቻሉ የኅብረት ሥራ ማህበራትን በመዋሃድ መልሶ አለማደራጀት የአገልግሎት አሰጣጣቸው እንዳይዘምንና እንዳይጠናከር ማነቆ ሆኗል፡፡

### የፖሊሲ አቅጣጫው

- የኅብረት ሥራ ማህበራትን ገለልተኛነታቸውን ከሚጻረር የውጭ አካል ተጽዕኖ ተላቅቀው በነፃ ገበያ ስርዓት ውስጥ ይበልጥ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ይደረጋል፣ የአመራር፣ ቁጥጥርና ቅጥር ባለሙያዎች ተግባርና ሃላፊነት በለየ ሁኔታ አስተዳደራቸው በቅጥር ባለሙያዎች ይመራሉ፣
- የኅብረት ሥራ ማህበራትን ይበልጥ ተወዳዳሪ ለማድረግ የማዋሃድ ወይም የመሰብሰብ አማራጭን እንዲከተሉ ይደረጋል፣
- የኅብረት ሥራ ማህበራት በግብርና ግብዓትና አገልግሎት፣ ምርት ገበያ ፣ እሴት ጭመራ፣ ብደርና ቁጠባ እና መሰረት ልማት አቅርቦት በሰፊው በጥራትና ተወዳዳሪነት በላው መልኩ እንዲያቀርቡ ተገቢው ድጋፍ ይደረጋል፣
- የኅብረት ሥራ ማህበራት ኢንቨስትመንትን ለማስፋት የሚያስችል አማራጭ የፋይናንስ ምንጮች እንዲጠቀሙ ይደረጋል፣
- የኦዲት፣ የኢንስፔክሽን እና የብቃት እውቅና ደረጃ አሰጣጥ ይጠናከራል፡፡

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የህብረት ስራ ማህበራት የፖሊስ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የህግ ማዕቀፍ ይሻሻላል፣ ጠንካራ ተቋማዊ አደረጃጀትና ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

### 5.4.3 የወጪ ንግድ

የግብርና ምርቶች የወጪ ንግድ ለሀገራችን ዋነኛ የውጪ ምንዛሪ ምንጭ ከመሆናቸውም ባሻገር ግብርናን ገበያ መር እንዲሆን ማስቻል እና በእሴት ሰንሰለቱ ዉስጥ ሰፊ የስራ እድል በመፍጠር ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ ነባሩ ፖሊሲ በገበያ በተለይም በአለም ገበያ የሚመራ የግብርና ልማት የፖሊሲ አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡ የወጪ ንግድን ለማበረታታት የግብርና የቀረጥ እፎይታ፣ የብድር አቅርቦትና አነስተኛ የወለድ ምጣኔ፣ የዉጪ ምንዛሬ አቅርቦት እና ለአልሚዎች መሬትን በዝቅተኛ የሊዝ ዋጋ ማግኘት እንዲችሉ በማድረግ በርካታ የማበረታቻ ዕርምጃዎችን መንግስት ወስዷል፡፡ በመሆኑም ግብርና ምርቶች የወጪ ንግድ ገቢ እድገት አሳይቷል፡፡ የተገኘው ዕድገት እንደተጠበቀ ሆኖ የግብርና ምርቶች የወጪ ንግድ ከአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ያለው ድርሻ ሲታይ በጣም አነስተኛ ነው፡፡

የግብርና የወጪ ምርቶች ልማት እና ንግድ የፖሊሲ ማዕቀፍ የወጪ ንግዱን የምርት አቅርቦት መጠንና ዓይነት የሚለይ፣ ለጥራትና ዕሴት ጭመራ ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ፣ የገበያ ማስፋፊያ ስራዎችን ለማከናወን፣ የመዳረሻ ገበያዎችን ለማስፋትና የዋጋ ተወዳዳሪነትን ለማሳዳግ የሚያስችል የተሟላ የህግ ማዕቀፍና አሰራር ስርዓት አልተዘረጋም፡፡ በመሆኑም የገዢ ሀገሮችን የተለያዩ የጥራት እና ደህንነት መስፈርቶችን ለይቶ አለመዘጋጀት፣ የዓለም ዓቀፍ ገበያን መሰረት ያደረገ የምርት ትንበያ መረጃ ስርዓት አለመኖር፣ በንግድ ድርድር የተገኙ እንዲሁም በሀገራትና አህጉራት ችሮታ የተሰጡ የገበያ እድሎችን አሟጦ አለመጠቀም፣ ምርቶቻችን ብራንድ አለመደረቻቸው ከግብርና ወጪ ንግድ ሊገኝ ይችል የነበረውን የበለጠ ውጭ ምንዛሬ አልተገኘም፡፡

የሆርቲካልቸር የወጪ ንግድ መጠን ለማሳደግ ከአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች ምርት ለማሰባሰብ (ኮንሶሊዴሽን) የሚያስችል አሰራር ስርዓት ተግባራዊ አልተደረገም፡፡ በተጨማሪም ለሆርቲካልቸር ምርት አሰባሳቢዎች (አምራቾችና ዩኒየኖች)

ኤክስፖርት በሚደረገው ምርት ላይ ተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ የሚጠይቅ በመሆኑ አነስተኛ አርሶ አደሮች ለወጪ ንግድ አቅርቦት ተሳትፎን እየገደበ ይገኛል፡፡

የግብርና ምርቶች ከሀገር እንዳይወጡ እገዳ ለማጣል መነሻ የሚሆኑ ኢኮኖሚያዊና የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፡፡ ሆኖም ግን እገዳ የሚጣልበትና የሚነሳበትን ግልፅና ተገማች አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ እያለ አሁን ባለው አሰራር ግን እገዳ ከመጣሉ በፊት አምራቾችና የገበያ ተዋናዮች እና ከመንግስት አካላት ጋር የሚደረግ በቂ ውይይት አለመኖሩ እንዲሁም የእገዳ ውሳኔ ከተወሰነ በሃላ በውሳኔው ሊጎዱ የሚችሉ ባለድርሻ አካላት ውሳኔውን ሊያውቁ የሚችሉበት ግልፅ አሰራር አልተዘረጋም፡፡

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የግብርና ወጪ ምርቶች ልማት እና ንግድ የምርት አይነትና መጠን፣ የማዳረሻ ገበያ ፍላጎት (የደን መጨፍጨፍና መራቆትን የተከላከለ የግብርና ምርት ስርዓት የሚጠይቁትን ጨምሮ) ፣ ጥራትና በዋጋ ተወዳዳሪ የለየና እሴት ሰንሰልቱን የተከተለ ሆኖ ይገነባል፣
- የግብርና ምርቶች ከሀገር እንዳይወጡ የሚወሰንበት አሰራር ስርዓት ግልፅና ተገማች እንዲሆን ይደረጋል፣
- ከባቢያዊ፣ አህጉራዊና አለማቀፋዊ ስምምነቶች የሚከፍቱትን የገበያ እድል በበለጠ ለመጠቀም የግብርና ምርቶች የወጪ ንግድ ለማሳደግ ይሰራል፣
- የግብርና ወጪ ምርቶች ልማት እና ንግድ አቀናጅቶ የሚመራ ጠንካራ ተቋማዊ አደረጃጀት ይገነባል፡፡

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የወጪ ንግድ ምርቶች ልማትና ግብይት ስትራቴጂ ይነደፋል፣ የልማት ፕሮግራምና የማበረታቻ ስርዓት ይዘረጋል፣ የተቀናጀ መዋቅራዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣
- የግብርና ምርቶች ከሀገር እንዳይወጡ የሚከለከሉበት የሚገዛ የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ አሰራሩን ግልፅና ተገማች የሚያደርግ መልኩ ይሻሻላል፣
- ከባቢያዊ፣ አህጉራዊና አለማቀፋዊ ስምምነቶች የሚከፍቱትን የገበያ እድል በበለጠ ለመጠቀም የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

### 5.4.4 ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት

ሀገራዊ የምግብ ፍላጎትን ለማሟላት በግብርና ዘርፍ ላይ ትኩረት በማድረግ ዋና ዋና የምግብ ሰብሎችና የእንስሳት ውጤቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት በምግብ ራስን በመቻል ሀገራዊ የምግብ ሉአላዊነት ለማረጋገጥ ያስችላል፡፡ በተጨማሪ የውጪ ምንዛሬ ለማዳንና የምግብ ዋጋ ንረትን ለመቀነስ ይረዳል፡፡ ሆኖም ግን  የነባሩ ፖሊሲ ትኩረት የነበረው የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ እና ከምግብ ተመፅዋችነት መላቀቅ ቢሆንም የሀገር ውስጥ የምግብ ፍላጎትን ለሟሟላት የሚያስችል የምርት አቅርቦትና ፍላጎት ሚዛን ተከተሎ በተመረጡ ምርቶች እሴት ሰንሰለትን የተከተለ የአጭርና የረጅም ጊዜ የልማት መርሀ ግብር ለመተግበር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት አልተዘረጋም፡፡

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- ከውጪ የሚገቡ የግብርና ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት የምርት አቅርቦትና ፍላጎት ሚዛንን መሰረት በማድረግ የምርቶቹን እሴት ስንሰልት የተከተለ እና ለተወዳዳሪነት ተገቢውን ትኩረት የሰጠ ሆኖ ይገነባል፡፡

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- ከውጪ የሚገቡ የግብርና ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት በተመረጡ የምርቶች እሴት ሰንሰለት ስትራቴጂ ይነደፋል፣ የድጋፍና የማበረታቻ ስርዓት ይዘረጋል፣ የልማት ፕሮግራሞች ይነደፉሉ፣ መዋቅራዊ አደረጃጀት ይገነባል፡፡

## 5.5 የገጠር ኢኮኖሚ ልማት

### 5.5.1 የገጠር ልማትና ትራንስፎርሜሽን

በሀገራችን የገጠሩ ነዋሪ 78 በመቶ የሚሆነውን ህዝብ የሚይዝ ሲሆን የኑሮው መሰረቱ ግብርና ነው፡፡ ይህንን በመገንዘብ የገጠር ልማት ፖሊሲው ግብርናን ማእከል ያደረገ ልማት የገጠር ህዝብ ከድህነት ማላቀቅና ከልማቱ ተጠቃሚነት እንዲያረጋግጥ በማድረግ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ኢኮኖሚያዊ እድገት የማምጣት አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡ በተጨማሪም ከግብርና ውጪ ያሉ የገጠር ልማት እንቅስቃሴዎችን ማጠናከር (የገጠርና ከተሞች ትስስርን ጨምሮ) እና የተቀናጀ የገጠር መሰረት ልማትን

ማስፋፋት አቅጣጫ አስቀምጧል። ይህንኑ የፖሊሲ አቅጣጫ መሰረት በማድረግ ተከታታይ የልማት እቅዶች በመተግበር እና ከፍተኛ መዋለ ንዋይ በማፍሰር በገጠር የድህነት መጠን ቀንሷል።

ሆኖም ግብርና ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት አሳክቶ ከግብርናው ዘርፍ የመነጨውን ሀብት ለገጠር ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር መፈጠር የሚያስችል ግብርናን ከሌሎች ኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ማስተሳሰርን፣ በገጠር ከግብርና ውጪ ያሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች (የገጠር ኢንዱስትሪ ልማት፣ የማምረቻ እና አገልጎሎት ዘርፎችን ጨምሮ) ማስፋትን፣ የገጠርና ከተሞች ትስስርን ጨምሮ እና የተቀናጀ የገጠር መሠረተ-ልማቶችንና አገልግሎቶን ማስፋፋትን የሚያስችል የፖሊሲ አቅጣጫ አልተቀመጠም። ይህንንም የሚያስተባብርና የሚመራ ተቋማዊ አደረጃጀትም በተሟላ መልኩ አልተዘረጋም።

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የገጠር ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር ለማሳካት ግብርናን ከሌሎች ኢኮኖሚ ዘርፎች እንዲተሳሰር፣ በገጠር ከግብርና ውጪ ያሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች የግብርና መዋቅራዊ ሽግግር እንዲያግዙ፣ የከተማና ገጠር ትስስር እንዲጠናከር እና የተቀናጀ የገጠር መሠረተ-ልማቶችንና አገልግሎቶችን እንዲስፋፉ ይደረጋል፣ ይህንንም የሚያስተባብር መዋቅር ይሰየማል።

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- ግብርናን ከሌሎች ኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር የሚያስተሳስር እና በገጠር ከግብርና ውጪ ያሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ማስፋፊያ እንዲሁም የተቀናጀ የገጠር መሠረተ-ልማቶችንና አገልግሎቶን ማስፋፊያ ስትራቴጂ ይነደፋል፣ የልማት ፕሮግራሞች ይተገበራሉ፣
- ወረዳን ማዕከል ያደረገ ዘርፈ ብዙና የተቀናጀ የገጠር ልማትና ትራንስፎርሜሽን የሚደግፍ የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የገጠር ልማትና ትራንስፎርሜሽን የሚያስተባብር መዋቅራዊ አደረጃጀት ይሰየማል።

### 5.5.2 በገጠር የወጣቶች ስራ እድል ፈጠራ

በሀገራችን በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ የመጣውን የወጣት ቁጥር በአግባቡ በእውቀትና ክህሎት ማብቃት ለኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር የሚያስፈልግውን የበቃ የሰው ሃይል ለማቅረብ ቁልፍ ጉዳይ ነው። ይህንን በመገንዘብ መንግስት የተያዩ የፖሊሲ ማዕቀፍችን በመዘርጋት ወጣቱ በማህበራዊ፣ ፖሊቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ በመጠናከር ከውጤቱም ተጠቃሚ እንዲሆን የማስቻል አቅጣጫ አስቀምጧል። የአቅጣጫውም ትኩረት የነበረው የወጣት ስራ እድል ፈጠራ ሲሆን ይህንንም መንግስት አስቻይ ሁኔታና ድጋፍ በማመቻቸት ወጣቱ በራሱ እና የግሉ ዘርፍ ስራ እንዲፈጥር ነው። ይህ ታሳቢ ያደረገው የግብርና ዘርፍ እያደገና እየዘመነ ሲሄድ ቴክኖሎጂና አገልግሎቶችን በሰፊው የሚጠቀም እንደሚሆናን በገጠር ከግብርና ውጪ ያሉ የኢኮኖሚ ዘርፎች ስለሚያሳድጉ የሰለጠነ ወጣትን መሳብና በብዛት መቅጠር እንደሚችሉ ነው።

ሆኖም ባለፉት አመታት በሀገራችን ከፍተኛ የሆነ የግብርና እድገት ቢመዘገብም ይህን ነው የሚባል የቴክኖሎጂና አገልግሎት አጠቃቀም ለውጥ ባለማስከተሉ እንዲሁም በገጠር ከግብርና ውጪ ያሉ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ባለመስፋፋቱ ቁጥሩ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ የመጣውን የተማረ የገጠር ወጣት ሳቢና ቀጣሪ መሆን አልተቻለም።

የገጠር የስራ እድል ፈጠራ በተፈለገው ደረጃና ስፋት ለመተግበር የመረጃ፣ የእውቀትና የአመለካከት ችግሮች፣ የግብርና ሙያ በቴክኖሎጂ ባለመደገፉ በሙያው ለመሰማራት ያለው ፍላጎት አነስተኛ መሆን፣ ለወጣቶች የሚደረገዉ ድጋፍ ዉስን መሆን፣ የመሬት አቅርቦት፣ የፋይናንስ አቅርቦትና አፈጻፀም ቸግሮች፤ የስልጠናና ቴክኖሎጂ ልማት አለመስፋፋት፣ የገበያ አቅርቦትና ትስስር ማነስ፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት፣ የመሠረተ-ልማት በበቂ አለመስፋፋት፣ በየደረጃው ያለ ፈፃሚና አስፈፃሚ አካላት የአቅም ውስንነት እንዲሁም በግብርና የስራ ዘርፍ ለመስራት የወጣቶች የአመለካከት ችግሮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

ከመደበኛው እንቅስቃሴ የተለየና ዘርፈ ብዙ የሆነ አዲስ አስተሳሰብና አቅጣጫ የሚጠቁም እና ስራ አጥነት የሀገሪቱ ቁልፍ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ ችግር ከመሆኑም በላይ የዜጎችን የሥራ ዕድል ጥያቄ በአግባቡ መመለስ አስፈላጊ ነው። የመሬት አቅርቦትና ተጠቃሚነት ለማሻሻል፣ ለግብርና መዘመን የሚያስፈለገውን ቴክኖሎጂና አገልግሎቶችን እንዲያቀርቡ ለማስቻል፣ በዘመናዊ ግብርና አሳታፊ እና

በገጠር ከግብርና ውጪ ያሉ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ውጤታማ ተሳትፎ ማረጋገጥ ወሳኝ ነው።

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የግብርናና የገጠር ልማቱ ወጣቱ የሚስብ እና ውጤታማ ተሳትፎ የሚያረጋግጥ እንዲሆን ይደረጋል፣
- ወጣቶች በግብርናና ገጠር ልማት ፍትሃዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ለዘርፉ እድገት የላቀ አስተዋፆዎ እንዲያበረክቱ ይደረጋል።

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የገጠር ስራ እድል ፈጠራ ስትራቴጂ ይሻሻላል፣ የድጋፍና ማበረታቻ አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ የአሰራር ስርዓትና የተቀናጀ መዋቅራዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣
- በቢዝነስ ዕሳቤ የተቃኘ የግብርና ኢንተርፕረነርሽፕ ማጎልበቻ የአሰራር ስርዓት እና ተቋማዊ አደረጃጀት ይዘረጋል።

## 5.6 መሰረተ ልማት

### 5.6.1 ግብርናን ያማከለ የመሰረት ልማት ዝርጋታ

ግብርናን ለማልማት እና የምርት ግብይቱና እሴት ጭመራ ለማሳለጥ የተቀናጀ የግብርናና ገጠር መሰረት ልማት ቁልፍ ሚና አለው። በመሆኑም መንግስት መዋለ ንዋይ በማፍሰስ የመንገድና ትራንስፖርት፣ ቴሌኮም አገልግሎት፣ ኤሌክትሪክ፣ የምርት ማቀነባበሪያ (አግሮ ኢንዱስትሪ)፣ የመስኖ አውታሮች፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ተዘርግቷል። ይህም እስከአሁን ለተመዘገበው የግብርናና ገጠር እድገት የበኩሉን አስተዋፆ አበርክቷል።

ሆኖም የመሰረተ ልማት ዝርጋታዎች የልማት አካባቢዎች የግብርና የመልማት አቅም ግምት ውስጥ በበቂ ሁኔታ ያላስገቡ፣ የተገነቡትም በበቂ መጠንና በሚፈለገው ጥራት ባለመስፋፋታቸው በግብርና ልማቱን ገድበውታል። እነዚህ ውስን የመሰረት ልማት ዝርጋታዎች በመንግስት በጀት ላይ የተንጠለጠሉ እና አስተዳደሩም ወጥ እና ጠንካራ ባለቤት እንዲኖረው አልተደገረም። በዚህም ምክንያት የግብርና ምርቶች ጥራታቸው

ተጠብቆ ወደ መዳረሻ ገበያ እንዲደርሱ የሚያስችሉ የማቀዝቀዣ ሰንሰለት የተሟላላቸው የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አቅርቦት እጥረት፣ ዘመናዊ የእንስሳት ማጓጓዣ መኪኖች በበቂ አልቀረቡም። በመሆኑም ለሀገር ውስጥና ለወጪ ንግድ የሚቀርቡ ቁም እንስሳት በዕቃ ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች እንዲጓጓዙ መደረጉ እና ለመሰረተ ልማት ግንባታ በቂ የብድር አገልግሎት አለመመቻቸቱ ዘርፉ እንዳይዘምን ገድቦት ይገኛል። ከዚህም በተጨማሪ የግብርና ምርትና ግብዓት ማከማቻ/ማቆያና ማቀነባበሪያ፣ የግብይት ማዕከላት፣ የቅዝቃዜ ሰንሰለቱ የተሟላ መጋዘኖች በበቂ ደረጃ አለመኖር እንዲሁም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት አለመዘርጋት የምርት ብክነትና ጥራት እንዲሁም በአምራቾች፣ በተጠቃሚው እና በሀገራዊ ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያስከተለ ይገኛል።

**የፖሊሲ ማሻሻያው**

- የግብርና መሰረት ልማት ዝርጋታ (በተለይም የምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ) የግብርን ዘርፍ ልማት በተሻለ ሁኔታ እንዲደግፍ የልማት አካባቢዎች የግብርና የመልማት አቅም ግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ ይገነባል፣
- የተቀናጀ መሰረተ ልማት ለማስፋፋት የመንግስት እና የግል ዘርፍ አጋርነት ይጠናከራል፣ የግሉ ዘርፍና የህብረት ስራ ማህበራት ጉልህ ሚና እንዲኖራቸው ይደረጋል።

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የተቀናጀት መሰረት ልማት ዝርጋት ስትራቴጂ የግብርናን የመልማት አቅም ግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ ተቋማዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣
- የመንግስት እና የግል ዘርፍ አጋርነት እና የህብረት ስራ ማህበራት የመሰረተ ልማት ዝርጋታና አስተዳደር የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል።

### 5.6.2 የግብርና አገልግሎት መሰረተ ልማት

የግብርና አገልግሎት መሰረት ልማት በተለይም የቴክኖሎጂና ግብዓት ጥራት ቁጥጥር እንዲሁም የእንስሳት እና እጽዋት ጤና አጠባበቅ እና ምርት ጥራት ኳራንታይን መሰረተ ልማቶች የግብርና ቴክኖሎጂና ግብዓት እና ምርት ጥራትና ጤንነት ለመጠበቅ

ብሎም የግብርና ምርትና ምርታማነት ለመጨምር፣ የምግብ ደህንነትን ለመጠበቅ እና የወጪ ንግድ የመዳረሻ ገበያዎች የጥራት ደረጃ አሟልቶ የውጪ ምንዛሪ ግኝት ለማሳደግ ወሳኝ ሚና አለው። ይህንኑ በመገንዘብ መንግስት ባለፉት አመታት የተለያዩ የግብርና አገልግሎት መሰረተ ልማት ለማስፋፋት ጥረት እያደረገ ይገኛል።

ሆኖም የመሰረተ ልማት ዝርጋታዎች በበቂ መጠንና በሚፈለገው ጥራት ካለመስፋፋታቸው በተጨማሪ የመሰረት ልማቶቹ አገልግሎት አቅርቦት የተገልጋዮቹን ፍልጎት እና አለም አቀፍ መስፈቶችን እንዲያሟሉ የሚያስችል የተሟላ የአሰራር ስርዓት አልዘረጋም። በሌላ መልኩ እነዚህ ውስን መሰረት ልማት ዝርጋት በመንግስት በጀት ላይ የተወሰነ እና አስተዳደሩም መንግስት በመከናውኑ ምክንያት በተፈለገው መጠንና ጥራት አልተስፋፋም። የፌዴራልና እና የክልል የዕፅዋትና እንስሳት ኳራንቲን ላቦራቶሪዎች፣ መግቢያና መውጫ ኬላዎች በሚፈለግ መጠን አልተዘረጉም። ከዚህም በተጨማሪ የተሟላ የድህረ መግባት ኳራንቲን እና በመስክ ማቆያ ቦታዎችና ማስወገጃ ፋሲሊቲ፣ እንዲሁም ገቢና ወጪ ዕፅዋትና የዕፅዋት ውጤቶች ከአደገኛ ኬሚካሎች፣ አፍላቶክሲንና ሌሎች ባዕድ ነገሮች ነጻ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ የሚያስችል በሰው ሃይል የተደራጀ የተሟላ የቁጥጥር ስርዓት አልተዘረጋም።

የዕፅዋት ዘር ጥራት ቁጥጥር የተሟላ ላቦራቶሪ፣ የዝርያ መፈተሻ ሙከራ ጣቢያ ቦታዎች እንዲሁም የተሟላ አይሲቲ መሰረተ ልማት ሳይዘረጋ እየተሰራ ይገኛል። የፀረ ተባይ አስተዳደር፣ አጠቃቀም፣ ደህንነት ጥበቃ እና ስርጭት ቁጥጥር የሚያገለግሉ የደረጃቸውን የጠበቁ ፀረ ተባይ ኬሚካል መጋዘኖችና መርጫ መሳሪያዎች፣ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈባቸው ፀረ ተባይ ኬሚካል ማስወገድ የሚያስፈልጉ መሰረተ ልማት በሚፈለገው ጥራትና ብዛት አልተዘረጉም። ርጭት አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ የአውሮፕላን ማኮብኮቢያ ሜዳዎች በበቂ ሁኔታ አልተሟሉም። በተመሳሳይም የአፈር ማዳበሪያ ጥራት ቁጥጥር መሰረተ ልማት ባለመዘርጋቱ አዲስ ማዳበሪያ ለማስመዘገበና ጥቅም ላይ ማዋል አልተቻለም።

የምርት ደህንነት ለመጠበቅና ለመከላከል ከውጭ ሀገር የሚገቡና ከሀገር የሚወጡ ዕፅዋትና የዕፅዋት ውጤቶች ጥራታቸውን ጠብቀው እንዲገቡና እንዲወጡ በላብራቶሪ የታገዘ ኳራንቲን አገልግሎት ለመስጠት የሚያግዙ ላብራቶሪዎች እና የድህረ-ኳራንቲን

መሰረት ልማት ባለመሟላታቸው በሀገሪቱ ገቢ እና ወጪ ንግዱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡

ወደ ሀገር ለሚገቡ ቁም እንስሳት የጤና መቆጣጠርያ የሚሆን የኳራንቲን መሰረተ ልማት ባለመዘርጋቱ የእንስሳት ሀብት እና የማህብረሰብ ጤና ለመጤ ተላላፊ በሽታዎች አጋላጭ እንዲሆን ዳርጎታል፡፡ በሌላ በኩል የቁም እንስሳት የወጪ ንግድ ለቁጥጥር የሚያስፈልጉ የኳራንቲን መሰረተ ልማት በበቂ መጠን ባለመዘርጋታቸው እና ያሉትም የአገልግሎት ጥራት መጓደል ምክንያት በመዳረሻ ገበያ የምርት ጥራትና ደህንነት ተቀባይነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጥሯል፡፡ በተጨማሪም የእንስሳት ውጤቶች የጥራት ማረጋገጫ ለመስጠት ዕውቅና የተሰጠው ላብራቶሪ በሀገር ውስጥ ባለመኖሩ ምክንያት በውጪ ምንዛሪ ከሀገር ውጪ እንዲመረመር መደረጉ የተጠናከረ የእንስሳት የኳራንቲን አገልግሎት ለመስጠት አዳጋች ሆኗል፡፡ የወጪ ንግድ መዳረሻቸውን መካከለኛው ምስራቅ ሀገራት የሆኑ ቁም እንስሳት በትራንዚት ሀገር ማረፊያ ቦታ ባለመዘጋጀቱ ምክንያት ድጋሚ ሰርተፍኬት ተሰቷቸው እንዲላኩ መገደድ ላኪዎች ለንግልት እና ተጨማሪ ወጪ መዳረግ ባሻገር በሶስተኛ ሀገር ስም ኤክስፖርት እንዲደረግ ያደረገና ይህም ሀገራችን ማግኘት የሚገባትን ከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ ገቢ አሳጥቷል፡፡

የእንስሳት ቄራዎች አገልግሎት በአብዛኛው መንግስት በመያዙ እነዚህም በተገቢው መስፈርትና ደረጃ ባለመገንባታቸው አገልግሎቱ የተደራሽነትና ጥራት ጉደለት ከማስከተሉም በላይ የህገወጥ እርድ እንዲስፋፋ አድርጓል፡፡ በሌላ መልኩ ፍላጎት ያላቸው የግል አገልግሎት አቅራቢዎች ወደ ስራ ለመግባት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በተለይም የከተማ ማስተር ፕላን ሲዘጋጅ ለቄራ አገልግሎቶች የሚሆን ቦታ ባለመለየቱ አገልግሎቱ በመንግስት እንዲወሰን አድርጎታል፡፡

### የፖሊሲ ማሻሻያው

- የእንስሳት እና እፅዋት ጤና አጠባበቅ፣ ጥራትና ኳራንቲን አገልግሎቶች መሰረተ ልማት የግብርና ቴክኖሎጂና ግብዓት እና ምርት ጥራትና ድህንነት በተሟላ መልኩ ለማስጠበቅ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተመሰከረላቸው (Accredited) እንዲሆኑ እና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አሰራር እንዲቀናጅ ይደረጋል፣
- የአገልግሎት መስረተ ልማቶች በመንግስትና የግል አጋርነት እንዲገነቡና እንዲተዳድሩ ይሆናል፣

- የግሉ ዘርፍ በአገልግሎት መሰረተ ልማት ዝርጋታና አስተዳደር ጉልህ ሚና እንዲኖረው ይደረጋል።

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የግብርና አገልግሎት መሰረተ ልማትና አስተዳደር በዓለም አቀፍ ደረጃ የተመሰከረላቸው (Accredited) ማስደረግን ጨምሮ ስትራቴጂ ይነደፋል፣ አሰራር ስርዓት እና ተቋማዊ አደረጃጀትና ቅንጅታዊ አሰራር ይዘረጋል።
- የመንግስት እና የግል ዘርፍ አጋርነት አሰራር ስርዓት እንዲሁም የግሉ ዘርፍ እና ህብረት ስራ ማህበራት የመሰረተ ልማት ዝርጋትና አስተዳደር ላይ እንዲሳተፉ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የማበረታቻ ስርዓት ይዘረጋል።

## 5.7 የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግና ማጠናከር

የግሉ ዘርፍ በግብርና ቴክኖሎጂ፣ ግብዓትና አገልግሎት በማቅረብ፣ በቀጥታ ምርት ማምረት፣ ግብይትና እሴት ጭመራ አገልግሎቶች ላይ በመሳተፍ ለግብርና ምርትና ምርታማነት እድገት ያለው አስተዋፆ ከፍተኛ ነው። የግሉ ዘርፍ በግብርና ልማትና ግብይት ውስጥ ተሳትፎና ውጤታማነት ከፍተኛ ፋይዳ ቢኖረውም ከአገልግሎትና ሌሎች ዘርፎች ጋር ሲነፃፃር የግብርና ልማት ከፍተኛ ልፋት የሚጠይቅ፣ ከፍተኛ አደጋ (risk) ያለው፣ የትርፍ ህዳጉ ዝቅተኛ ስለሆነ የግሉ ዘርፍ በግብርና ልማት ውስጥ በሚፈለገው ደረጃ ለማሳተፍ እና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የዘርፉን ልዩ ባህሪያት ያገናዘብ የፖሊስ ማዕቀፍ እና አሰራር ስርዓት አልተዘረጋም። በሌላ መልኩ ነባሩ ፖሊሲ የትኩረት አቅጣጫ የነበረው የውጪ ቀጥታ ኢንቨስትመንትና የሀገር ውስጥ ባላሀብቶችን በመሆኑ ወደ ኢንቨስትመንት በማደግ ላይ ያሉ አነስተኛ አርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮችን ለመደገፍና ለማበረታታት የሚያስችል የአሰራር ስርዓት አልተዘረጋም።

በሌላ በኩል የኢንቨስትመንት መሬት አቅርቦት የሚመራበት የተሟላ የአስራር ስርዓት ባለመዘርጋቱ አርሶና አርብቶ አደሩን የማፈናቀል አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጥሯል። ይህም የአካባቢው ነዋሪዎች ልማቱን በበጎ እንዳያዩት ከማድረጉ በተጨማሪ ለልማቱ የደህንነት ስጋት ሲፈጥር ቆይቷል። በሌላ መልኩ በዘርፉ የሚሰማሩ ተዋንያን የሚለዩበት መስፈርቶች ባለመቀመጣቸው ለልማቱ አወንታዊ ሚና የማይጫወቱ ተሳታፊዎች ይዞ

መቀጠሉ ውጤታማነቱን ተፈታትኖታል። በተጨማሪም ከቀረጥ ነፃ ማበረታቻ ድጋፍ የተሰጣቸው ባለሀብቶች ከታለመላቸው የግብርና ልማት ውጭ ለሌላ አላማ እየዋሉ ይገኛሉ።

የውጪ ኩባንያዎች መዋለ ንዋያቸውን በግብርና ላይ አፍስሰው የሚያገኙቱን ትርፍ ወደ ዋና መስሪያ ቤታቸው ልከው ለባለአክሲዋኖች ለማከፍፈል በሀገራችን ባለው የውጪ ምንዛሬ እጥረት የተነሳ ተግባራዊ ማደረግ አልተቻለም። ይህም የውጪ ኩባንያዎች በሀገራችን ግብርና እንዳይሰማሩ ወይም ያሉትም ኢንቨስትመንቶች እንዳያስፋፉ እንቅፋት ሆኖ ይገኛል።

ጉምሩክ የሚቆጣጠረው የገቢ ካፒታል ዕቃዎች አሰራር በተመዘገቡ ዝርዝር (ፖሲቲቭ ሊስት) ብቻ በመሆኑ አዳዲስ በዝርዝሩ ያልተካተቱ የግብርና ቴክኖሎጂና መሣሪያዎችን ለማስተናገድ አያስችልም፤ ይህም ክልከላ በየጊዜው የሚወጡ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን ለግብርና ዘርፍ እድገት ጥቅም ላይ እንዳይውሉ እንቅፋት ከመሆኑም በላይ ለግል ዘርፉ ተዋንያን ለአላስፈላጊ ወጪና እንግልት ዳርጓቸዋል።

የመንግስትና ግል አጋርነት የህግ ማዕቀፍ ዝቅተኛ የካፒታል መነሻ መጠኑ የግብርና ዘርፍ መሰረተ ልማቶች ለሟሟላት አዳጋች መሆኑና መዋቅራዊ አደረጃጀቱ በፌደራል ደረጃ ላይ ብቻ የሚገኝ በመሆኑ በዘርፉ የመንግስትና ግል አጋርነትን ለመተገበር የማይቻል አድርጎታል።

የሰው ሃይል ልማት ፍላጎት ከትምህርትና ስልጠና ተቋማት ባለመተሳሰሩ የግሉ ዘርፍ የሚያስፈለገውን የብቃት ማዕቀፍ ሊያሟላ አልቻለም። በመሆኑም የግሉ ዘርፍ ውጤታማነትና ተወዳዳሪነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከመፍጠሩም በላይ ስራ ፈጣሪ ምሩቃንን በሚጠበቀው ደረጃ ማፍራት አልተቻለም።

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የተሻለ አቅም በመፍጠር ላይ ያሉ አነስተኛ አርሶና አርብቶ አደሮችን ወደ መካከለኛ ግብርና አልሚነት እንዲሸጋገሩ የሚያስችል ድጋፍና ማበረታቻ ይሰጣል፣
- የሰፋፊ ግብርና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ይደረጋል፣ ውጤታማነቻው ይረጋገጣል፣

- የኢንቨስትመንት፣ ንግድ፣ ታክስ እና ግምሩክ የህግ ማዕቀፎች (የማበረታቻ ስርዓት፣ የንግድ ምዝገባና ፍቃድ እና ብቃት ማረጋገጫ ጨምሮ) የግብርና ልዩ ባህሪ ባገናዘበ ሁኔታ ልማቱና ግብይቱን እንዲደግፍ ይደረጋል፣
- የመንግስትና ግል አጋርነት የህግ ማዕቀፍ እና አሰራር ስርዓት የግብርና ልዩ ባህሪ ባገናዘበ ልማቱን እንዲደግፍ ይደረጋል።

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የተሻለ አቅም በመፈጠር ላይ ያሉ አነስተኛ አርሶና አርብቶ አደሮችን ወደ መካከለኛ ግብርና አልሚነት እንዲሸጋገሩ የሚደግፍ የህግ ማዕቀፍና አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የኢንቨስትመንት፣ ንግድ፣ታክስ እና ግምሩክ የህግ ማዕቀፎች የግብርና ልዩ ባህሪ ባገናዘበ ሁኔታ ልማቱና ግብይቱን እንዲደግፍ ሆነው ይሻሻላሉ፣
- የሰፋፊ ግብርና ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ስትራቴጂ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓትና መዋቅራዊ አደረጃጀት ይጠናከራል፣
- የመንግስትና ግል አጋርነት የህግ ማዕቀፍ የግብርና ልዩ ባህሪ ባገናዘበ ሁኔታ ያሻሻላሉ፣
- ውጤታማ የግል ኢንቨስትመንት (Responsible Agricultural Investment) ለማስፈን የሚያችል የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ አሰራር ስርዓት እና ተቋማዊ አደረጃጀት ይዘረጋል።

## 5.8 የግብርናና ገጠር ልማት ፋይናንስ ሥርዓት

ፋይናንስ (ብድርና መድን) የግብርናን ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን (መሬት፣ ጉልበት እና ቴክኖሎጂ) አጣምሮ ምርትማነትና ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ ወሳኝ መሳሪያ ነው። ነባሩ ፖሊሲ የግብርና ዘርፍ በተለይም አነስተኛ አርሶና አርብቶ አደሮችን የተጠናከረ የፋይናንስ አቅርቦት ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚያስፈልግ አቅጣጫ አስቀምጧል። በተጨማሪም የፋይናንስ አቅርቦቱ በመደበኛ ባንኮች በኩል በተሟላ መልኩ ሊቀርብ እንደማይችል በመገንዘብ ጠንካራ የገጠር ፋይናንስ ሥርዓት መገንባት እንደሚያስፈልግ አብራርቷል። የገጠር ፋይናንስ ሥርዓቱም በዋናነት የገጠር ባንኮች የሚያቀርቡትን

የብድር መጠን ከፍ በማድረግ ከቡድን ብድር በተጨማሪ የአርሶና አርብቶ አደሩን ምርት እንደ ዋስትና በማስያዝ የግል ብድር መውሰድ እንዲሁም ከኅብረት ሥራ ማኅበራት ጋር ትስስር በመፍጠር ተደራሽነታቸውን እንደሚጨምሩ አቅጣጫ ተቀምጧል። እንዲሁም የኅብረት ሥራ ማኅበራት ሌሎች የፋይናንስ ተቋማትን ከግብርና ጋር በማስተሳሰርም ሆነ የራሳቸውን ባንክ በማቋቋም የገጠር የፋይናንስ ሥርዓት ግንባታን እንዲያግዙ የፖሊሲ አቅጣጫው ከመጠቆሙም ባሻገር ሌሎች የፋይናንስ አማራጮችን ለማስፋፋት የአሰራር ስርዓት እንደሚያስፈልግ ተመላክቷል።

ሆኖም ግን የመደበኛ ባንኮችና መድን ድርጅቶች ግብርናን በተለይም አነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮችን እና አርብቶ አደሮችን በተገቢው ለማገልገል የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ባለመዘርጋቱ እንዲሁም የፖሊሲ ባንክ የሆነው የኢትዮጵያ ልማት ባንክም ቢሆንም ትኩረቱ ትላልቅ ኢንቨስትመንቶችን ላይ በመሆኑ ለዘርፉ የቀረበው የፋይናስን አገልግሎት አነስተኛ ነው። የጥቃቅን ፋይናንስ ተቋማት ለግብርናና ገጠር ምቹ የሆነ የቡድን ዋስትና የመሳሰሉ አሰራሮች ቢኖሯቸውም ያላቸው የካፒታል አቅርቦት ከፍላጎት አኳያ ዝቅተኛ በመሆኑ፣ የህብረት ስራ ማህበራት የሚጠበቀውን ያህል የፋይናንስ አገልግሎት ማቅረብ አለመቻላቸው እና ሌሎች የፋይናንስ አማራጮችን ሥራ ላይ እንዲውሉ የሚያስችል የተሟላ የህግ ማዕቀፍና የአሰራር ስርዓት አልተዘረጋም።

ከሁሉም በላይ የሀገራችን የፋይናንስ ተቋማት የግብርናን ልዩ ባህሪያት በተለይም ለአደጋ ተጋላጭነቱን በተገቢው የሚጋራ የፋይናንስ አቅርቦት ለማዘጋጀት የአቅማ፣ ግንዛቤ እና ፍላጎት ማጣት ውስንነቶች አሉባቸው። በመሆኑም ለዘርፉ ከመደበኛ ባንኮች የሚቀርበው ብድር ባላፉት ቅርብ ዓመታት በከፍተኛ ሁኔታ እየቀነሰ በመምጣት በአሁኑ ወቅት ከባንኮች ከሚቀርቡት አጠቃላይ ብድር ውስጥ ከ10 በመቶ በማይበልጥ ሲሆን ከዚህም ውስጥ ለአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደር እና አርብቶ አደሩ የተቀረበው ከ20 በመቶ በታች ነው። ለዚህም እንደ ምክንያት የሚቀርቡት ዘርፉ በአብዛኛው በአነስተኛ አምራቾች ላይ የተመሰረት እና የሚገኘውም ገቢ የሚዋዥቅ መሆኑ ፣ ለብድር ማስያዥያነት የሚሆን በቂ የእሴት ክምችት አለመኖር፣ ያላቸውም ንብረት ባለመመዝገቡ ለዋስትናነት ማስያዣነት ለማሟላት አለመቻላቸው ይጠቀሳሉ። በተጨማሪም የተበዳሪዎችን ማንነት መረጃ ቋት በተደራጀ ሁኔታ ባለመዘርጋቱ የተነሳ የፋይናንስ ተቋማቶቹ የፋይናንስ ፈላጊዎችን የፋይናንስ አገልግሎትን ተጠቅመው

ለመመለስ ወይም ለመክፈል ተአማኒነት ለመመዘን አዳጋች ሆኖ መቆየቱ ነው። በሌላ መልኩ ከፍተኛ የብድር ዋስትና ጥያቄዎች እና የወለድ ምጣኔ የብድር ፈላጊው ህብረተሰብ አቅም ጋር ያለተገናዘበ ነው። ይህንኑ ችግር ለመቅረፍ መንግሥት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ተዘዋዋሪ የብድር ስርዓት ቢዘረጋም የብድር ተመላሽ መጠን ዝቅተኛ በመሆኑ የብድር ስርዓቱን በዘላቂነት ለማስቀጠል ተግዳሮት ሆኖ ይገኛል።

የመድን አቅርቦትም በአብዛኛው በአጠቃላይ የመድን አገልግሎት ላይ ያተኮረ ነው። በፕሮጀክት ደረጃ ከተተገበሩ ውስን የግብርና መድን ሽፋን አይነቶች ልምድ ወስዶ በማስፋት የተጠናከረ የግብርና መድህን ሽፋን በሀገር ደረጃ አልተስፋፋም። በተጨማሪም የአርሶና አርብቶ አደሩ አሰፋፈር በሰፊ የመሬት ሽፋን ላይ የተበታተነ በመሆኑ ተደራሽነትን በቀላሉ ለማረጋገጥ አዳጋች አድርጎታል። የመደበኛ ብድርና መድን አቅርቦት ችግሮችን ለመፍታት የተወሰኑ የፋይናንስ አማራጮች ለምሳሌ የገጠር መሬት መጠቀም መብትን ለብድር መስያዣ መጠቀም፣ ምርትን በመጋዘን አስቀምጦ ለብድር መስያዣ መጠቀም በሀገር ደረጃ ቢሞከሩም ተደራሽነቱ ገና ከጅምር ያለፈ አይደለም። ከውጪ የሚመጡ የአክስዮን ካፒታል ግብርና ላይ አዋጭ በሆነ መልኩ ሃብታቸውን የሚያፈሱበት ሥርዓት ባለመዘርጋቱ ካፒታላቸውን ከግብርና ውጪ ባሉ ሌሎች ዘርፎች ላይ እንዲያፈሱ ተገደዋል። የህብረት ሥራ ማህበራት የመሠረተ ልማት ፍላጎት በፕሮጀክት ፋይናንስ አሰራር እንዲገነባ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ባለመኖሩ የመሰረት ልማት ዝርጋታ በመንግሥት ውሱን በጀት ላይ ብቻ እንዲወሰኑ አድርጎታል።

በአጠቃላይ የዘርፉን ምርታማነት እና ተወዳዳሪነት ለማሳደግ ከመሬት፣ ጉልበት፣ውሃ እና የቴክኖሎጂ አቅርቦቶች በተጨማሪ የዘርፉን ባህሪያት ያገናዘ ተደራሽ የፋይናንስ አቅርቦት በተለይም ተመጣጣኝ የወለድ ምጣኔ እና የረጅም የብድር መክፈያ ጊዜ ያለው የብደር አገልግሎት፣ ከተጠቃሚው አቅም ጋር የተጋናዘበ የመድህን ሽፋን እና አማራጭ የፋይናንስ ምንጮችን ማስፋፋት የማይተካ ሚና አላቸው። በመሆኑም በመደበኛው ባንኮች፣ መድህን ድርጅቶች እና አነስተኛ የገንዘብና ብድር ተቋማት ከሚቀርበው የፋይናንስ አገልግሎቶች በተጨማሪ የፖሊሲ ሚና የሚጫወት የግብርና ፋይናንስ ተቋም ያስፈልጋል።

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የግብርና ገጠር ልማት የብድር አቅርቦት ለማሻሻል መደበኛ ባንኮች ዘርፉ ካለው ሁለንተናዊ አስተዋፆ አንፃር የሚያበረታታ የብድር ድርሻው (loan portfolio) እንዲያድግ ይደረጋል፣ ራሱን የቻለና የፖሊሲ ተግባራት የሚወጣ የግብርና ባንክ ይቋቋማል፣ ይህንኑ የሚያስተባብር ተቋማዊ አደረጃጀት ይገነባል፣
- የገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ሥራ ማህበራት በራሳቸው አቅምና ከአባላት ውጪ የአክሲዮንና ፕሮጀክት ካፒታል እንዲያሰባስቡ ይደረጋል፣ የህብረት ስራ ባንክ ማቋቋም ይፈቀዳል፣
- ተንቀሳቃሽ ንብረትን (መሬት የመጠቀም መብት፣ እንስሳት፣ ግብርና ምርቶች) ለብድር ማስያዣነት መጠቀም ይፈቀዳል፣
- አማራጭ የፋይናንስ ምንጮች ስራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፣
- የዘርፉን ልዩ ባህሪ ባገናዘበ መልኩ የውጪ ምንዛሬ ፖሊሲ ይሻሻላል፣
- የግብርናና ገጠር ልማት መድን ሽፋን ለማሻሻል መደበኛ ኢንሹራስ ድርጅቶች የዘርፉን የአደጋ ተጋላጭነት እና ለሀገራዊ ኢኮኖሚ ካለው አስተዋፆ አንፃር የሚያበረታታ የመድን ድርሻው (insurance portfolio) እንዲያድግ ይደረጋል።

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የመደበኛ ባንኮች ለዘርፉ የሚያቀርቡት የብድር ድርሻ (loan portfolio) ከፍ እንዲያደርጉ የሚደግፍና የሚያበረታታ የአስራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- ራሱን የቻለና የፖሊሲ ተግባር የሚወጣ የግብርና ባንክ የሚያቋቁም የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓትና ተቋማዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣
- የህብረት ስራ ብድርና ቁጠባ ማህበራት በራሳቸው አቅምና ከአባላት ውጪ የአክሲዮንና ፕሮጀክት ካፒታል እንዲያሰባስቡ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የህብረት ስራ ባንክ ማቋቋም የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣
- ተንቀሳቃሽ ንብረትን (መሬት የመጠቀም መብት፣ እንስሳት፣ ግብርና ምርቶች) ለብድር ማስያዣነት ለመጠቀም የሚያስችል የተሟላ የአሰራር ስርዓትና ተቋማዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣
- አማራጭ የፋይናንስ ምንጮች ለመጠቀም የሚያችል የተሟላ የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣

- የመደበኛ ኢንሹራስ ድርጅቶች ለዘርፉ የሚያቀርቡት የመድን ድርሻው (insurance portfolio) ከፍ እንዲያደርጉ የሚደግፍና የሚያበረታታ የአስራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

## 5.9 ተቋማዊ የአሰራር ስርዓት

### 5.9.1 የሰው ኃይል ልማት

የሰው ሃይል በብቃት፣ በቅልጥፍናና በውጤታማነት ማደራጀት እና የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የተገልጋዮች እና የባለድርሻ አካላትን ፍላጎት ለማርካት ወሳኝ ነው፡፡ ይህንኑ መሰረት በማድረግ መንግስት የሙያና የሥራ ብቃት ማረጋገጫ ሥርዓት፣ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራም እንዲሁም የሰው ሃብት ሥራ አመራር ስርዓት ስራ ላይ በማዋል በሀገሪቱ ለተመዘገበው እድገት የበኩሉን አስተዋፆ አድርጓል፡፡

ሆኖም ትኩረት አቅጣጫ የነበረው በአመዛኙ የቀበሌ ልማት ባለሙያዎች ላይ ሲሆን በዘርፉ ውስጥ ስለላሉ ሌሎች ባለሙያዎች ውጤታማነትና ተጠያቂነት እንዲሁም የማትጊያ እና የደረጃ (ሙያ) እድገት ስርዓት በተሟላ መልኩ አልተዘረጋም፡፡ በተጨማሪም ዘርፉ በሙያው በሰለጠነ ሰው ሃይል (ፕሮፌሽናል) የሚመራበት አሰራር አልተፈጠረም፡፡የሰው ኃይል የሚመራበት የፖሊሲ ማዕቀፍ እና የአሰራር ስርዓት አልተዘረጋም፡፡ የአመራሩ የብቃት መገምገሚያ ስርዓት ያልተቀመጠለት ከመሆኑም ባሻገር የኃላፊነትና ተጠያቂነት መርሆም ስለሌለው ድክመትን አርሞ ሥራውን ለማቀላጠፍ አልተቻለም፡፡ ሌሎች የማበረታቻ፣ ተሳትፎ፣ የሰው ሀብት ሙሌት ፣ የሰው ሀብቱ የስራ አፈጻፀም ምዘና ስርዓት ዝርጋታ፣ ስልጠና መስጠት፣ የፍላጐት ዳሰሳ ጥናት፣ የፕሮግራም ቀረጻ፣ የትግበራ እና የውጤታማነት ግምገማ፣ ስልታዊ የተተኪ አመራር ማዘጋጀት፣ የእውቀት ስራ አመራር ስርዓት ሳይዘረጋ ቆይቷል፡፡ ምቹ የስራ አካባቢ ደህንነት እና ጤንነት የሚያረጋገጥ አሰራር ስርዓት ባለመኖሩ ሠራተኞችን ለሥራ የሚያነሳሳ የስራ ስምሪትና አሰራር ለመዘርጋት ባለመቻሉ ብቃት ያላቸውን ሠራተኞችን ለማቆየትም ሆነ አዳዲስ ሰራተኞችን ለመሳብ አዳጋች ሆኗል፡፡

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የባለሙያና አመራር ለማደራጀት ዕውቀትን፣ ክህሎትንና ብቃትን መሰረት ያደረገ የምልመላ፣ መረጣ እና ምደባ ስርዓት ለመዘርጋት እንዲሁም ኃላፊነትና ተጠያቂነት

(ግምገማና ምዘና)፣ የደረጃ (ሙያ) እድገት ደመወዝና ማትጊያ እና ምቹ የስራ አካባቢ ደህንነትና ጤንነት ስርዓት የዘርፉን ልዩ ባህሪያት ባገናዘ መልኩ ይደራጃል፡፡

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የሰው ሀብት አደረጃጀትና አስተዳደር ስትራቴጂ ይነደፋል፣ የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

### 5.9.2 የተቋማት ትብብርና ተጠያቂነት ስርዓት

ግብርና በባህሪው ረዥም የእሴት ሰንሰለት ውስጥ የሚያልፍ በመሆኑ የብዙ ተቋማት ተሳትፎና ድጋፍ እንዲሁም ቅንጅትና ትብብርን ይፈልጋል፡፡ የተቋማት የስልጣን ወሰናቸውን በማይነካ ሁኔታ ለመተግበርና ለማስተግበር ትብብርና ተጠያቂነት በሰፈነበት አኳኋን ማከናወን ግቦቻችንን ለማሳካት አስፈላጊ ነው፡፡

ተጠያቂነትን መሰረት ያደረገ ትብብር እንዲፈጠር ማድረጉ በሃገራዊ የግብርና ልማት ርዕይና ዓላማዎች ላይ የጋራ መግባባት ለመያዝ፣ ሀገራዊ የግብርና ልማት ፕሮግራሞችን ከአዳጊና ተለዋዋጭ ሁኔታዎች እና ከአባቢያዊ ሁኔታዎች ጋር ለማጣጣም፣ የግብርናውን ዘርፍ ተመጋጋቢነትና ትስስር ለማጎልበትና በተነፃፃሪ ዕድሎች ላይ የተመሰረተ ፈጣን ዕድገት ለማረጋገጥ፣ሀብትን በቅንጅትና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀም ይረዳል፡፡

በግብርና ዘርፍ አደረጃጀቶች እና በግብርና ልማት ላይ ወሳኝ ድርሻ ያላቸው አካላት በተዋረድና በጎንዮሽ ተናበውና ተቀናጅተው ከግል ተቋማትና ልማት አጋር አካላት ጋር የትብብርና ተጠያቂነት አሰራር ስርዓት መዘርጋት በዘርፉ ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ ይረዳል፡፡

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- በሁለቱ የመንግስት እርከኖች የተዘረጉ የግብርና ዘርፍ ፈፃሚዎች ሚናቸውና ኃላፊነታቸው ተለይቶ ተጠያቂነት የሰፈነበት ውጤታማ ግንኙነት እንዲኖራቸው ይደረጋል፣

- የግብርና ተቋማት ከሌሎች ዘርፎች ተቋማት እንዲሁም ዘርፉን ከሚደግፉ መንግስታዊ ያልሆኑና የግል ተቋማት ተጠያቂነት በሚያሰፍን መልኩ ውጤታማ ግንኙነት እንዲኖራቸው ይደረጋል፣
- የዕቅድ ክትትልና ግምገማ እና ግብርና መረጃ ስርዓቶች ይጠናከራሉ።

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- በፌዴራልና ክልል እርከኖች የተዘረጉ የግብርና ዘርፍ ተቋማት፣ ዘርፉን ከሚደግፉ መንግስታዊ ያልሆኑና የግል ተቋማት እንዲሁም ከሌሎች ዘርፎች ተቋማት ጋር ለሚኖራቸው ግንኙነት የሚወስን የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ አሰራር ስርዓት ይዘረጋል።
- የተጠናከረ የዕቅድ ክትትል፣ ግምገማ እና የመረጃ ስርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ አሰራር ስርዓት ይዘረጋል።

### 5.9.3 የትምህርትና ስልጠና እና የግብርና ዘርፍ ተቋማት ትስስርና ተጠያቂነት ስርዓት

የትምህርትና ስልጠና ተቋማት በፍጥነት በመስፋፋት ለዘርፉ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሃይል እያቀረቡ ይገኛሉ። ነበሩ ፖሊሲ በዩኒቨርስቲዎች፣ በምርምር ተቋማት፣ በቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት እና በኢንዱስትሪዎች መካከል የተቀናጀ የቴክኖሎጂ ሽግግር ተግባራትን ለማከናወን እና ለኢንዱስትሪው በክህሎት የዳበረ የሰው ሃይል ለማፍራት የሚያስችል ስርዓት እንደሚዘረጋ ያስቀምጣል። የእነዚህን ተቋማት ትስስር ለመፍጠርና ለማጠናከር የተለያዩ የጋራ መድረኮች ተቋቁመዋል። ከቅርብ አመታት ወዲህ እነዚህን መድረኮች ተቋማዊ ለማድረግ የዩኒቨርሲቲ፣ ምርምር እና የግብርና ልማት ተቋማት የሚያካትት የምርምር ካውንስልና ሴክሬታሪያት ተቋቁሟል። ሆኖም ግን የእነዚህን ተቋማት ትስስር ውጤታማና ተጠያቂነት የሰፈነበት ለማደረግ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ እና ተቋማዊ የአሰራር ስርዓት አልተዘረጋም። በተለይም ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች በአብዛኛው ለመንግስት ቅጥር የሚያሰለጥኑ በመሆኑ ለግሉ ዘርፍ የሚያስፈልግ በመካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሃይል ማፍራት አልተቻለም።

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የግብርና ልማት፣ ምርምር እና ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ትስስርና ተጠያቂነት የሰፈነበት ውጤታማ ግንኙነት እንዲኖራቸው ይደረጋል፣
- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርትና ስልጠና በግብርና ዘርፍ የሰው ሃይልና ክህሎት ፍላጎት መሰረት እንዲመራ ይደረጋል።

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የግብርና ልማት፣ ምርምር እና ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ትስስርና ተጠያቂነት የሰፈነበት ውጤታማ ግንኙነት እንዲኖራቸው የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓትና ተቋማዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣
- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርትና ስልጠና በግብርና ዘርፍ የሰው ሃይልና ክህሎት ፍላጎት እንዲመራ የሚያደርግ የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓትና ተቋማዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣
- የግብርና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና በግብርና ዘርፍ የመካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ሃይልና ክህሎት ፍላጎት እንዲመራ የሚያደርግ የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓትና ተቋማዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣

## 5.9.4 የዲጂታል ግብርና እና ኮሙኒኬሽን የአሰራር ስርዓት

የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ኢኮቴ) በተለያዩ ዘርፎች የለውጥ መሳሪያ በመሆን ሀገራዊ ኢኮኖሚን ለማሳደግና የማህበረሰብን ተጠቃሚነት ለማሻሻል ከፍተኛ አስተዋፆ እያበረከተ ይገኛል። በግብርናው መስክ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ምርታማና በገበያ ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥም ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ወቅታዊ መረጃን መሰረት በማድረግ ጥናትና ምርምር በማካሄድ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችንና ምክረ-ሐሳቦችን በሚፈለገው ቦታ ለመስጠት፤ ለትክክለኛነት የቀረበ ግብርና (precision agriculture) እና ሜካናይዜሽን በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል፣ የምርት ጥራትን ለማረጋገጥ፤ ዲጂታል ኤክስቴንሽንና የምክር አገልግሎት አሰጣጥን ለማቀላጠፍ፣ የግብርና ግብአትና ምርት ዱካ ለመከታተል፣ የሰብልና እንስሳት ተባይና በሽታ ቅኝትና የሥጋት ትንተና ለማድረግ፣ ቅድመ ማስጠንቀቂያ እና ወቅታዊ ምላሽ ለመስጠት፣ የግብርና ገጠር ፋይናንስ አገልግሎት ምቹ ለማድረግ፣ የግብርና ምርት ትንበያ ለመስጠት፣ የግብርና

ግብይት (ከምርት እስከ ገበያ ያለውን ዱካ ለመከታተል፣ የኤሌክትሮኒክ የአሰራር የታገዘ የግብርና ምርቶች ንግድ ለማስፋፋት፣ የገበያ መረጃ አገልግሎት ለመስጠት)፣ የግብርና መረጃ በየፈርጁ በማደራጀት ለፖሊሲ አውጭዎችና ውሳኔ ሰጭ አካላት እንዲሁም ለተጠቃሚው በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግ፣ የክትትል፣ ግምገማና ግብረ-መልስ አሰጣጥ ሥርዓትን በየደረጃው ለመዘርጋት፣ የጂኦ-ስፓሻል ቴክኖሎጂን በመጠቀም የተጎሳቆሉ፣ ያገገሙ፣ የለሙ መሬቶችን በቀላሉ ለመለየት እና የተፈጥሮ ሃብት አያያዝና አጠቃቀም መረጃ ለመዘርጋት ያስፈልጋል፡፡

ይህንን ታሳቢ በማድረግ መንግስት የፖሊሲ ማዕቀፍና የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ኢኮቴ በአገራዊ ኢኮኖሚ እድገት ላይ ተጨባጭ ለውጥ ማስመዝገብ እንዲችል በቅርቡ የዲጂታል ኢኮኖሚ ስትራቴጂ ተፅድቆ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡ የመረጃ አሰባሰብ ወጥ አሰራር ባለመኖሩ መረጃዎች እርስ-በአርስ የሚጣጣሙ ያለመሆን፣ በግብርና ውስጥ የበለፀጉ ኢኮቴ የተበጣጠሱና እርስ በእርስ የማይመጋገቡ መሆን፣ የግብርና መረጃ አያያዝና ልውውጥ ፖሊስ ያለመኖር፣ የኢኮቴ ልማትና ኢንቨስትመንት በዘላቂነት በፕሮግራም ያለመመራት፣ እስከታችኛው የአስተዳደር እርከን ድረስ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መዋቅራዊ አደረጃጀትና መሰረተ-ልማት በሚፈለገው ልክ አለመዘርጋት፣ የኃይል አቅርቦትና የኢንተርኔት አገልግሎት በተለይ በገጠራማ አካባቢ አለመኖር፣ የበለፀጉ የኢኮቴ መረጃ ሥርዓቶችን የመጠቀም አቅም እንዲሁም ፈቃደኝነት ማነስ፣ በኢኮቴ የተሰማሩ የግሉ ዘርፉ በግብርናው መረጃ ሥርዓት ማዘመን ዙሪያ አስተዋጽኦ ማነስ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ግብርናን በኢኮቴ ለመደገፍ የተለያዩ ስራዎች የተሞከሩ ቢሆንም አብዛኞቹም በሙከራ ላይ ተገድበው በመቅረታቸው፣ የተበጣጠሱና እርስ-በእርስ የማይመጋገቡ በመሆናቸው የሥራ ድግግሞሽና የሀብት ብክነት መኖሩ እንዲሁም በግብርናው ዘርፍ የዲጂታል ቴክኖሎጂ አጠቃቀም እጅግ አነስተኛ መሆኑ በግብርናው ዘርፍ የሚጠበቀውን ውጤት ማምጣት አልተቻለም፡፡

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የግብርናው ዘርፉ የዲጂታል አሰራርን የበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የተቀናጀ የግብርና የዲጂታላይዜሽን ስትራቴጂ፣ የግብርና መረጃ አያያዝ፣ አጠቃቀምና ልውውጥ የፖሊሲ እና ህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓትና መዋቅራዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣ የልማት ፕሮግራም ይተገበራል።

## 5.9.5 የቴክኖሎጂ፣ ግብዓትና አገልግሎት እና ምርት ጥራት፣ ጤናና ደህንነት ቁጥጥር

የግብርና ቴክኖሎጂና ግብዓት ቁጥጥር ሥርዓት ጥራትን፣ ፈዋሽነትን፣ ብቃትን በማረጋገጥና የኳራንቲን አገልግሎት በመስጠት የቅድመ ምርትና ድኅረ ምርት ብክነትን በመቀነስ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር፣ የምርት ጥራትና ጤንነት በማረጋገጥ የምግብ ደህንነትን እንዲጠበቅ እንዲሁም ወደ ውጭ የሚላኩ የግብርና ምርቶች የመዳረሻ ገበያዎች የጥራትና ጤንነት መስፈርቶችን እንዲያሟሉ በማገዝ የውጭ ምንዛሬ ለማስገኘት አስተዋፅዖ ከፍተኛ ነው። ይህንን የሚያግዘውን የብዙ ተዋንያን የምርምርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ጥራትና ቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት ጥራት ያለው ቴክኖሎጂና ግብዓት ለማቅረብ ወሳኝ ነው። በተመሳሳይ ደረጃቸውን ያልጠበቁ የግብርና መሣሪያዎች ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ እና በሀገር ውስጥ የሚመረቱትም የጥራት ደረጃቸውን በመቆጣጠር ተጠቃሚዎችን ከኪሣራ እና ወጪ ይታደጋል። ከዚህ በተጨማሪ የሕይወታዊ ሃብትን በመጠበቅ ግብርናን ለመነሻ ዘር ምንጭ ከሆነው ከብዛ ዘርና አባለ ዘር ጥገኝነት በመከላከል ዘላቂነት እንዲኖረው አስተዋፅዖ በማበርከት ለምግብና ስርዓተ ምግብ ዋስትና መረጋገጥ የማይተካ ሚና ይጫወታል።

ለሥራው የሚመጥን የቁጥጥር አደረጃጀት እንዳይኖር ማድረጉ፣ የልማት እና ተቆጣጣሪ የሥራ ዘርፎች አለመለያየት በቁጥጥር ሥራዎች ላይ የገለልተኝነት ጥያቄ ማስነሳቱ፣ የመሳሪያዎችና ማሽነሪዎች ፍተሻ፣ የምርመራና የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ቁጥጥርና ዕወቅና የመስጫ ሥርዓት አለመዘርጋት፣ በተቆጣጣሪ ተቋማት የሚታዩ የሥልጣንና ኃላፊነት መጋጨትና መደራረብ እና ቅንጅታዊ አሰራር ጠንካራ አለመሆን የቁጥጥር ተግባሩን ቀልጣፋና ውጤታማ እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ በአገልግሎት ተቀባዩ ላይ መጉላላትና ቅሬታ እየፈጠሩ ይገኛል።

የሰብል ቴክኖሎጂና ግብዓት ምዝገባ እና ቁጥጥር ስራን በተጠናከረ ተቋማዊ አደረጃጀት እና ቅንጅታዊ አሰራር ባለመስራት ወደ ሀገር ውስጥ መግባታ የሌለባቸው (ያልተመዘገቡ እና የተከለከሉ) ፀረ ተባይ ኬሚካሎች እንዲሁም በህገ ወጥ ንግድ የሚዘዋወሩ ኬሚካሎች እንዲበራከቱ መሆኑና ይህም ለሰብል ምርት መቀነስ፣ ጥራት ጉድለትና መባከን ከማስከተሉም በላይ በምግብና በሰው ጤንነትና ደህነት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አስከትሏል፡፡ በተጨማሪ ገለልተኛ የቴክኖሎጂ ለቀቃና ምዝገባ የተጠናከረ ባለመሆኑ የምርታማነታቸውና በሽታ መቋቋም አቅማቸው አንፃር የተሻሻለ የማይባሉ የሰብል ዝርያዎች እየተለቀቁ መሆኑ እንዲሁም ለሀራችን ተስማሚነታቸው ያልተረጋገጡ ዘርያዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ በር ከፍቷል፡፡

የእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ሥራ በብሄራዊ ደረጃ በመወሰኑ እና በክልልና ታች ባሉ የግብይት ሰንሰለት፣ አያያዝና አጠቃቀም ላይ የቁጥጥር መዋቅሩ ባለመዘርጋቱ ምክንያት ጥራታቸውን ያልጠበቁ መኖ እና ፋዋሽነታቸው ያልተረጋገጠ መድሃኒቶች ወደ ተጠቃሚው እንዲደርስ ብሎም የህገወጥ የሀገር ውስጥ እና ድንበር ዘለል ንግድ በመስፋፋቱ በእንስሳት ምርታማነት እየጎዳ ይገኛል፡፡

በብዙ ተዋንያን የሚፈልቁ ቴክኖሎጂዎች እና ሁሉንም የሚቀርቡ ግብዓቶች እና የሚሰጡ አገልግሎቶች ቁጥጥር ስርዓት፣ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ባለቤትነት መብት ጥበቃ እና ሮያሊቲ ክፍያ ስርዓት፣ የግል ዘርፍ እንዲሁም ለአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደርና እና አርብቶ አደሮች የሚሰጡ ማበረታቻዎን አፈፃፀም ክትትል ስርዓት አልተዘረጋም፡፡

## የፖሊሲ አቅጣጫው

- የግብርና ቴክኖሎጂ፣ ግብዓትና አገልግሎት እና ምርት ጥራት፣ ጤናና ደህንነት ቁጥጥር ሥርዓት ጠንካራና ከአስፈፃሚ ተቋማት ተፅዕኖ በተላቀቀና የጥቅም ግጭት እንዳይኖረው ሆኖ ይዋቀራል፡፡

## የማስፈፀሚያ ስልቶች

- የግብርና ቴክኖሎጂ፣ ግብዓትና አገልግሎት እና ምርት ጥራት፣ ጤናና ደህንነት ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት የሚያስችል የተሟላ የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓት፣ ተቋማዊ አደረጃጀት እና መሰረተ ልማት ይዘረጋል፣

- በግሉ ዘርፍ ሊከናወኑ የሚችሉ ጥራት ፍቃድ ፍተሻና ቁጥጥር ማድረግ የሚቻልባቸውን ተግባራት ተለይቶ የፍቃድና ቁጥጥር ስርዓት የሚዘረጋ የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የቁጥጥርና ምርመራ፣ የፍተሻና ዕውቅ እና መስጫ ማዕከላትና ላብራቶሪዎች መሰረት ልማት አለም አቀፋዊ እውቅ እንዲያገኙ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- የግብርና ምርቶች ቁጥጥር ስርዓት ለማጠናከር፣ ሀገራችን ያፀደቀቻቸውን አካባቢያዊ፣ አህጉራዊና አለማቀፋዊ ስምምነቶች የሚያስቀምጡትን ግዴታዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል።

## 5.10 ዘርፈ-ብዙ ጉዳዮች

ዘላቂና አካታች የግብርና ልማትን እውን ለማድረግ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ግብርና ልማት ማካሄድ፣ የተፈጥሮና ብዝሀ ሕይወት ሀብት አጠቃቀምን ማሻሻል፣ ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ተጋላጭነትን መቀነስ እንዲሁም ትኩረት ያጡ የማህበረሰብ ክፍሎችን በልማቱ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል። የመልማት እምቅ አቅማቸውን አሟጠው ያልተጠቀሙ (የአርብቶ አደር እና የምግብ ዋስትና ያላረጋገጡ) አካባቢዎች ልዩ ትኩረት ይፈልጋሉ። በተጨማሪም የግብርናው ዘርፍ ዋነኛ የምግብ ምንጭ ስለሆነ በንጥረ-ምግብ ይዘቱ የበለፀገ የምግብ አቅርቦትና ተደራሽነት ማረጋገጥ ልዩ ትኩረት ይፈልጋል። እነዚህ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ከዚህ በላይ በቀረቡት ዘጠኝ ዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮች ውስጥ ተካትተው የሚተገበሩ ይሆናል።

### 5.10.1 ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተስተጋበረ የግብርና ልማት

የግብርና ምርትና ምርታማነትን በዘላቂነት ማሳደግ የሚቻለው በየጊዜው እየተለዋወጠ ከሚገኘው የአየር ንብረት ጋር በማስተጋበር እንዲሁም በመሬትና የተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚደርሰውን ጫና በቀነሰ መልኩ ከተካሄደ ነው። ይህም በግብርና ልማት እና ከባቢ መካከል ያለውን መስተጋብር ሚዛን በማስጠበቅ የተፈጥሮና ብዝሀ ሕይወት ሀብት አጠቃቀምን (የአፈር፣ የደን ፣የውሃ አካላት) ዘላቂነት በማረጋገጥ የግብርና ምርትና

ምርታማነት እንዲያድግ፣ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ እድገት እንዲሻሻል ከማስቻሉም ባሻገር ሀገራችን የተቀበለቻቸውን አህጉራዊና ዓለማቀፋዊ የልማት ስምምነቶችን በላቀ ደረጃ ለመተግበር ያስችላል፡፡

ይህንኑ ለማስፈፀም የሚያስችሉ የፖሊሲ ማእቀፎች ተዘጋጅተው ተግብራዊ እየተደረጉ ይገኛሉ፡፡ የግብርና ልማትን ከዘላቂ ተፈጥሮ ሃብት አያያዝና አጠቃቀም ጋር ጎን ለጎን ለማከናወን የፖሊሲ አቅጣጫ አመላክቷል፡፡ ሆኖም ማእቀፎቹ ተፈፃሚነታቸውን የሚያረጋግጡ የህግ ማዕቀፎች ባለመነደፋቸው እንዲሁም ተቋማዊ ቅንጅት የሚፈጥር አሰራር ስርዓት አልተዘረጋም፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ (የሙቀት መጨመር፣ ዝናብ ወቅት መዛባት፣ የጎርፍና የመሬት መንሸራተት) በሰብልና እንስሳት ልማት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጥሯል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም የሰብልና እንስሳት ተባይና በበሽታ ክስተት ድግግሞሽና ስርጭት እንዲባባስ አድርጎታል፡፡ ይህም ግብርናውን ይበልጥ ለተፈጥሮ አደጋ ተጋላጭ አድርጎታል፡፡

የግብርና ኤክስቴንሽን ዋና ትኩረት የነበረው የአፈር ማዳበሪያና የምርጥ ዘር አጠቃቀም በማስፋት የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ አርሶ አደሮችን ቁጥር መጨመር ላይ ነበር፡፡ አርሶና አርብቶ አደሩ መሬቱን በአግባቡ በመንከባከብ ጥቅም ላይ እንዲያውል አስገዳጅ ሁኔታ ባለመኖሩ የወል ይዞታ ያላቸውን የግጦሽ መሬት፣ የደን ቦታ፣ የከርሰ ምድር ውሃን የሚሞሉ ውሃ አዘል መሬቶች የመሳሰሉት የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዲደርስባቸው አስገድዷል፡፡ ይህም ወደፊት የሚገጥመንን የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ለመቋቋም ሀገራችን የሚኖራትን የተሻለ ዕድል ይበልጥ እንዲጠብ ያደርገዋል፡፡

የእንሰሳት ዝርያ ማሻሻያ ስራዎች ልቅ የሆነ የውጭ ዝርያዎች ስርጭት በሀገር በቀል ዶሮና ዳልጋ ከብት ዝርያዎች ላይ ተጽዕኖ ፈጥሯል፡፡ በአጠቃላይ የሰብልና የእንስሳት ልማት አካሄድ እና የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ስርአታችን የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን በማባባስ አሁን የሚታየውን የምርትና ምርታማነት እድገት ላይ ተፅዕኖ በማድረስ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ፈታኝ ያደረገዋል፡፡

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የመሬትና ተፈጥሮ ሃብት ልማት፣ የቴክኖሎጂ ማፍለቅና ማስረፅ፣ የግብዓት አቅርቦት፣ የፋይናንስ አገልግሎት፣ የሜካናይዜሽን አገልግሎት እንዲሁም የተቀናጀ መሰረተ ልማት ማስፋፊያ (መስኖ ልማትን ጨምሮ) ስራዎች እየተለዋወጠ ከመጣው የአየር ፀባይ በሚመልስ መልኩ በመተግበር ከአየር ንብረት ለውጥ እና ከተፈጥሮ ጋር የተሰተጋበረ ግብርና ልማት ይተገበራል፣
- የግብርና ምርትና ምርታማነት ዘላቂነትን ለማረጋገጥ የአካባቢ፣ የተፈጥሮና ብዝሀ ሕይወት ሀብት እንክብካቤና አጠቃቀም ውጤታማነትን ለመጨመር፣ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ የአካባቢ ሚዛንን ለማስጠበቅ እና በየጊዜው የሚከሰቱ የተፈጥሮ መዛባት መስተጋብር የሚፈጥር ግብርና ልማት እንዲተገበር ይደረጋል።

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተሰተጋበረ ግብርና ልማት ስትራቴጂ ይሻሻላል፣የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓትና ተቋማዊ አደረጃጀት ይዘረጋል፣
- ብዝሃ ሕይወት ጥበቃና አጠቃቀም ስትራቴጂ ይሻሻላል፣ የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓት ይጠናከራል፣
- የተቀናጀና ከተፈጥሮ ጋር የተስተጋበረ ግብርና (Regenerative Agriculture) ስትራቴጂ ይዘጋጀል፣ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- ዘላቂ የግብርና ምርታማነት ስርዓት ስትራቴጂ እና የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የአሰራር ስርዓትና ተቋማዊ አደረጃጀት ይዘረጋል።

### 5.10.2 የምግብ ዋስትና እና አደጋን የመቋቋም አቅም ማጠናከር

በተለያዩ ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሮአዊ አደጋዎች ምክንያት ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሁም የመልማት እምቅ አቅም በተለያዩ ምክንያት ያልተጠቀሙ የምርት ስርዓቶች ትኩረት ያደረገ የግብር ልማት የዜጎችን ተጋላጭነት ለመቀነስ እና የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ያስችላል። እስከ አሁንም በተደረጉ ጥረቶች መንግስት የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ በመንደፍ ከየአካባቢው ሁኔታ ጋር የተጣጣመ ልማት ለማከናወን በድርቅ አካባቢዎች የሚተገበር ስራ በመለየትና ልዩ ልዩ ድጋፍ የመስጠት አቅጣጫዎች አስቀምጧል። በልማታዊ ሴፍቲኔት እስከ 3.9 ሚሊዮን የሚደርሱ ተጠቃሚዎች ጥሪት አፍርተው ከድጋፍ እንዲወጡና በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ዋስትናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል። በተጨማሪም ዜጎች ለተለያዩ ሰው ሰራሽ እና

ተፈጥሮአዊ አደጋዎች ሲጋለጡ በጊዜያዊነት የሚያጋጥማቸውን የምግብ ክፍተት መሙላት እና አደጋን የመቋቋም አቅም ለመገንባት የሚያግዙ ስራዎች እየተከናወኑ ይገኛል፡፡

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- ስር ለሰደደ የምግብ ዋስትና አለመረጋጋጥ እና በተለያዩ ጊዜ በሚከሰቱ አደጋዎች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ውጤታማ ተሳትፎና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እንዲሆኑ ይደረጋል፣
- የአደጋ ስጋት ምላሽ አቅም እና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስርዓት ይጠናከራል፡፡

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ይሻሻላል፣ መዋቅራዊ አደረጃጀትና ቅንጅታዊ አሰራር ይዘረጋል፣
- የአደጋ ስጋት ምላሽ አቅም እና የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓት ይጠናከራል፣ መዋቅራዊ አደረጃጀትና ቅንጅታዊ አሰራር ይዘረጋል፣
- የግብርና ልማት ስር የሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር ያለባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎችን ትኩረት እንዲያደርግ የሚያስገድድ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣
- በገጠር የሚኖሩ ስር የሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር ያለባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ከግብርና ውጭ ባሉ የገጠር ኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ላይ ተሳታፊ እና ተጠቃሚ የሚያደርግ ስርዓት ይዘረጋል፡፡

### 5.10.3 የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት

ከሀገራችን ማህበረሰብ ውስጥ ግማሽ ያህሉ ሴቶች ሲሆኑ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካ መስክ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡ ግብርና በአመዛኙ በቤተሰብ ጉልበት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ሴቶች ከፍተኛ አስተዋፆ ያበረክታሉ፡፡ በተጨማሪም በገጠር ከግብርና ውጪ የሚከናወኑ የገቢ ማስገኛ ተግባራት እንዲሁም በአትክልትና እንስሳት እርባታ ስራዎች ላይ በመሳተፍ የቤተሰቡን ገቢ ከመደጎም ባለፈ የምግብና ስርዓት ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የላቀ ሚና እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡ ይህንኑ በመገንዘብ መንግስት የፖሊሲ ማእቀፎቹን የሴቶችን የመሬት ባለቤትነትና ተጠቃሚነት እንዲሁም

ሌሎች የግብርና ቴክኖሎጂ፣ ግብዓትና አገልግሎት ፍትሃዊ ተጠቃሚነት አቅጣጫ አስቀምጧል። ሆኖም ይህንን ውጤታማ ለማድረግ እና የሴቶች ለግብርና እድገት የላቀ አስተዋፅዎ ማበርከት የሚያስችሉ የህግ ማዕቀፍና አሰራር ስርዓት ወጥነት ባለው መልኩ አልተዘረጋም።

የሴቶችን ውጤታማ ተሳትፎና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ የተሟላ የህግ ማዕቀፍና የአሰራር ስርዓት ባለመዘርጋቱ በሴቶች ላይ ያለው የተዛባ አመለካከት የተነሳ ሴቶች ለግብርናው ልማት የሚያስፈልጉ ቴክኖሎጂዎችን፣ ግብዓትና አገልግሎቶችን መጠቀም ይቸገራሉ። በመሆኑም የሴቶች ምርታማነትና ተጠቃሚነታቸው ዝቅተኛ ሆኗል።

በባህላዊ አሰራር ተፅዕኖ እና በየደረጃዉ ከሚገኙ አስፈፃሚና ፈፃሚ አካላት የአመለካከትና የቁርጠኝነት መጓደል ሴቶች በመሬት፣ በብድር፣ በመስኖ ልማት፣ በስራ-እድል ፈጠራና በሌሎችም ጉዳዮች ከወንዶች እኩል የመወሰንና መጠቀም እድል አላገኙም። በተመሳሳይ መልኩ የኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ቀረፃና ይዘት በቤተሰብ መሪዎች ፍላጎቶችና ቅድሚያ በሚሰጧቸው ጉዳዮች ብቻ የተቃኘ በመሆኑ እና አባወራው በኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ከተካተተ ሴቶችም ቴክኖሎጂው ይደርሳታል በሚል የተዛባ እሳቤ የተመሰረተ መሆኑና ይህም አገልግሎት ባለትዳር ሴቶችን ፍላጎቶችና ጥቅሞች ለማካተት አልቻለም።

የግብርና ቴክኖሎጂዎች ዝግጅት በአብዛኛው የአርሶና አርብቶ አደር እማ-ወራዎችና ባለትዳር ሴቶችን ልምድ፣ እዉቀት፣ ልዩ ፍላጎት፣ ጉልበትና ጊዜ ከግምት ባለማስገባቱ የሴቶችን አቅም፣ ጉልበትና ጤናቸዉ ተስማሚ የሆነ ቴክኖሎጂ በበቂ መጠንና አይነት አይቀርብም። በተጨማሪም ስርዓተ-ፃታን ያማከለ የምርት ዱካን የተከተለና የእሴት ጭመራን ያካተተ የግብርና ምርት ገበያ ትስስር እንዲሁም የዘመናዊ የግብይት ቴክኖሎጂና የገበያ መረጃ አቅርቦት ተደራሽ አይደለም።

የሴቶች አደረጃጀት ወጥና የተናበበ ባለመሆኑ እና በበቂ የሰው ሀይል ባለመደራጀቱ በእውቀትና ክህሎት እንዲሁም በመረጃ ልውውጥ የተደገፈ አቅም መፍጠር አልተቻለም። ይህም በግብርና ገጠር ልማት በሚካሄዱ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶችና እቅዶች ውስጥ የሴቶች ጉዳይ በአግባቡ እንዳይካተት ሆኗል።

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- ሴቶች በግብርና ልማት ውጤታማ ተሳትፎና ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና ለዘርፉ እድገት የላቀ አስተአፆ ማበርክት እንዲችሉ የመሬት የመጠቀም መብት ፣ ኤክስቴንሽን ምክርና አገልግሎት፣ ቴክኖሎጂና ግብዓት፣ ፋይናንስ አገልግሎት፣ የገበያ ትስስርና እሴት ጭመራ አገልግሎት አቅርቦትና ተደራሽነት እንዲሁም ከግብርና ውጪ ባሉ የገጠር ኢኮኖሚ ልማት ተሳትፎቸውን ይረጋገጣል።

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- የስርዓት ፃታ እኩልነት ስትራቴጂ ይሻሻላል፣ መዋቅራዊ አደረጃጀትና ቅንጅታዊ አሰራር ይዘረጋል፣
- የገጠር መሬት የህግ ማዕቀፍ የሴቶችን የመሬት የመጠቀም መብት በሚያረጋግጥ መልኩ ይሻሻላል፣
- የሴቶች ጉልበት የሚቆጥብ የግብርና ቴክኖሎጂ ማቅረብና ማስፋፋት የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ አሰራር ስርዓት ይዘረጋል።

## 5.10.4 ዘላቂ የቆላማ አካባቢ ግብርና ስርዓት

በሀገራችን የመልካዓ ምድራዊ አቀማመጥ ዝቅተኛ የሆነ አካባቢ (ቆላማና/ አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር) ከጠቅላላው የቆዳ ስፋት ከ60 በመቶ በላይ የሚሸፍን ሲሆን ከ15 በመቶ በላይ ህዝብ ይኖርበታል። የኢኮኖሚ መሰረቱ በአብዛኛው በተፈጥሮ የግጦሽ መሬት ላይ የተመሰረተ የእንስሳት እርባታ ከመሆኑም በላይ ከአጠቃላይ የእንስሳት ሃብት ውስጥ 40 በመቶ ከዚሁ አካባቢ የሚገኝና ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት ፋይዳው ከፍተኛ ነው። የኑሮ ዘይቤውም በአብዛኛው አርብቶ አደር ስለሆነ ለኑሮው እና የአካባቢውን ሥርዓተ-ምህዳር፣ የአየር ንብረትና የተፈጥሮ ሀብቱን በተገቢው መልኩ ለመጠቀም ከቦታ ወደ ቦታ እየተንቀሳቀሰ የሚኖር የህብረተሰብ ክፍል ነው። ይህንኑ በመገንዘብ መንግስት የተለያዩ የአግሮ ኢኮሎጂ ዞኖች ጋር የተጣጣመ እንዲሁም በአርብቶ አደሩ አካባቢ የሚሰሩ ስራዎች የተኩረት አቅጣጫ አስቀምጧል። በቅርቡም የአርብቶአደር ልማት ፖሊሲና ማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች ፀድቀው ወደ ስራ ተገብቷል።

በእነዚህ አካባቢዎች የሚካሄዱ የግብርና ገጠር ልማት ስራዎች የአካባቢውን ሥርዓተ-ምህዳርና ዝናብ ሁኔታ፣ የመሬት አጠቃቀምና አስተዳደር፣ የእንስሳት ሀብት የመልማት

አቅም፣ የኑሮ ዘይቤ ባገናዘበ መልኩ የተቀናጀና ዘላቂ ልማት ስራዎችን ለመቃኘት የሚያስችል የህግ ማዕቀፍና አሰራር ስርዓት አልዳበረም፡፡ ይህንን የሚመራና የሚያስተባብር ጠንካራ መዋቅራዊ አደረጃጀትና ቅንጅታዊ አሰራር አልተዘረጋም፡፡

የልማት ስራዎች አካባቢውንና የህብረተሰቡን የአኗኗር ዘይቤ ከግምት ውስጥ ያላስገባና የትኩረት ማነስና ከፍተኛ የሆነ የግንዛቤ ክፍተት ያለበት በመሆኑ ዉጤታማ በሆነው የባህላዊና ልማዳዊ ዕውቀት ላይ ተመስርቶ ከቦታ ወደ ቦታ በመንቀሳቀስ የሚያከናውነውን የእንስሳት እርባታ ጎን ለጎን በተፋሰስ አካባቢዎች በማስፈር በሂደትም ወደ አርሶ አደርነት የመቀየር፣ ባህሉንም የመለወጥ ስልት እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡ የግብርና ኤክስቴንሽን ሥርዓቱም በአብዛኛው በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች ያሉትን ሰብል ተኮር የምርት ስርዓቶች ላይ ትኩረት የሰጠ በመሆኑ በአካባቢው ሲተገበር የነበረው የግብርና እና የኑሮ ማሻሻያ ሥራዎች በተለይም በእንስሳት ሃብት ልማት ላይ የተፈለገውን ውጤት ማስመዝገብ አልተቻለም፡፡ በተመሳሳይም የምርምር፣ የቴክኖሎጂና ግብዓት፣ የፋይናንስ አቅርቦትና ሥርጭት ሥርዓቱም የተጠናከሩ አይደሉም፡፡

የመሬት አጠቃቀምና አስተዳድሩም የአካባቢውን ባህላዊ የመሬት ስሪት ከግምት ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ ሰፊ የሆነው የግጦሽ መሬት ከህብረተሰቡ አኗኗር ውጪ ለሆነ አገልግሎት እንዲውል መደረጉና በዚህም ተፈላጊ የሆኑ የግጦሽና የውኃ መጠቀሚያ ኮሪደሮች መዘጋት፣ ተደጋጋሚ ድርቅና የአየር ንብረት ለውጥ በአካባቢው ሥርዓተ-ምህዳር ላይ ጉዳት በማስከተሉ በህብረተሰቡ አኗኗር ላይ ከፍተኛ ጫና መፍጠሩ፣ ሰፋፊ የግጦሽና በመስኖ ሊለማ የሚችል መሬት በመጤ እጽዋትና ቁጥቋጦ መወረር እና ባህላዊ የሆኑ የማህበረሰቡ እውቀት ትኩረት መነፈግና ተቋማቱ እየተዳከሙና ብሎም እየጠፉ መሄዳቸው ለተለያዩ ችግሮች ዳርገውታል፡፡ እንዲሁም አካባቢው በአብዛኛው ወቅቱን ያልጠበቀና አነስተኛ የዝናብ መጠን የሚያገኝ ከመሆኑም በላይ በሚከሰተው ከፍተኛ የአየር ሙቀትና አፈር ክለት የተነሳ ከሚዘንበው ዝናብ አብላጫው በትነትና በጎርፍ አማካይነት የሚባክንበት በመሆኑ ለተደጋጋሚ ድርቅ ተጋላጭ ነው፡፡

**የፖሊሲ አቅጣጫው**

- የቆላማ አካባቢ ግብርና ምርትና ምርታማነትን በዘላቂነት ለማረጋገጥ የአካባቢውን ሥርዓተ-ምህዳርንና የአኗኗር ዘይቤን ባገናዘበ መልኩ እንዲስፋፋ ይደረጋል ፣

- በገበያ የሚመራ እንስሳት ሃብት ልማት፣ ውሃን ማእከል ያደረገ የሰብልና የእንስሳት መኖ ልማት፣ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት፣ የመሬትና ተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምና አስተዳደር፣ የተቀናጀ የግብርና የምርምርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት፣ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የአደጋ ተጋላጭነትን ለመቀነስና የመቋቋም አቅምን ማጠናከር ላይ በትኩረት ይሠራሉ፣
- የገጠር ፋይናንስ እና የቴክኖሎጂና ግብዓት አቅርቦቶች ተደራሽነት ይሻሻላል፣
- አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ልማትን ከሌሎች ኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር እንዲተሳሰር ይደረጋል፣ አማራጭ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች እንዲስፋፉ ይደረጋል፣ በከተማና ገጠር ትስስር ይጠናከራል፣የተቀናጀ የገጠር መሠረተ ልማቶችንና አገልግሎቶችን እንዲስፋፉ ይደረጋል።

**የማስፈፀሚያ ስልቶች**

- ዘላቂ የቆላማ አካባቢ (አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር) ግብርና ስትራቴጂ ይነደፋል፣ የህግ ማዕቀፍ ይቀረፃል፣ የአሰራር ስርዓት፣ ተቋማዊ አደረጃጀትና ቅንጅታዊ አሰራር ይዘረጋል።

## 5.10.5 የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ዋስትና ስርዓት

የዜጎችን አካላዊና አእምሮአዊ ጤንነት የተሟላ ለማድረግ ጥራቱና ደህንነቱ የተጠበቀና በንጥረ-ምግብ ይዘቱ የተሟላ በቂና የተሰባጠረ የምግብ አቅርቦት አስፈላጊ ነው። የግብርና ዘርፉ በሀገራዊ ኢኮኖሚ እና ማህበራዊ እድገት የላቀ ሚና እንዲጫወት በግብርና ዘርፉ ተዋናይ የሆነው አምራች ሀይል የምግብና ሥርዓተ ምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ግድ ይላል። መንግስት የዜጎቹን የስርዓተ-ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ የምግብና ሥርዓተ ምግብ ፖሊሲ አቅጣጫ ያስቀመጠ ሲሆን ይህም በአብዛኛው ግብርናን ያማከለ የስርዓተ ምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ላይ ያተኮረ ነው። የግብርናው ዘርፍም ስርዓተ-ምግብ ተኮር ግብርናን ተግባራዊ ለማድረግ ስትራቴጂ ቀርፆ በመተግበር ላይ ነው።

ነባሩ ፖሊሲ የተሰባጠረ፣ ደህንነቱ የተጠበቀና በቂ የምግብ አቅርቦት በቤተሰብ ደረጃ እንዲረጋገጥ ከማድረግ አንፃር የተቃኘ አልነበረም። በንጥረ-ምግብ ይዘታቸው የበለፀጉ ምርቶች ላይ ያለው ትኩረት አናሳ መሆን የግብርናው ዘርፍ የምርት ስርዓት፣

የምርምር ውጤቶች፣ ብዜትና ስርፀት እንዲሁም የግብርና እሴት ሰንሰለቱ ስርዓተ-ምግብ ተኮር እንዳይሆን አድርጎታል። በዚህም ምክንያት የእንስሳት ተዋፅኦ፤ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ዋጋ ከፍተኛ ከመሆኑ በተጨማሪ በገበያ በተፈለገው አይነትና መጠን አይገኝም። እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ግብርናው የምግብ ስርዓት (Agri-Food system) ማዕከል ባደረገ መልኩ መቃኘትና የአምራቹን ማህበረሰብ የስርዓተ-ምግብ ማሻሻል ያስፈልጋል።

### የፖሊሲ አቅጣጫው

- ለዜጎች በቂ፣ የተሰባጠረ፣ በንጥረ-ምግብ ይዘቱ የበለፀገና ደህንነቱ የተረጋገጠ ምግብ አቅርቦትን፣ ተደራሽነትንና አጠቃቀምን በዘላቂነት ይሻሻላል፣
- በምግብ ንጥረ ነገር ይዘታቸው የበለፀጉ የግብርና ምርቶች ምርትና ምርታማነትን እንዲያድግ፣ ዋጋቸውም ተመጣጣኝ እንዲሆን፣ የምርቶቹን የምግብና የንጥረ-ምግብ ብክነትን ለመቀነስ፣ የምርቶችን ጥራትና ደህንነት ለመጠበቅ፣ የተሰባጠረ የአመጋገብ ባህልን ለማስረፅ በትኩረት ይሰራል።

### የማስፈፀሚያ ስልቶች

- የሥርዓተ-ምግብ ተኮር ግብርና ስትራቴጂ ይሻሻላል፣ የህግ ማዕቀፍ ይነደፋል፣ የማበረታቻና አሰራር ስርዓት እና ተቋማዊ አደረጃጀትና ቅንጅታዊ አሰራር ይዘረጋል።

## 6. የፖሊሲው አፈፃፀም ማዕቀፍ

ይህን ፖሊሲ ወደ መሬት ለማውረድ የሚያስፈልጉ ራሳቸውን የቻሉ ፖሊሲዎች፣ የህግ ማዕቀፎች፣ ስትራቴጂዎች፣ የአሰራር ስርዓቶች እና ተቋማዊ አደረጃጀቶች ማሻሻያ በተደረገባቸው በዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮች ከላይ በተዘረዘሩብት መሰረት በአጭር፣ መካከለኛ እና በረጅም ጊዜ ተቀርፀው ወይም ተዘርግተው ይተገበራሉ።

## 7. ፖሊሲውን የማስፈፀም ኃላፊነት ያለባቸው ተቋማት

ይህንን ፖሊሲ ለማስፈፀም የፌዴራል መንግስት እና የክልል መንግስታት በቅንጅትና ትብብር መንፈስ ይሰራሉ፡፡ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የፌደራልና ክልል የግብርና ዘርፍ ፈፃሚ ተቋማት የጋራ መድረክ ይቋቋማል፡፡

ይህንን ፖሊሲ ለማስፈፀም የበርካታ የፌዴራል እና የክልል ተቋማት ሚናና ሃላፊነት የሚጠይቅ ሲሆን የግብርና ሚኒስቴር እና ከክልል ግብርና ቢሮዎች የግብርና ልማትና ግብይት ተግባራትን በዋናነት ይተገብራሉ፣ ያስተባብራሉ፣ በተጨማሪም መንግስት የገጠር ልማትን የሚያስተባብር ተቋም ይሰይማል፡፡

## 8. የፖሊሲ ክትትል፣ የግምገማ እና የክለሳ ስርዓት

የፖሊሲውን ትግበራ ለመከታተል እና ውጤታማነቱን ለመለካት ጠንካራ የክትትልና ግምገማ ስርዓት ይዘረጋል፡፡ በተጨማሪም የተመረጡ የፖሊሲ አቅጣጫዎች በሰፊው ስራ ላይ ከመዋላቸው በፊት በሙከራ ሲተገበሩ የተጠናከረ መረጃ ማሰባሰብና ትንተና ስርዓት ይዘረጋል፡፡ ከእነዚህ ስርዓቶች በሚመሰበሰብ መረጃ ትንተና መሰረት ፖሊሲው እንደ አስፈላጊነቱ እንዲከለስ ይደረጋል፡፡

## 9. የፖሊሲው ስርጭት

የፀደቀው የፖሊሲ ሰነድ በህትመትና በሌሎች የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለባለድርሻ አካላት እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

## 10. ፖሊሲው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ

ፖሊሲው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ከፀደቀበት ________________ ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ·à. የቃላት መፍቻ

**'አርሶ አደር'** ማለት ከግብርና ስራ ባገኘው ገቢ እራሱን እና ቤተሰቡን የሚያስተዳደር የኢኮኖሚ ተዋንያን ነው።

**'የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች'** ማለት የመሬት ይዞታቸው ከአስራ ሄክታር ያልበለጠና በጥርም እርሻ እንስሳት ርባት የሚተዳደር የገጠር ማህበረሰብ አካል ነው።

**'አርብቶ አደር'** ማለት የግጦሽ መሬት በመያዝና ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ በዋነኝነት እንስሳት እርባት ላይ ኑሮው የተመሰረተ የገጠር ህብረተሰብ አካል ነው።

**'ከፊል አርብቶ አደር'** ማለት በዋነኝነት የግጦሽ መሬት በመያዝና ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ ላይ የተመሰረት እንስሳት እርባት እና በተወሰነ ደረጃ በእርሻ ላይ ኑሮው የተመሰረተ የገጠር ህብረተሰብ አካል ነው።

**'የመካከለኛና ሰፋፊ ግብርና'** ማለት የፀና የንግድ ፍቃድ ኖሮት በካፒታልና እውቀት ላይ የተመሰረት እና አስር ሄክታር እና ከዚያ ባለይ የእርሻ መሬት ወይም ከተወሰነ የእንስሳት ቁጥር በላይ የሚከናወን የግብርና ልማት ነው።

**'ግብርናን ማሻገር'** ማለት ለገበያ የሚያመርት፣ ከፍተኛ ቴክኖሎጂና ግብዓት የሚጠቀም፣ የላቀ የሰው ሃይል ምርታማነት፣ እሴት የሚጨምር ሆኖ የዘመነ፣ አሳታፊና ዘላቂ የግብርና ሽግግር ነው።

**'የገጠር መዋቅራዊ ለውጥ'** ማለት የገጠር ነዋሪዎች ሁለንተናዊ የለውጥ ጉዞ የሚያመላክት ሆኖ በግብርና ላይ ብቻ ተንጠልጥሎ ያለውን የኑሮ መሰረታቸውን በማሰባጠር በገጠር ሌሎች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች እና የቢስዘነስ ዕሳቤዎች ተስፋፍተው በገጠርና በከተማ ጠንካራ የንግድና አገልግሎት ግንኙነት መፍጠር ነው።

**'የገጠር ነዋሪ'** (rural household) ማለት በገጠር በግብርና ስራ፣ አርብቶና ከፊል አርብቶ አደሮችን እና በሌሎች የኢኮኖሚ እንቅስሳሴዎች ኑሮው የተመሰረት ነው።

**'የግብርና ምርቶች'** ማለት በጥሬው የተመረተ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ እሴት የተጨመረበት የሰብል (እህል፣ አትክልትና ስራስር፣ ፍራፍሬ፣ አበባ፣ የቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም፣ የመኖ ሰብሎችን ጨምሮ) ፣የእንስሳት (የዳልጋ ከብት፣ በግ፣ ፍየል፣ የጋማ ከብት፣ ግመል፣ ዶሮ፣ ንብ፣ ዓሣ፣ የሐር ትል፣ አሳማ፣ ጥንቸልና ወደፊትም

ሊላመዱ የሚችሉትንም ጨምሮ) እና የተለያዩ ከሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ደን ውጤቶች (የግንባታ፣ የማገዶ፣ የምግብና መድሃኒት፣ ኢንዱስትሪ፣ ሙጫና ዕጣን፣ ቀርከሃ ጨምሮ) እና የደን አገለግሎቶች ማለት ነው።

**'መሬት ማሰባሰብና ማዋሃድ'** (Land consolidation) ማለት አነስተኛ መሬት ባለይዞታዎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የተበጣጠሱ መሬቶችን ማለዋወጥ እና ኩታ ገጠም ማድረግ እንዲሁም የጋር ባለቤትነት በማስፈን በሂድትም ካፒታልና እውቀት የያዙ ተዋንያኖች በጋር የሚያሳትፍ ማምረት፣ የመጀመሪያ ደረጃ እሴት ጭመራ፣ ግብይትና ማቀነባበር ተግባራትን ያካትታል።

**'ቴክኖሎጂ'** ማለት በግብርናው ዘርፍ በሚደረጉ የምርምርና ፈጠራዎች ውጤት ሲሆን የእፅዋት እና እንስሳትና አሳ ዘርና ዝርያዎች፣ ስነ-ህይወታዊና የተፈጥሮ ማዳበሪዎች፣ አዳዲስ እና የተሸሻሉ የእርሻ ማሳሪያዎች፣ ደቂቅ ዘአካላት፣ መድሃኒታማና መአዛማ ኬሚካሎች፣ የሰብልና እንስሳት ጤና ጥበቃ የምርምር ውጤቶች፣ የእንስሳት መኖና ስነ ምግብ እንዲሁም የአሠራርና የአመራረት ስልቶች ምክረ ሃሳብን ያካትታል።

**'ግብዓት'** ማለት ከምርምር የወጡ ቴክኖሎጂዎች ተባዝተው ለተጠቃሚዎች የሚደርሱ የሰብል፣ እንስሳትና አሳ እና ደን ምርትና ምታማነትን የሚያሳድጉ፣ የሰው ሃይል ምርትማነትን የሚጨምሩ፣ የአፈር ለምነትና ጤንነት የሚያሻሽሉ፣ የእፅዋት እና እንስሳት ጤናን የሚጠብቁና የሚከላከሉ፣ መሬት በዛቂነት ለመጠቀም የሚያስፈልጉትን እና የመሳሰሉትን ያካትታል።

**'አገልግሎት'** ማለት ቴክኖሎጂና ግብዓትን (ተያያዥ ዕውቀትና ክህሎት ጨምሮ) ለተጠቃሚዎች ማቅረብ ሲሆን የኤክስቴንሽንና ምክር፣ የሜካናይዜሽን፣ የእፅዋት ጥበቃ፣ የእንሰሳት ጤናና ደህንነት እና የመሳሰሉትን ያካትታል።

**'የግብርና ውሃ'** ማለት ከዝናብ ከገጸ-ምድርና ከርሰ ምድር ምንጮች የሚገኝ ውሃ ሰብል ለማምረት፣ ለእንስሳትና አሳ እርባታ፣ ለተፈጥሮ ሃብትና ለደን ልማት የተላያዩ የውሃ አጠቃቀም ስልት በማቀናጀት የመስኖ ልማትን፣ የተፋሰስ፣ የአፈርና ውሃ አያያዝና አጠቃቀምን፤ የውሃ ተፋሰስንና የእርጥበታማ መሬቶች አያያዝን ያካትታል።

**'ረቂቅ ግብርና'** (Precision Agriculture) ማለት የማምረቻ ግብዓቶችን ብክነት በከፍተኛ ሁኔታ የቀነሰ ግብርና ሆኖ ባደገ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም የአመራረትና ምርት ላይ አዋኪ

ስነ-ህይታዊም እና ኢ-ህይወታዊ ተግዳሮቶችን በአስተማማኝ መቆጣጠር የቻለ፣ ስማርት (Smart) ግብርና ስርዓቶች የተከተለ፣ የመረጃ ቅብብሌሽና ፍሰት ማቀላጠፊያዎች እና የጂ.አይ.ኤስ ቴክኖሎጂ ግብርና ያካትታል፡፡

**'አካታች'** ማለት ሁሉንም የግብርናና ገጠር ልማት የሚመለከታቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ማለትም አርሶአደር፣ አርብቶ አደር፣ ከፊል አርብቶ አደር፣ የከተማ ግብርና ተዋንያን፣ ሴቶች፣ ወጣቶች፣ የግል አልሚ፣ የእሴት ሰንሰለት ተዋንያን ተሳትፎና ተጠቃሚነትን መሰረት በማድረግ የምግብና ስርዓተ ምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ነው፡፡

**'የምግብ ሉዓላይነት'** ማለት ከምግብ ተመፅዋችነት ለመላቀቅ እንዲሁም ከውጪ የሚገቡ የግብርና ምርቶች በሃገር ውስጥ ምርት ለመተካት የግብርና ምርትና ምርትማነት በማሳደግ የሀገርን ሉዓላይነት ማስጠበቅ ነው፡፡

**'ካፒታል'** ማለት ወደ ግብርና ዘርፍ ከተለያዩ ተዋንያን የሚፈስ ገንዘብ እና የግብርና ምርት ለማምረት ጥቅም ላይ የሚውሉ አካላዊ ግብዓቶች ያካተተ ነው፡፡

**'የፆታ አገላለፅ'** በዚህ ፖሊሲ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው ሁሉ የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡